# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ትግበራና አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

**መጋቢት 2011**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


ማውጫ ........ i

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summary) ...... I

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አመሰራረት ........ 1

የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP) ........ 3

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ ........ 5

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ ........ 7

የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የከተማ ልማት ዘርፍ) አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 8

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 8

የሰው ኃይል ........ 8

የፋይናንስ ምንጭ ........ 9

ሰንጠረዥ አንድ- :የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከ2007 እስከ ታህሳስ 30 2011 ዓ.ም ድረስ የተመደበው በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ ........ 9

ሰንጠረዥ2- የULGDP II ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከ2007 እስከ ታህሳስ 30/2011 ዓመት የተመደበው በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ ........ 10

የኦዲቱ ዓላማ ........ 10

የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ........ 10

የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issues) ........ 10

ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 11

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 11

ክፍል ሁለት ........ 13

የኦዲት ግኝቶች ........ 13

2.1 ዕቅድና በጀትን በተመለከተ (Planning and Budgeting) ........ 13

የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ (CIP) መዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ........ 13

ለጥገና የሚወጣው በጀት እና አፈጻጸሙ ከእቅዱ ከ80 ፐርሰንት አለማነሱን በተመለከተ፣ ........ 16

2.3 የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ (Financial Management) ........ 20

ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት መካሄዱን በተመለከተ፣ ........ 20

የሚዘጋጁ የግንባታ ግብዓቶች መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) ዝግጅትን በተመለከተ፣.....22
ከተሞች ለሚያሰሯቸው ፕሮጀክቶች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ መክፈላቸውን በተመለከተ፣.....24
የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣.....27
የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣.....30
ከተሞች ከፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን በተመለከተ፣.....32
2.4 የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ግዢን (Procurment) በተመለከተ.....37
ለፕሮጀክቶች የጨረታ ሂደት ከመጀመሩ በፊት የተሟላ ዲዛይን ስለመዘጋጀቱ፣.....37
የአፈር ምርመራና የቅየሳ (ሰርቬይ) ጥናት በአግባቡ መሰራቱን በተመለከተ፣.....39
ሚ/ር መ/ቤቱ የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣.....44
ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያካሂዱ ተቋማት ግዥ/ ቅጥርን በተመለከተ፣.....47
2.5 ገቢን በራስ አቅም የመሰብሰብና የማሳደግ አቅምን በተመለከተ (Own Source Revenue Enhancement).....49
ከተሞች በየዓመቱ ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ማሳደጋቸውን በተመለከተ፣49
2.6 ግልፅነትና ተጠያቂነትን በተመለከተ (Accountability and Transparency).....53
ከተሞች የአገልግሎት ስታንዳርድ አውጥተው በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣.....53
ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣.....58
2.7 የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናቶች ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘቡ መሆኑን በተመለከተ (Environmental and Social Safeguards).....59
የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናትን በተመለከተ፣.....59
2.8 የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ (Job Creation).....65
የሁለተኛው የከተሞች አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች (ዩኤልጂዲፒ) ላይ በተቀመጠው ዕቅዱ መሰረት አዳዲስ የስራ እድል ስለመፍጠሩ፣.....65
2.9 የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ መሰራታቸውን በተመለከተ (Quality of Infrastructure).....67
የመሰረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው መሰራታቸውና ለተባለላቸው አገልግሎት እየዋሉ ስለመሆኑ፣.....67
የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ መተላለፋቸውን በተመለከተ፣.....75

2.10 ከፕግራሙ ጋር የተያያዙ መረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ......................76
የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣........................76
በፌዴራል እና በክልል ያሉ ባለሙያዎች የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ፣..............78
በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፣..........79
ክፍል ሦስት ..........81
መደምደሚያ..........81
ክፍል አራት..........86
የማሻሻያ ሃሳቦች ..........86
አባሪ አንድ፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች..........92
አባሪ ሁለት፡ የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢቸውን ሊዝን ጨምሮ በ10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች ..........95
አባሪ 3፡ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞብላይዘሽንና ፋይናንስ ቢሮ አደረጃጀት .......98
አባሪ 4፡ በወቅቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን ያላዘጋጁ ከተሞች..........99
አባሪ 5፡ ከ2007 እስከ 2010 ከ80 ከመቶ በታች የጥገና አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች.....102
አባሪ ስድስት፡ ከ2007 -2010 በጀት አመታት በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ..........103

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive Summary)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ትግበራና አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህን የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2001 እስከ 2011 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ ከተሞች የመሠረተ ልማት ዕቅድ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 24 እ.ኤ.አ ሊያዘጋጁና በምክር ቤታቸው በማጸደቅ እንዲሁም የተከለሰው ዕቅድ እስከ የካቲት 6 እ.ኤ.አ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መቅረብ ቢኖርበትም በናሙና ባየናቸው ከተሞች የ2007፣ 2008፣ 2009 እና በ2010 ዓ.ም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተዘጋጅቶ የማያቀርቡ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ ለጥገና የሚወጣው በጀት አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 በመቶ ማነስ የሌለበት ሊሆን እንደሚገባ በፕሮግራም ኦፕሬሽን ማኑዋሉ ላይ ቢቀመጥም ከተጠቀሰው በታች አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ አብዛኛዎቹ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜና ዋጋ እንደማይጠናቀቁ፣
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ፣
- ✓ የአዳማ፣ የቢሾፍቱ፣ የሮቤ፣ የሐዋሳ፣ የባቱ፣ የዲላ፣ የደብረ ታቦር፣ የባህር ዳር፣ የአሰላ የከተማ አስተዳደሮች ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ማለትም Preliminary Design (Survey Data) እና የተለያዩ Drawing እንደማያዘጋጁ፣

- ✓ የከተሞች የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ መሆንና በእቅዱ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ እና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ቢገባም ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት የማያሳድጉ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት የሚዘጋጁትና በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ይሁንታ የሚያገኙ ፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ መሆኑ፣
- ✓ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ቢኖሩም የሕብረተሰብ የመልሦ ማስፈር ጥናት ሳይከናወን እንደሚሰራ፣
- ✓ በአብዛኛው የአካባቢና ማህበራዊ ደህንናት ልየታ (Screening) ሪፖርት ሲሰራ ከዓለም ባንክ ፈንድ ለመጠቀም ብቻ ሲባል እንጂ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይቶ የማይሰራ እንደሆነና የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአንዱን ለሌላው ኮፒ ፔስት በማድረግ ሪፖርቶቹ እንደሚዘጋጁ፣
- ✓ አንዳንድ ከተሞች የስራ ዕድል ለመፍጠር በበጀት ዓመቱ ካቀዱት አንፃር ግባቸውን እያሳኩ እንዳልሆነ፣
- ✓ በፕሮግራሙ ከሚሰሩት የመሠረተ ልማት ግንባታ መካከል የኮብል ስቶን ግንባታ ስራ የጥራት ችግሮች መኖር፣

በመሆኑም

- ✓ ከተሞቹ ማግኘት የሚገባቸውን ነጥብና ከፍተኛ ገንዘብ እንዳያጡ፣ በርካታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጀምሩና በወቅቱ እንዲጠናቀቁ እንዲሁም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲሰሩ የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ እንዲዘጋጅ ሊደረግና በወቅቱ በማጸደቅ ወደ ሥራ መግባት አለባቸው:: ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይሄ ስለመደረጉ ከፍተኛ ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ከተሞቹ ከፕግራሙ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረቱን ማጠናከር ይኖርበታል::
- ✓ በከተሞቹ የሚገኙት አብዛኛዎቹ መሰረተ ልማቶች ጥገና ስለሚያስፈልጋቸው ከተሞች ከአዳዲስ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ጎን ለጎን ለነዚህ መሰረተ ልማት አውታሮች አይነተኛ ትኩረት እንዲሰጡና ሥራው ቀጣይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው የሲአይፒያቸውን 10% ወይም የአጠቃላይ የከተማውን ሃብት 2% ለጥገና በጀት እንዲመድቡና በየዓመቱ በእቅድ እየያዙ መተግበር እንዲጀምሩ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ከፍተኛ ክትትልና

እገዛ ሊደርጉላቸውና ጥገናው በራስ ኃይል (አቅም) ወደፊት ለመስራና ዘላቂነት እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ፕሮጀክቶቹ በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራቸው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከተሞች ተገቢውን ክትትል ሊያደርጉና ላልተገባ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ እንዳይዳረጉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህብረተሰቡም እሮሮ እንዳይነሳባቸው ፕሮጀክቶች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሁሉን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በየዓመቱ በዕቅድ በመያዝ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ከተሞቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን እንዲዘጋጁ፣ የሚዘጋጁትም ዲዛይኖች ገለልተኛ በሆነ አካል ሊከለሱ ይገባል፡፡ በፌዴራል ሞባይል ቡድንና ይሄን ፕሮግራም እየረዱ ባሉት አማካሪዎች ከፍተኛ ግምገማ በማድረግ ከተሞቹን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች ሳይከናወኑ ግንባታዎች እዳይከናወኑ በየደረጃው ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር በማደረግ የመሰረተ ልማቶቹ ሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ከፕሮግራም ፈንዱ ለከተሞች የሚለቀቀው ገንዘብ በማሳወቅ ረገድ መዘግየት እንዳይፈጠር፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ ዝግጅት በወቅቱ እንዲካሄድ፣ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀመሩና ሚ/ር መ/ቤቱ በዚህ ረገድ በርካታ አሜሪካ ዶላር እንዳያጣ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በወቅቱ ማከናወን ይኖርበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሞች በፕሮግራሙ ላይ በተቀመጠው መሰረት በየዓመቱ ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት ባነሰ ሁኔታ የሚያሳድጉትን ከተሞች ተለይቶ የገቢ አሰባሰባቸው የሚያድግበትን ከእቅድ አንጻር አነስተኛ የሆነበትን መንስኤ አጥንቶ የሚሻሻልበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ሊያደረግላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከገቢ ጋር በተያያዘ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተከታታይ የአቅም ግንባታ እና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ✓ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊጠኑና ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ

በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጡት ተፅእኖ የሚቀነስበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

- ✓ በከተሞቹ በዕቅዱ መሰረት ለነዋሪዎቻቸው ጊዜያዊና ቋሚ የስራ ዕድል በፕግራሙ አማካኝነት ሊፈጥሩና በከተሞች ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥርን ከመቀነስ አኳያ ፕሮግራሙ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲሳካ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሥራ ዕድል ለመፍጠር በፕሮግራሙ የተቀመጠው አላማ እንዲሳካ የበኩልን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ በፕሮግራሙ የተሰሩ እየተገነቡ ያሉ እና የሚገነቡት የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ጥራታቸውን ጠብቀው ሊገነቡ እና ይህን በማያሟላ መልክ የሚሰሩ በየደረጃው ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተገነቡት መሰረተ ልማቶች በየጊዜው እየተበላሹ መንግስትም አላስፈላጊ ወጪ እንዳያወጣ፣ ለጥገና የሚወጣውን ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ለማዳን እንዲሁም የሚሰሩት የፕሮጀክት ግንባታዎች ለተፈለገላቸው ዓላማ ሳይውሉና የሚፈልግባቸውን ቆይታ ሳያከናውኑ እንዳይበላሹ እና ህብረተሰቡ በዚህ ምክንያት ቅሬታና እሮሮ እንዳያነሳ በየደረጃው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የግንባታዎቹን ጥራት ለመጠበቅ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትና በከተሞቹ ለሚገኙ ፕሮጀክቶቹን ለሚቆጣጠሩ የፕሮጀክት ኢንጂነሮችና ሌሎች ባለሙያዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር ስልጠናና የልምድ ልውውጥ በማዘጋጀት የባለሙያዎቹን ክህሎትና አቅም የሚገነባበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. መንግስት በአገሪቱ የተጀመረውን የተሃድሶና የትራንስፎርሜሽን እንቅስቃሴ በተሳካ አካኋን እንዲቀጥል የቤት ልማት ፕሮግራምና የከተሞች መሰረተ ልማት ስትራቴጂ ቀርፆ ከመቼውም የተሻለ ኢንቨስትመንት በማካሄድ ከተሞቻችን በተለያየ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገቡ አይነተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

2. በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ከአለም ባንክ ባገኘው እርዳታና ከከተሞች በሚመነጩ ፈንዶች 19 የተለያዩ ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች (Urban Local Governments) ተጠቃሚ በማድረግ አይነተኛ ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ ባለፉት አምስት አመታት ከተሞች በፕላን እንዲመሩ፣ የከተማ ነዋሪው ህብረተሰብ የመኖሪያ ቤት ባለቤት እንዲሆን፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የከተማ አገልግሎቶች ለተገልጋዩ እንዲቀርቡና በከተሞች የመሰረተ ልማት በማስፋፋት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እንዲፋጠን ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ አበረታች ለውጥ ተገኝቷል፡፡

3. በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመንም መንግስት የአገራችን ከተሞች እድገት ይበልጥ እንዲፋጠን እና ከተሞች ለአገራችን የኢኮኖሚ እድገት የሚያመጡትን አስተዋፅኦ ለማሳደግ ከእርዳታ ከሚገኘውና ከተሞች ከሚያመነጩት ገንዘብ የዘጠኝ ክልሎች፣ የአርባ አራት ማዘጋጃ ቤቶች እና የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴርን አቅም በማሳደግ አገሪቷ በ2017 መካከለኛ ገቢ ያላት አገር የመፍጠር ራዕይን ለማሳካት እየሰራ ይገኛል፡፡

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አመሰራረት

4. ባለፉት አምስት አመታት በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ዘርፍ እንደሌሎቹ ዘርፎች ሁሉ ፈጣን ልማትን በማረጋገጥ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ መሰረት በመጣል በአገራችን የተጀመረውን የተሃድሶና የትራንስፎርሜሽን እንቅስቃሴ በተሳካ አኳኋን እንዲቀጥል የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

5. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የስራና መገናኛ ሚኒስቴርን በትዕዛዝ ቁጥር 1/35 የቤት ልማትን ለመገንባት እና ለማስተዳደር እንዲሁም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና ካለበት ፈቀቅ እንዲል በትዕዛዝ የተቋቋመ ሲሆን

የተለያዩ የለውጥ ሂደቶችን አልፏል፡፡ በተለይም ተከታታዮቹ ሁለት ለውጦች ግን የስም ቅያሬን ጨምሮ ከፍተኛ የድርጅታዊ አቋምና ዓላማ ለውጦች ያስከተሉ ነበሩ፡፡

6. የቀድሞ የስራና መገናኛ ሚኒስቴር በ1969 ዓ.ም ከነበረበት የቤት ልማት በተጨማሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን በይበልጥ ለማሳደግና ለማሳለጥ እንዲሁም በመሬት ልማትና ማኔጅመንት እንቅስቃሴዎች ለመካፈል የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 8/80 ተቋቋመ፡፡

7. ከአምስት አመት በኋላም በአዋጅ ቁጥር 41/85 የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በመባል የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲያብቡ፣ የቤት ልማት ፕሮግራሞች የበለጠ እንዲሳኩ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎችን በይበልጥ እንዲያብቡ የመስራት ኃላፊነት ተረክቦ መስራት ጀመረ፡፡

8. በሚቀጥሉት ሁለት አመታት በአዋጅ ቁጥር 4/1987 እና 471/1987 ዓ.ም የስም ለውጥ ሳያደርግ በአዲስ አደረጃጀት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በመባል እየሰራ ቆየ፡፡

9. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በፀደቀው አዋጅ 471/98 መሠረት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተቋቋሟል፡፡ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በአዲስ መልክ ሲቋቋም በአዋጁ ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ የኮንስትራክሽን ዘርፍን የሚመለከቱት የቀድሞ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባሮችን የከተሞች ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባሮችን ይዞ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

10. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ባለፉት ዓመታት በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

11. ከዛም ከአምስት ዓመት በኋላ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሰረት የኮንስትራክሽን ዘርፍ እራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ እንዲደራጅ ከመደረጉ ጋር ተያይዞ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በመባል በከተሞች የመሠረተ ልማት አቅርቦት ላይ እንዲያተኩር በማድረግ እንዲቋቋም ተደረገ፡፡

12. በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በመባል በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP)

13. ይህ በ19 ከተሞች ከአለም ባንክ፣ ከክልልና ከከተሞች በድምሩ 203 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር ተመድቦ ከ2001 ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ የተከናወነ ፕሮጀክት ነው፡፡ የከተሞች አቅም በገቢ መሰብሰብና በፋይናንስ አስተዳደር አሳታፊ የሆነ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ የመፈፀም አቅም በማሳደግና የመሠረተ ልማት አቅርቦት መሻሻል በመቻላቸው እና ከተሞች ለአምስት ዓመት የተፈቀደውን በሁለት ዓመት ተኩል ተጠቅመው በማጠቃለላቸው ተጨማሪ 150 ሚልዮን ዶላር ከአለም ባንክ ተፈቅዶ ፕሮግራሙ ሊከናወን ችሏል፡፡

14. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ

- ✓ የማስፈጸም አቅምን መሠረት በማድረግ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው በቂ የመሠረተ ልማት አገልግሎት ለማቅረብ፣
- ✓ የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት ፕሮግራሞችንና በጅምር ላይ ያሉ የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣
- ✓ እንዲሁም ዘላቂና ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥና በተገቢው ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን አቅም እንዲፈጥሩ ማገዝ ነው፡፡

15. የሁለተኛው ምዕራፍ የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP II) ከመጀመሪያው ምዕራፍ የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP I) የቀጠለ ነው፡፡ ULGDP II የተጀመረው በ2007 ዓ.ም ሲሆን እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የሚቀጥል ሲሆን 44 ከተሞች ከዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ULGDP II በመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠቃሚ የነበሩትን 18 ከተሞች (አዲስ አበባን በመተው) ጨምሮ 26 አዳዲስ ከተሞች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

16. የፕሮግራሙ አጠቃላይ ማስፈፀሚያ በጀት 556.55 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በቀጥታ ለ44 ከተሞች ለመሰረተ ልማት አገልግሎት የሚውል ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ መሰረት በማድረግ ለከተሞች የሚተላለፍ 499.5 ሚሊዮን ዶላር፣ ለክልሎች

አቅም ግንባታ አገልግሎት የሚውል 30 ሚሊዮን ዶላር እና ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር አቅም ግንባታ አገልግሎት የሚውል 27 ሚሊዮን ዶላር ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ከኢትዮጵያ መንግስት የተመደበ 176.55 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ከዓለም ባንክ የተመደበ 380 ሚልዮን ነው፡፡

17. በULGDP II የሚካፈሉ 44 የከተማ መስተዳደሮች፡-

- ✓ 18 ከተሞች[1] ባልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት (Capacity Building for Decentralized Service Delivery) ተጠቃሚ የነበሩ ሲሆኑ አዲስ አበባ ከዚህ ውጪ ሲሆን ሌሎቹን በመጀመሪያው ማጣቀሻ ተመልክተዋል፡፡
- ✓ 18 ከተሞች[2] በULGDP የአቅም ግንባታ ድጋፍ ብቻ የሚደረግላቸው ሲሆኑ በሁለተኛው ማጣቀሻ ተመልክተዋል፡፡
- ✓ 8 ከተሞች[3] እነዚህ ደግሞ ከKfw (Kreditanstalt fur Wiederauufbau) ኢንቨስትመንት ድጋፍ የሚያገኙና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ደግሞ ከGIZ (Duetsche Gesellschaft fur Internationale Zusammenarbeit GmbH) የሚያገኙ ናቸው፡፡

18. የሁለተኛው ምዕራፍ የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ዓላማ

- ✓ የከተማ አስተዳደሮቹ በዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ወቅት የከተማ ነዋሪዎቹን ባሳተፈ መልኩ እንዲሆን ማድረግ፣
- ✓ ቀልጣፋ የሆነ የገንዘብ ቁጥጥር እንዲኖር ማድረግ፣
- ✓ ገቢያቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እንዲል ማድረግ፣
- ✓ በሚሰጡ ውሳኔዎች ተጠያቂነትን ለማስፈን፣
- ✓ በአጠቃላይ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የዜጋውን እርካታ ለማሳደግና ዘላቂና ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ መሠረተ ልማት በመገንባት የከተሞችን ልማት ለማፋጠን ነው፡፡

---

[1] ድሬደዋ፣ ሐረር፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ሻሸመኔ፣ ጅማ፣ ሃዋሳ፣ ዲላ፣ ወ/ሶዶ፣ አርባ ምንጭ፣ ባ/ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ አክሱም እና ሽሬ እንደስላሴ

[2] አሰላ፣ ቡራዩ፣ ሰበታ፣ አምቦ፣ ሮቤ፣ ባቱ፣ ደ/ብርሃን፣ ደ/ታቦር፣ ወልዲያ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ አላማጣ፣ ሁመራ፣ ውቅሮ፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም፣ አረካ እና ቡታጅራ

[3] አድዋ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ሆሳዕና፣ ነቀምቴ፣ ጋምቤላ፣ ሰመራ፣ አሶሳ እና ጅግጅጋ

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ (የከተማ ልማት ዘርፍ)**

19. ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ልማትና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያረጋግጡ፣ ለኑሮ አመቺና በፕላን የሚመሩ እንዲሆኑ በማድረግ የአካባቢያቸውን የልማት ማዕከልና የዲሞክራሲ ተምሳሌት ሆነውና እርስ በርስ ተሳስረው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን በማረጋገጥ በልፅገው ማየት፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ (የከተማ ልማት ዘርፍ)**

20. የተቋሙን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በከተሞች እንዲቀርብ በማድረግ ከተሞች የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት ሆነው ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፡፡

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር**

21. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፣

- የከተማ ልማትንና ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን የልማት ፓኬጆችን እና ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና አገራዊ ስፓሻል ፕላን ኢንዲሰራ በማድረግ የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- ከተሞች ከአገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፣
- ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣

- የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የህዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግስታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፣
- የከተሞችን መሬት በቁጠባ መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ስልት ይነድፋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፣ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፣
- የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፣ የከተማ የምግብ ዋስት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣
- የአዲስ አበባንና የድሬደዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፣
- የነፃ ገበያ ስርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ስርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፣ በከተሞች ፍልሰትን መሰረት ያደረገ የለማ የመሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሰጣል፣
- የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ስርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካልእንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፣
- የኮንስትራክሽን ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ይተገብራል፣ ለዘርፉ እድገት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ይተግብራል፣
- በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣

በዲዛይን፣ በጨረታና በኮንትራት ይዘት ላይ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

- በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፣
- በፌዴራል መንግስት በጀት ለሚሰሩ ሕንፃዎች፣ ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
- የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፣
- አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሀንዲሶችና አርክቴክቸሮችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወሰናል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መስራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## በሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ

22. የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /System description/ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

- ✓ ቢሮው ሴክተሩ የሚፈልገውን የፋይናንስ ፍላጎት በመተንተን የፋይናንስ ፍላጎቱን ለመሙላት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣
- ✓ ከአበዳሪና ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ ፈንድ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ✓ ከተሞች የገቢ ማመንጨት አቅማቸው እንዲጎለብት የሚያስችሉ ሥራዎች እንዲከናወኑ ማስተባበርና መደገፍ፣

- ✓ የተገኙ ፈንዶችን በአግባቡ ማስተዳደርና ለተፈለገለት ዓላማ እንዲውል መከታተል፣ መቆጣጠር፣
- ✓ የፕሮጀክት ግዢዎች በፍጥነት ተከናውነው ፕሮጀክቶች በወቅቱ እንዲፈጸሙ የመከታተልና የመቆጣጠር፣
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀረጹ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና እቅዶች የበጀት ፍላጎት ውጤትን መሰረት አድርጎ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣
- ✓ የአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማ እና ጥናት ማድረግ ፣
- ✓ የፕሮግራም በጀት አሰራር ማሻሻያ ሥርዓት በማጠናከር እና በማስረጽ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ የሆነ የበጀት አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ፣
- ✓ በበጀት ዝግጅትና አተገባበር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በማድረግ የእቅዶችን ተፈጻሚነት ማሳደግ ፣
- ✓ የመንግስትና የአበዳሪና ለጋሽ ድርጅቶች አሰራርና መመሪያን ተከትሎ ክፍያዎችን የመፈጸምና መረጃውን አደራጅቶ የመላክ ሥራን ማከናወን ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የከተማ ልማት ዘርፍ) አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡

24. የከተማ ልማት ዘርፍ በስሩ አራት ቢሮዎች (የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ፣ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፣ የከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቋቋሚያ ቢሮና የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ቢሮዎች) አሉት፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የከተማ ልማት ዘርፍ) ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ ሦስት ተያይዘዋል፡፡

### የሰው ኃይል

25. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር (የከተማ ልማት ዘርፍ) 795 ቋሚ ሠራተኞች በመዋቅር የጸደቀለት ሲሆን እስከ ታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም ድረስ 488

(61.4%) ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ፕሮፌሽናል የሆኑ ወንድ 246 ሴት 99 ድምር 345 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ ወንድ 69 ሴት 74 በድምሩ 143 በጠቅላላ ወንድ *315* እና ሴት 173 በድምር 488 ሰራተኞች አሉት፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

26. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር (የከተማ ልማት ዘርፍ) በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ 2007 እስከ ታህሳስ 30 2011 ድረስ የተመደበለትን የካፒታል እና መደበኛ በጀት እንዲሁም የወጣውን ወጪ በሚከተሉት ሰንጠረዦች ላይ ተመልክቷል፡፡

27. ከ2007 እስከ ታህሳስ 30 2011 ዓ.ም ድረስ ከመንግስት የተመደበለት በጀት እና የወጣው ወጪ፡-

| በጀት ዓመት | የተፈቀደው በጀት | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 707,243,608.59 | 631,580,177.59 | (89.30%) |
| 2008 | 1,168,044,831.55 | 868,885,564.86 | (74.39%) |
| 2009 | 1,026,226,684.65 | 659,083,646.62 | (64.22%) |
| 2010 | 1,243,544,750.24 | 743,542,350.96 | (59.79%) |
| 2011 | 1,449,683,070.00 | | |

**ሰንጠረዥ አንድ- ፡የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከ2007 እስከ ታህሳስ 30 2011 ዓ.ም ድረስ የተመደበው በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ**

28. ለ ULGDP II ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የተመደበው በጀት እና የወጣው ወጪ

| በጀት ዓመት | የተፈቀደው በጀት | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 5,088,279,386.92 | 4,281,109,307.32 | 84% |
| 2008 | 5,568,761,153.70 | 4,873,595,330.54 | 88% |
| 2009 | 6,837,045,210.92 | 5,617,561,943.97 | 82% |
| 2010 | 6,931,981,950.28 | 5,477,381,877.13 | 79% |
| 2011 | 7,327,575,267.33 | 946,220,595.69 (እስከ ታህሳስ 30/2011) | 13% |

## ሰንጠረዥ2- የULGDP II ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከ2007 እስከ ታህሳስ 30/2011 ዓመት የተመደበው በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ

### የኦዲቱ ዓላማ

29. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ትግበራና አፈጻጸም ቀልጣፋ፣ ውጤታማና እና ስኬታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

30. በዚህ የኦዲት ውጤት የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ለተጠቀሱት ፕሮጀክቶች የተሻለ አፈፃጸም ለማስገኘት ከመርዳቱም በላይ ፕሮጀክቶቹን ለሚቆጣጠረው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ የገቢ ማሻሻያ ፈንድ ሞቢሊቲ እና ፋይናንስ ቢሮ ወደፊት በሚያከናውናቸው የከተሞች የአቅም ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው፡፡

### የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

31. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) የከተሞች የመሰረተ ልማት ግንባታ ትግበራና አፈፃፀም ውጤታማ፣ ስኬታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም ነው፡፡

### የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issues)

32. በተመረጡ የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና ሶስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም:-

    1. የከተሞች የመሰረተ-ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የእቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መደረጋቸውን መገምገም፣

        1.1. የመሰረተ-ልማቱ እንዲፋጠን የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ፣ ጨረታዎችና ግዥዎች ግልፅ እና በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳና በጀት ውስጥ የተከናወኑ መሆኑን መገምገም፣

1.2.የከተሞች የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳና በጀት መፈፀማቸውን መገምገም፣

1.3.በፕሮጀክቶቹ የሚደረገው የአካባቢያዊና ማህበረሰብ የተፅዕኖ ግምገማ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈፀሙን መገምገም፣

2. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞችን የመሰረተ ልማት-ማስፋፊያ ፕሮግም ትግበራና አፈጻፀምን በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

33. ከላይ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና ሦስት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 40 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criterias) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚ/ር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ እና አፈጻጸሞች፣ እንዲሁም ፕሮግራም ኦፕሬሽናል ማኑዋል ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተልከው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ አንድ ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

34. ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉና በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2001 እስከ 2011 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ሆኖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር ባለው የከተማ የገቢ ማሻሻያ ፈንድ ሞቢሊቲ እና ፋይናንስ ቢሮና በናሙና በተመረጡ 6 ከተሞች ባሉ የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ነው፡፡

35. ዝርዝር የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሲሆን፣ በተጨማሪም በናሙና በተመረጡት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አዳማና ባቱ ከተሞች፣ በአማራ ክልል በሚገኙ ባህርዳርና ደብረ ታቦር ከተሞች እና

በደቡብ ህዝቦች ብሄሮችና ብሄረሰቦች ክልል ሃዋሳ እና ዲላ ከተሞች በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ከተሞች የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች  በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 ዕቅድና በጀትን በተመለከተ (Planning and Budgeting)

### የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ (CIP) መዘጋጀቱን በተመለከተ፣

36. የከተማ አስተዳደሮቹ የ3 ዓመት የመሰረተ-ልማት እቅድ (*Capital Investment Plan*) ከትግበራ እቅድ ጋር አያይዘው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትል እና ሲአይፒ በወቅቱ እንዲላክ ለማፍጠን በተላለፈ ደብዳቤ ላይ በተቀመጠው ጊዜ መሠረት ሊያዘጋጁና የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ በሚተገበርበት በጀት ዓመት ውስጥ የከተማ ምክር ቤቱም ሊያፀድቅና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሊልኩ ይገባል፡፡

37. ከተሞች የመሠረተ ልማት ዕቅድ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 24 እ.ኤ.አ ሊያዘጋጁና በምክር ቤታቸው በማጸደቅ እንዲሁም የተከለሰው ዕቅድ እስከ የካቲት 6 እ.ኤ.አ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መቅረብ ቢኖርበትም በናሙና ባየናቸው ከተሞች የ2007፣ 2008፣ 2009 እና በ2010 ዓ.ም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተዘጋጅቶ የማያቀርቡ ከተሞች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ለማሳያ በ2007፣ 2008፣ 2009 እና 2010 ዓ.ም በወቅቱ የመሰረተ ልማት ዕቅዱን ያላዘጋጁ ከተሞች፡-

- በወቅቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን ያላዘጋጁ ከተሞች በ2007 12፣ በ2008 9፣ በ2009 12 እና በ2010 ዓ.ም 12 ከተሞች ሲሆኑ
- እንዲሁም የተከለሰውን የመሠረተ ልማት ዕቅዱን በወቅቱ ያላቀረቡ ከተሞች ደግሞ በ2007 16፣ በ2008 7፣ በ2009 16 እና በ2010 ዓ.ም 12 ከተሞች ናቸው
- በ2008 ዓ.ም ሁለት ከተሞች ጋምቤላና ሐረር በጀት ዓመቱ ካለፈ በኋላ ዕቅድ ያቀረቡ ናቸው፡፡

ዝርዝሩ በአባሪ አራት ላይ ተያይዟል፡፡

38. እንዲሁም የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅድ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ እንደማይዘጋጅ ማለትም ከዓመታዊ ትግበራ ዕቅዱ፣ ከበጀቱና ከግዢ ዕቅዱ ጋር ተጣጥሞ የማይዘጋጅ እንደሆነ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በናሙና ከታዩ

ከተሞች ካየናቸው የመሠረተ ልማት ግንባታ እቅዶች እና ከከተሞቹ ኃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር መሠረታዊና ትክክለኛ ጥያቄ እንደሆነና በወቅቱ ላለመዘጋጀቱ ዋናው ምክንያት የመሠረተ ልማቱ እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት ማሻሻያ በመምጣቱ ምክንያት እንደሆነና በዚህም ምክንያት እንደገና ጨረታ ለማውጣት እንደተገደዱ፣ በየደረጃው ማለትም ከቀበሌ እና ከካቢኔው ፀድቆ ሲመጣም በርካታ ጊዜ ሊወስድ ስለቻለ እንደሆነና ዲዛይንና ሌሎች ተጓዳኝ ነገሮች የሚሰሩት ከከተማው ምክር ቤት ፀድቆ ሲመጣ ስለሆነ ይህም ሰፊ ጊዜ ስለወሰደ የመሠረተ ልማት ዕቅዱ ዘግይቶ ሊዘጋጅና ሊላክ እንደቻለ፣
- የባህር ዳር ከተማ ምክትል ከንቲባ፣ ፕሮጀክት ኢንጂነር እና ምክትል ስራ አስኪያጅ የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅድ በበቂ መረጃ እና እውቀት አለመዘጋጀቱን ገልፀው ምክንያቱም የመሠረተ ልማት ዕቅዱ ከተለያዩ ሴክተሮች የሚመጣ ሰለሆነ ከነዚህ አካባቢዎች የሚመጣው መረጃ የተለያየ ስለሆነ በጥራት እንዳይሰራ የሚያደርገው መሆኑ፣ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች በየጊዜው ሰለሚለቁ ክፍተት የፈጠረባቸው መሆኑን፣ የመንግስት፣ የአስተዳደሩና የህብረተሰቡ ፍላጎትና አቅም የተጣጣመ አለመሆን ሲሆን ሌላው የኢንጂነሪንግ ኢስቲሜሽን ችግር መኖሩ፣ ቴክኒካል በሆኑ ነገሮች ላይ የእውቀት ችግር እንደነበረ ገልፀዋል፡፡
- የባቱ ከተማ ስራ አስኪያጅና ፕሮጀክት ኢንጂነር ዋናው ችግር የባለሙያ እጥረት እንደሆነ፣ ሌላው በቂ የስራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ስለሌሉ እንደሆነና አንዳንዶቹ ልምድ በሌላቸው ባለሙያዎች ስለተሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

40. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋና ዋና ምክንያቶች አንደኛው የከተሞች ካፒታል ኢንቨስትመንት በወቅቱ የማያፀድቁበት ምክንያት ምክር ቤቱ በወቅቱ በጀት ስለማያፀድቅ እንደሆነ፣ ሁለተኛው የክህሎት ክፍተት በመኖሩ ምክንያት እንደሆነና ጥሩ እውቀት ያላቸው ሰራተኞች ስለሚለቁ እንደሆነ፣

ሌላው አዳዲሶቹ ከተሞች ለፕሮግራሙ አዲስ በመሆናቸው ፕሮግራሙን በቀላሉ ያለመረዳት ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

41. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የኦዲት ግኝቱ ትክክል እንደሆነና በዚሁ መሠረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስለሆነ በዚህ ወቅት የከተማ ምክር ቤት ጉባኤ ዘግይቶ መሰብሰብ ምክንያት በጀት እና የመሠረተ ልማት ዕቅድ በወቅቱ ባለማጠናቀቃቸው ከዝግጅት ምዕራፍ የወጡ እንደሆነና ኦዲት ግኝቱ ትክክል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

42. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ

- ፕሮግራሙ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ የመንግስትን የበጀት ዕቅድ ዑደቱን ተከትሎ ሲሰራ የነበረና በዚህም መሰረት የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ እ.ኤ.አ ሐምሌ 24 በየዓመቱ መፅደቅ እንዳለበት ነገር ግን ከገለልተኛ ዓመታዊ አፈፃፀም ገምጋሚ አማካሪ መረጣ ጋር ተያይዞ የግዥ ሂደቱ በመዘግየቱ ምክንያት የበጀት ድልድልና የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ ዝግጅት ጊዜ ጋር ሳይጣጣም እንደቆየ፣
- ስለሆነም የዓመታዊ አፈፃፀም ግምገማው በመዘግየቱ የበጀት ድልድሉን በማዘግየት በክልል ደረጃ የበጀት ጣሪያ በሰኔ ወር ለከተሞች ማሳወቅ እንዳልተቻለ፣
- ይህ ሁኔታ ደግሞ ከተሞች የበጀት ዕቅድ ዑደቱን ተከትለው ዕቅዳቸውን እንዳያጠናቅቁ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ በመቆየቱ የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ ዝግጅት ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ ወደፊት መገፋቱና የክለሳውም ጊዜም መዘግየቱ ከላይ ከእቅድ ዝግጅት መዘግየት ጋር ተያይዞ መሆን ከነበረበት ከጥር ወር መጨረሻ ወደ ግንቦትና ሰኔ ወራት መገፋቱ ተገቢ አስተያየት እንደሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ በተለይም ከልማት አጋሩ ከዓለም ባንክ ጋር በመወያየት በMulti year contract በመጠቀም የ2010 በጀት ዓመት ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማው በጊዜ ተጀምሮ በመካሄድ ላይ እንደሚገኝ
- በተጨማሪም የመሰረተ ልማት እቅድ የሚያካትተው ሁሉንም በከተማው የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን ሲሆን ከክልሎችና ከዞኖች ለከተሞቹ የሚገባቸውን ድጎማ በወቅቱ ባለማሳወቅ ወይም ክልል ምክር ቤት በወቅቱ ተሰብስቦ በጀት ያለማፅደቅ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን በወቅቱ ማጠናቀቅ አለመቻል፣

- የከተሞች አመራር በወቅቱ የመሠረተ ልማት እቅድ ዝግጅትን አለመደገፍ እና አለማፅደቅ እንዲሁም የከተማው ምክር ቤት የተዘጋጀውን የመሠረተ ልማት እቅድን በወቅቱ ተሰብስቦ በቃለ ጉባኤ አለማፅደቅ የሚጠቀሱ እንደሆነና ጋምቤላና ሐረር ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቀሱ እንደሆነ

ገልፀዋል፡፡

43. የመሠረተ ልማት ግንባታ እቅድ በወቅቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለመቅረቡና ባለመፅደቁ ምክንያት ከተሞቹ ማግኘት የሚገባቸውን ነጥብና ገንዘብ ሊያሳጣቸው እንደቻለ እንዲሁም በርካታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይጀመሩና እንዳይጠናቀቁ እንዲሁም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዳይሰሩ እንዳደረገ እንዲሁም የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅድ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ አለመዘጋጀቱ ፕሮጀክቶች በቅደም ተከተላቸው እንዳይሰሩ፣ የመሰረተ ልማት እቅዱ (Capital Investment Plan) በተደጋጋሚ ጊዜ እንዲስተካከል በመደረጉ በተዋረድ ባሉ ምክር ቤቶችና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ እንዳይፀድቅ ከማድረጉም በላይ የግንባታ ፕሮጀክቶች የመሠረተ ልማት እቅዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጀመሩና እንዳይጠናቀቁ አድርጓል፡፡

## 2.2 የመሠረተ ልማት አውታሮች አስተዳደርን በተመለከተ (Asset Management)

**ለጥገና የሚወጣው በጀት እና አፈጻጸሙ ከእቅዱ ከ80 ፐርሰንት አለማነሱን በተመለከተ፣**

44. የከተማ አስተዳደሩ ለጥገና (መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች፣ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች፣ የገበያ ቦታዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ወዘተ) የሚወጣውን በጀት ሊያዘጋጅና አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 በመቶ ማነስ የሌለበት ሊሆን ይገባል፡፡

45. ሆኖም ሁሉም በፕሮጀክቱ ሥር የታቀፉ ከተሞች

- ለፕሮጀክት ጥገና ትኩረት ሰጥተው አለመስራት፣
- በአዳዲስ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ላይ ማተኮርና ጥገና ለሚደረግላቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ትንሽ ትኩረት የመስጠት ነገር መኖርና
- የሚፈለገውን የጥገና በጀት አለመመደብ እንዲሁም

- ለጥገና የሚወጣው በጀት አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 በመቶ ማነስ የሌለበት ሊሆን እንደሚገባ በፕሮግራም ኦፕሬሽን ማኑዋሉ ላይ ቢቀመጥም ከተጠቀሰው በታች አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች መኖራቸውም

ታውቋል፡፡

46. ከሁሉም ከተሞች የአሰላ ከተማ ከ2008 እስከ 2010 ድረስ ባሉት ሶስት በጀት አመታት በተከታታይ አፈጻጸሙ ከ80 ከመቶ በታች ነበር፡፡ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች ዝርዝር በአባሪ 5 ተያይዟል፡፡

47. እንዲሁም በከተሞቹ በርካታ የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥገና የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ አሳሳቢና አንገብጋቢ የሆኑትን ለይቶ ቅድሚያ በመስጠት ለመጠገን የሚያደርጉት ጥረት አናሳ እንደሆነና ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በከተሞቹ የሚያዘው የጥገና እጥረት (Maintenance Deficit) ከፍተኛ እንደሆነ ለማሳያ፡- በናና ከተመለከትናቸው ከተሞች

✓ **በ2007 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | Maintainance Deficit | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ደብረ ታቦር | 3,177,953.84 | 808,057.28 | 25% |
| 2. | ባህር ዳር | 27,986,638.00 | 16,870,079.92 | 60% |
| 3. | አዳማ | 238,033,967.50 | 14,529,900.42 | 6% |

✓ **በ2008 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | Maintainance Deficit | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ደብረ ታቦር | 29,740,864 | 5,625,000.00 | 19% |
| 2. | ባህር ዳር | 107,050,840 | 9,672,554.00 | 9% |
| 3. | አዳማ | 287,380,236 | 34,427,534.19 | 12% |

✓ **በ2009 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | Maintainance Deficit | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ደብረ ታቦር | 109,391,461.00 | 8,463,372.79 | 8% |
| 2. | ባህር ዳር | 114,455,677.00 | 34,339,810.00 | 30% |
| 3. | አዳማ | 77,407,601.00 | 37,251,380.37 | 48% |

✓ በ2010 ዓ.ም

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | Maintainance Deficit | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ደብረ ታቦር | 28,500,000.00 | 8,500,000.00 | 30% |
| 2. | ባህር ዳር | 83,998,323.80 | 21,241,345.85 | 25% |
| 3. | አዳማ | 77,407,601.00 | 55,806,500.77 | 72% |

እንደሆነ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና በናሙና ለተመረጡ ከተሞች ኃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

48. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ:-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ችግሩ የሚመነጨው ከ Poor Plannning የመጣ ችግር እንደሆነ፣ በደንብ በጥናት ላይ እና በጥልቀት ተመስርቶ የማቀድ ችግር እንደሆነና ሌላው የበጀት ችግር ያመጣው ችግር እንደሆነ ይሄ ደግሞ ለጥገና በጀት የያዝነውን በጀት ሙሉ በሙሉ ካልተጠቀምንበት ብዙ ነጥብ ያሳጣና ብዙ ብር ወደ ማጣት የሚያደርስ እንደሆነ፣
- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር እና ምክትል ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሥራው የሚካሄደው በግምት መሆኑ ያመጣው ችግር እንደሆነና እንዲሁም ዕቅዱ ሲዘጋጅ በደንብ ፕላን ያለማረግና በርካታ ነገሮች ተጠንቶ ስለማይሰራ ያመጣው ችግር እንደሆነ፣

ገልፀዋል፡፡

49. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በመርህ ደረጃ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆን የመሠረተ ልማት ዕቅዱ ላይ ከተያዘው በጀት 10 ፐርሰንት የሚሆነው ለጥገና ይውላል የሚል ቢሆንም ነገር ግን ይህ ችግር የሚፈጠረው በየከተማው ያለው አመራር ለጥገና ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት ችግር እና የቁርጠኝነት ችግር ነው ይህ ችግር በ2010 ዓመተ ምህረትም ቀጥሏል እንዲሁም ለጥገና ምን ያህል ወጪ ያስፈልጋል እና የት የት ያሉ ቦታዎች ጥገና ያስፈልጋቸዋል የሚለውን ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት ችግር ያመጣው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

50. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት፡-

- ከተሞች ከተቆረቆሩበት ጊዜ አንስቶ ለብዙ ዓመታት የመሠረተ ልማት ሃብታቸው ሳይጠገን የቆየ በመሆኑ የጥገና ውዝፍ (Maintainanace Backlog) እንዳለባቸው፣
- የመሰረተ ልማት ሀብት አስተዳደር ዕቅድ ሲዘጋጅ ጥናቱ ከተሞቹ ከተቋቋሙበት ጊዜ አንስቶ ያላቸውን ነባርና አዲስ ሃብት እርጅናቸውንና እጥረታቸውን ስለሚዳስስ ወደ ኋላ ይሄድና እስከ ዛሬ ድረስ ለዓመታት ያልተካሄደውን ጥገና እንደሚያመለክት፣ ይህም የጥገናውን ዕጥረት /Maintainance Deficit/ ከፍ እንዲል የሚያደርግ መሆኑ፣
- ከተሞች ማድረግ ያለባቸው በየዓመቱ በጥናት ላይ የተመሠረተ የመሠረተ ልማት ጥገና በጀት መያዝና ውዝፍ ጥገናው እስከሚያልቅ ድረስ እየጠገኑ መሄድ እንዳለባቸው፣ ለዚህም ከተሞች የመሰረተ ልማት ግንባታ ዕቅዳቸውን (ሲአይፒ) 10% ወይም የአጠቃላይ የከተማውን ሃብት 2% ለጥገና በጀት በየዓመቱ በእቅድ እንዲይዙ እየተደረገ እንደሚገኝ
- በተጨማሪም ከተሞች ከMaintainance Deficit ላይ አንገብጋቢ የሆኑ ጥገናዎችን ቅድሚያ በመስጠት እየጠገኑ እንደሆነ፣

ገልፀዋል፡፡

51. በተጨማሪም ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሃላፊዎች ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ፡-

- የመሰረተ ልማት ጥገናን በተመለከተ በከተሞች ከሚታዩት ዋና ዋና ችግሮች መካከል አንዱ የመሠረተ ልማት አለመስፋፋትና ተያያዥ አገልግሎቶች አለመሟላት እንደሆነ፣ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የፋይናንስ እጥረት እንደሆነ፣
- ከዚህም የተነሳ በአብዛኛው የከተሞች ትኩረት የነበረው በከተሞች የሚታየውን የመሠረተ ልማት ፍላጎት መሟላት እንደነበር፣ ይሁንና በመሠረተ ልማት አሴት ሥራ አመራር ማኑዋል መሰረት ከተሞች ለጥገና ከካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ 10 በመቶ ወይንም ከመሰረተ ልማት መተኪያ ወጪ 2 በመቶ ከሁለቱ የሚያንሰውን በመውሰድ ለረጅም ዓመታት የቆየውን የጥገና ችግር ለመቅረፍ እንደሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ በመሠረት ላይ እንደሚገኝ፣

- ነገር ግን በከተሞቹ የሚያዘው የጥገና በሁለት ምክንያቶች ከተሞች ለጥገና ትኩረት ያልሠጡ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንደሚታዩ እንዚህም ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመሰረተ ልማት ጥገና የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጪ ከአሴት ስራ አመራር እቅድ በተገኘ መረጃ በእቅዳቸው አካተተው እንዲሰሩ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣
- ይሁንና ለጥገና የሚያስፈልገው ወጪ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በረጅም ጊዜ ዕቅድ የሚፈታ ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንደሚገኝ

ገልፀዋል፡፡

52. በርካታ መጠገን ያለባቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች በዕቅድ እየተያዙ በወቅቱና በአፋጣኝ አለመጠገናቸው በከተሞቹ የሚገኙት የመሰረተ ልማት አውታሮች ለበለጠ ጉዳት እንዲዳረጉ ከማድረጉም በላይ አዲስ ለሚገነቡትም እንክብካቤ ማድረግን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## 2.3 የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ (Financial Management)

### ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት መካሄዱን በተመለከተ፣

53. በፕሮግራሙ የሚገነቡ ሁሉም የመሰረተ ልማት ግንባታ ትላልቅ ፕሮጀክቶች (ቄራ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ አስፋልት መንገድና ትልልቅ የገበያ ማዕከላት ግንባታ) የአዋጭነት ጥናት ሊካሄድላቸው እንዲሁም ከተጠኑ የቆዩ የሆኑ ፕሮጀክቶችንም ወቅታዊ ሊደረጉ እና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

54. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት

- ✓ በባህርዳር ከተማ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታ የአዋጭነት ጥናቱ የተካሄደው በመጋቢት 2005 (2013 እ.ኤ.አ) ቢሆንም ወደ ስራ ሳይገባ 5 ዓመታት ያለፈ መሆኑና አሁን ሌላ ጥናት ሊካሄድለት መሆኑ፣
- ✓ በአዳማ፣ በባቱ እና አርባ ምንጭ ከተሞች ለትልልቅ ፕሮጀክቶች (ትልቅ የገበያ ማዕከላት፣ ቄራ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ የጠጠር መንገድ) የአዋጭነት ጥናት ሳይካሄድላቸው ወደ ትግበራ የተኬደ መሆኑን፣

ከተከለሱ ሰነዶችና ከከተሞቹ ኃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንደኛ የአዋጭነት ጥናት ይሄን ያህል አስፈላጊ ነው ብለው ስላላሰቡ ጥናቱን ያልተካሄደ እንደሆነ፣ ሌላው ጥናቱን ለማካሄድ የሰው ሃይል እጥረት ስላለ እንደሆነና አቅም እንደ ከተማም እንደ ሃገርም አናሳ ስለሆነ ጥናቱን እንዳላካሄዱ የአዋጭነት ጥናት ለማካሄድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጊዜ እንደሚያስፈልግና በዚህም ምክንያት የመሠረተ ልማቶቹ አዋጭነት ሊታወቅ እንዳይችል እንደሚያደርገው፣
- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነርና ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶለት ነበር በመጋቢት 2013 እ.ኤ.አ ሆኖም ወደ ስራ ባለመግባቱና ጥናቱ ሁለት ዓመት ስላለፈው እንደገና ይጠና ስለተባለና በተለያየ ምክንያት ወደ ስራ ሊገባ እንዳልቻለ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የFukaka Solid Waste Management Practice የሚባል ሞዴል የሆነ አሠራር ስላመጣ ቀድሞ የተጠናው ይዘግይ ስለተባለ እንደሆነ፣
- የባቱ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከ2009 ዓ.ም በፊት ስለአዋጭነት ጥናት ግንዛቤ ስላልነበረን እንዲሁም ጥናቱን የሚሰራ ባለሙያም እጥረት ስለነበረ የአዋጭነት ጥናት አልተሰራም ከዛ በኋላ ግን ጥናቱ እየተሰራ እንደሆነ

ገልጸዋል፡፡

56. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የባህር ዳር ጥናቱን ሊሰራው የነበረው አካል የበጀት እጥረት ስለገጠመው እንደሆነ ሆኖም የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ ወሳኝ እንደሆነና በሌሎች ከተሞች ከተሞቹ ባሉባቸው አካባቢዎች አቅራቢያ ባሉ ዩንቨርሰቲዎች ከከተሞቹ ጋር በመቀናጀት የአዋጭነት ጥናት ማዘጋጀት ይገባቸው እንደነበረና ሆኖም ክፍተቶች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

57. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት በባህር ዳር የተጠናው ጥናት የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ግኝቶችን ያካተተ እንዲሆን በUN HABITAT በኩል ጊዜ ተወስዶ ዲዛይን/ጥናቱ ክለሳ ሲደረግለት እንደነበር፣ በአዳማ

በጀርመን ልማት ባንክ የተሠራውን የቄራ ፕሮጀክት እና በአርባ ምንጭ ያለውን የገበያ ማዕከል ጊዜ ወስዶ ማረጋገጥ እንደሚጠይቅ ገልፀዋል፡፡

58. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ የአዋጭነት ጥናት መካሄዱ አከራካሪ ጉዳይ እንዳልሆነና ጥናቱ ተካሄዶ መደርደሪያ ላይ (On shelf) መቀመጥ እንዳለበትና ወደ ፊት በተሰጠው አስተያየት መሠረት ለመተግበር እንደሚሞከር ገልፀዋል።

59. በባህር ዳር ከተማ ኃላፊዎች፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቢሮ ኃላፊ እና ለነባራዊ ሁኔታ በተሰጠው መልስ የተገለፁት ምክንያቶች የተለያዩና በማስረጃ የተደገፉ ባለመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

60. የመሰረተ ልማት ግንባታ ትላልቅ ፕሮጀክቶች (ቄራ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ አስፋልት መንገድና ትልልቅ የገበያ ማዕከላት ግንባታ) የአዋጭነት ጥናት ካልተካሄደላቸው የፕሮጀክቶቹ ትክክለኛ ወጪ እንዳይታወቅ፣ የሚያስገኙት ጥቅም ሆነ የሚያስከትሉት ጉዳትን በቅድሚያ ካልታወቀ ተጨማሪ ወጪ ሊያስወጡና በቅድሚያ ያልታየ የህዝብ ሮሮ ሊነሳባቸው ይችላል፡፡

**የሚዘጋጁ የግንባታ ግብዓቶች መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) ዝግጅትን በተመለከተ፣**

61. ለሚከናወኑ ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ግብአቶች መጠን (Bill of Quantity) ከተሞቹ ሲያዘጋጁ የተሟላ ሁሉንም ዋና ዋና ስራዎች የያዘ፣ ትክክለኛ የሆነና ሁሉንም በተቋራጮቹ የሚሰራውን ሥራ ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ

- ✓ በባህር ዳር ከተማ በ2007 ዓ.ም ከተጀመሩት ውስጥ የቄራ ማዘጋጃ ሲገነባ እንዲገነባ ከታሰበው ውጭ የማይሰሩ ሥራዎች (ለምሳሌ The BoQ of Abbatior of Christian pre slaughter contain (super structure) metal work, PVC work, Glazing፣ Lia Rage Muslims super structure contain metal work, Pre slaughter Muslims super structure contain metal work, Pig Lia Rage and Pre slaughter of super structure contain metal work and PVC work (ቢል ኦፍ ኩዋንቲቲ) የተካተተ መሆኑና በዚህም ምክንያት ለቄራው የተመደበው በጀት ከፍ እንዲል በማድረግ

ለሌሎች ፕሮጀክቶች የሚውል የነበረ አላስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ በጀት እንዲያዝ ያደረገ መሆኑ፣

- ✓ በተጨማሪም በ2009 ዓ.ም በባህዳር ከተማ ከተሰሩ ፕሮጀክት መካከል the BoQ of the drainage project lacks mass concrete work፣ the BoQ of the street light project did not contain concrete class of pole pads ጥናቱ ላይ በስህተት ሳይካተቱ የነበረ መሆኑ፣
- ✓ በደብረ ታቦር ከተማ በ2009 ዓ.ም ከተሰሩ ፕሮጀክት መካከል ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የተሰሩ ሼዶች ሲገነቡ (የተቆፈሩ አፈር አወጋገድን እና የሚሰሩ ቦዮች ልኬት (the BoQs of SME shed project lacks cart away distance for the excavated soil እና the BoQs of open drainage construction project lacks unit of measurement for trench excavation and for back fill around masonry works) ጥናቱ ላይ ያልተካተቱ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና በናሙና በተመረጡ የከተማ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ቢል ኦፍ ኩዋንቲቲ ሲዘጋጅ በጥናቱ ውስጥ ያልተካተቱ miss የተደረጉ ነገሮች ስለነበሩ ችግሮቹ ሊፈጠሩ እንደቻሉ፣
- የደብረ ታቦር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሚሰሩት እያንዳንዱ ስራዎች በቢል ኦፍ ኩዋንቲቲ መሠረት እያንዳንዱ ሥራ ተገምግሞና ሥራዎቹ ግልፅ በሆነና ሁሉንም መረጃዎች ባካተተ መልኩ ለሁሉም ተጫራቾች በሚገባ መልኩ ስላልተቀመጠ ያጋጠመ ችግር እንደሆነ፣
- የባቱ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ይህ ችግር የተፈጠረው ፐብሊክ ኮንሰልቴሽን ያልተካሄደ እንደነበርና በዚህ ምክንያት ከህብረተሰቡ በጣም ብዙ ቅሬታ ስለተነሳብን ዲዛይኑ በሚቀየርበት ጊዜ ይህ ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ፣

ገልፀዋል፡፡

64. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ የባህር ዳር ቄራን በተመለከተ ይህ ITEM መጀመሪያ በዲዛይን ውስጥ የነበረ ሲሆንና ቢል ኦፍ ኲዋንቲቲ ውስጥም የተካተተው በዚሁ መሠረት እንደሆነና በስህተትም ያልተካተተ መሆኑ የተያዘውም በጀት በ Addition and Omission የተስተካከለ እንደሆነ፣ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ የተነሱት ግኝቶች ጊዜ ወስዶ ማረጋገጥ ስለሚስፈልግ ኮሚቴ በማዋቀር ተጠርቶ ምላሽ እንደሚሰጥበት ገልፀዋል፡፡

65. ከተሞቹ የሚያዘጋጃቸው ቢል ኦፍ ኳንቲቲ (Bill of Quantity) የተሟላ እና ትክክለኛ የሆነና በተቋራጮቹ የሚሰራው ስራ ሁሉንም ዋና ዋና ስራዎች ያላካተተ ከሆነ ለሌሎች ፕሮጀክቶች የሚውል የነበረ አላስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ በጀት እንዲያዝ ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**ከተሞች ለሚያሰሯቸው ፕሮጀክቶች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ መክፈላቸውን በተመለከተ፣**

66. ከተሞቹ ለሚያሰሯቸው እያንዳንዱ ፕሮጀክቶች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ ሊከፍሉ አይገባም፡፡

67. ሆኖም መሰረተ ልማቶች ለመገንባት የተዘጋጀው የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ (Capital Investment Plan (CIP)) ላይ የተያዘው በጀትና በኮንትራት ውሉ ላይ የተቀመጠው ዋጋ መካከል ልዩነቶች እንዳሉ ለማሳያ፡-

| ተ.ቁ | ከተማው እና አካባቢው | CIP ላይ የተያዘው በጀት | ኮንትራት ውሉ የተፈረመው | ልዩነት በመብለጥ /በማነስ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በባህር ዳር በ2007 ዓ.ም ከተሰሩት | | | |
| | ▪ የቄራ ማዘጋጃ ግንባታ ለመስራት | 84,000,000 | 119,576,634.80 | 35,576,634 (42%) |
| | ▪ ሚሊኒየም ግሪነሪ ፕሮጀክት ለመስራት | 4,000,000 | 2,904,875.62 | (1,095,124.38) |
| | ▪ Old Dipo to SOS Village & Alkal Aspalt to SOS School ለመስራት | 46,000,000 | 102,525,003.13 | 56,525,003.13 (123%) |
| 2 | በሐዋሳ በ2009 ዓ.ም | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ከተሰሩት | | | |
| | ▪ Cobblestone Road from Don Dental to Tabor M/Y/Church ለመስራት | 2,071,771 | 3,942,900.93 | 1,871,129.93 (90%) |
| | ▪ Cobblestone Road from Sodo Residence to Engida Residence ለመስራት | 2,354,286 | 3,533,508.06 | 1,179,222.06 (50%) |
| 3 | በሐዋሳ በ2008 ዓ.ም ከተሰሩት | | | |
| | ▪ የኮብል ስቶን መንገድ ግንባታ ከሃይሉ ጆቴ በውድነህ አድርጎ እስከ እድር ሜዳ ለመስራት | 941,714 | 3,973,035.30 | 3,031,321.30 (322%) |
| | ▪ የኮብል ስቶን መንገድ ግንባታ ከሻምበል በላይ መኖሪያ እስከ ተክሌ ስጋ ቤት ከሙሉጌታ እስከ አትክልት ግሮሰሪ ከጥቃቅንና አነስተኛ ሱቆች እስከ ቤዛ ለመስራት | 1,765,714 | 3,198,652.35 | 1,432,938.35 (81%) |

እንደሆነ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፕሮጀክቱ አዲስ ስለነበር ኮንሰልታንቱ ለፕሮጀክቱ ያለዉ እዉቀት አናሳ መሆን ያመጣው እንደሆነ፣ የግሪነሪዉ ፕሮጀክት ደግሞ የውስጠኛውን የስነ ምድር (Geological strata) መጠናት ስለነበረበትና በወቅቱ ያልተጠና በመሆኑ ሲሆን ሌላዉ ደግሞ የእቅድ ድክመት ስለነበረ በመሆኑ ምክንያት የመጣ እንደሆነ፣

- የዲላ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2009 ዓ.ም እቅዱ የተሰራው በሌላ አካል ነበር እናም ኮስት ብሬክዳውን ሳይሰራ ወይም ግምት ውስጥ ሳይገቡ ነበር እቅዱ የወጣው ከዛ ትክክለኛው ዋጋ ጋር ሲገናኝ በጣም ልዩነት መፍጠሩን፣ ሌላው ፕላኑ ላይ የነበረ ችግር መሆኑ ማለትም በትክክል የማቀድ ችግር ስለነበረ መሆኑና የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት ሳያደርግ እቅዱ መዘጋጀቱ ችግር የፈጠረባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በ2007 ዓ.ም 1 ፕሮጀክት ልዩነት ፈጥሮብናል ምክንያቱም ፕሮጀክቱ የእግረኛ መንገድ ስለነበረው ዲች እንዲሰራ አልተፈቀደም እንደነበር በኋላ ግን ዲች እንዲካተት መደረጉ የዋጋ ጭማሪ እንዲያጋጥም እንዳደረገ፣
- የሀዋሳ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጅነር ተጨማሪ ስራዎች ሊያስፈልጉ የሚችሉ መሆኑ ለምሳሌ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የግድ ክዳን መሰራት እንዳለበት ስናቅ ክዳን እንዲሰራ ያደረግንበት ሁኔታ እንዳለ ምክንያቱም ክዳን ባለመሰራቱም ብዙ ችግሮች እንዳጋጠመና ሰዎችም በጎርፍ አደጋ የሞቱበት ሁኔታ እንዳለ ስለዚህ የግድ ተጨማሪ ስራ መሰራት ስለነበረበት ከእቅዱ በላይ ገንዘብ ሊወጣ እንደቻለ፣

ገልፀዋል፡፡

69. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በተለያየ ምክንያት የዋጋ መቀነስና መጨመር በተለይም ደግሞ በዶላር ምንዛሬ መጨመር ምክንያት የሚመጣ ችግር፣ ኮንትራክተሮች ተጨማሪ ሥራዎችን መስራትና ተጨማሪ ክፍያ ስለሚጠይቁ እንደሆነ እንዲሁም የጥሬ እቃ ዋጋ መጨመር ስለሚያጋጥም የዋጋ ልዩነቶች የሚፈጥሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

70. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት በባህር ዳር ከተማ በ2007 ዓ.ም የቄራ ማዘጋጃ ግንባታ ለመስራት ብር 84,000,000 ተብሎ አስተያየት የተሰጠበት አሃዝ ዋጋ በከተማው 2007-2010 ሲአይፒ ሰነድ ላይ ብር 99,271,085 እንደሆነና ይህ የተጠቀሰው ዋጋ መጠን የቅድመ ዋጋ ግምት (Rough Estimation) እንደሆነ፣ ነገር ግን Detail Design ሲሰራ ከተያዘው በጀት ሊያልፍ

እንደሚችል ስለሆነም በጨረታ ውድድር አነስተኛው የጨረታ ዋጋ የነበረው ብር 119,576,634.80 እንደሆነና ውል የተገባበበት ዋጋ በIBEX ውስጥ የተስተካከለ በጀት ተብሎ እንደሚመዘገብ፣ በተመሳሳይ Old Dipo to SOS Village & Alkal Aspalt to SOS School ለመስራት ከላይ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ቢታይ፣ በአመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ጋይድላይን (APAG) መሰረት የሲአይፒ ወይም የግዢ ዕቅድ በጀት እና በውል ዋጋ ልዩነቱ እስከ 20% ሊሆን እንደሚችል እንደሚጠቅስ በዲላ ከተማ የተጠቀሰው በዚህ ቢወሰድ፣ በሃዋሳ ከተማ ላይ የተጠቀሱትን ልዩነቶች ለማጣራት ጊዜ እንደሚያስፈልግና ዝርዝር አፈጻጸሙን ከተሞች ላይ በመውረድ በማረጋገጥ ለወደፊቱ ትምህርት እንዲወሰድበት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ የቄራ ማዘጋጃ ግንባታ ለመስራት በዕቅድ የተያዘው ብር 84,000,000 ተብሎ የተገለፀው ትክክል እንዳልሆነና በከተማው 2007-2010 ሲአይፒ ሰነድ ላይ ብር 99,271,085 እንደሆነ ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ላይ የገለፁ ቢሆንም ከባህርዳር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ባገኘነው 2007-2010 ዓ.ም ሲአይፒ ሰነድ ላይ ያልተገለፀ መሆኑ የተሰጠውን የሪፖርት ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

71. ከተሞቹ ለሚያሰሯቸው እያንዳንዱ ፕሮጀክቶች ሲታቀዱ በፕሮጀክት ጥናት መሰረት የዋጋ ግሽበትን ጭምር ከግንዛቤ አስገብተው ካልተሰሩ በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ የሚከፍሉ ከሆነ ለሌላ ፕሮጀክት ሊሆን የሚችል ገንዘብ ሊያሳጣ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣**

72. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

73. ሆኖም አብዛኛዎቹ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እንደማይጠናቀቁ ለማሳያ በ2007 ዓ.ም፡-

- ✓ በባህርዳር ሁለት ፕሮጀክቶች 122 እና 146 ቀናት ዘግይተው የተጠናቀቁ መሆኑ፣
- ✓ በአዳማ ሦስት ፕሮጀክቶች 201፣ 208 እና 244 ቀናት ዘግይተው የተጠናቀቁ መሆኑ፣

- ✓ በዲላ አንድ ፕሮጀክቶች 181 ቀናት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
- ✓ በቡራዮ አንድ ፕሮጀክቶች 127 ቀናት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
- ✓ በደብረብርሃን አንድ ፕሮጀክት 112 ቀናት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
- ✓ በደሴ አንድ ፕሮጀክት 185 ቀናት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
- ✓ በመቀሌ አንድ ፕሮጀክት 50 ቀናት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶች (Annual Progress Report) ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. በ2007፣ በ2008፣ በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ያልተጠናቀቁትን ፕሮጀክቶች ብዛት በአባሪ ስድስት ተቀምጧል፡፡

75. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በዚህ ቀን ስራ እንጀምራለን ብለን እንነሳለን ሆኖም በወቅቱ ጨረታ በማዉጣት ወደ ስራ ስለማይገባ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አይጀመሩም በዚህ ምክንያት አጠቃላይ ስራው ይዘገያል ሌላው እቅድ የሚፀድቀው በወቅቱ ስላልሆነ ስራዎች በወቅቱ አይጀመሩም ይህም ስራዎች እንዲጓተቱ ስለሚያደርግ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዳናጠናቅቅ ያደርገናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ ኮንትራት ስለማይፈረም የፕሮጀክት መነሻቸው ይገፋል ይህ ደግሞ ፕሮጀክቶቹ በወቅቱ እንዳይጠናቀቁ እንደሚደርግና ፕሮጀክቶች ወደ ክረምት እንዲገፉ በማድረግ በጥራት ስራቸው እንዳይካሄድ እንደሚያደርግ፣
- የዲላ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንደኛው ምክንያት አንዳንድ ማህበራት ዋጋ ሰብረው ይገቡና ከዛ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥማቸው ፕሮጀክቱን ጥለው ይጠፋሉ፣ ሁለተኛው የሚሰሩት ማህበራት የተለያየ ማሽኖች እጥረት ስላለባቸው በቶሎ ፕሮጀክቶቹ እንዳይጀመሩና እንዳይጠናቀቁ አድርጓል፣ ሌላው የዲዛይን ለውጦች ስለሚደረጉ በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ የሚወስድ መሆኑና ከግዢ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥመው መጓተትና የውጭ ምንዛሬ መጨመር ስለሚያጋጥም ፕሮጀክቶቹ በጊዜያቸው እንዳይጠናቀቁ እንሚያደርግ፣

- የሐዋሳ ከተማ የፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ይህ ችግር የሚፈጠረው አንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ እቅዱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ተጨማሪ ስራ እንዲሰራ ከህብረተሰቡ ጥያቄ ስለሚነሳ ለምሳሌ አንድ ሰፈር የሆነ ፕሮጀክት ስንሰራ እቅድ ይዘን ጨረታ ካወጣን በኋላ የሌላው ሰፈር ማህበረሰብ እኛም ጋር ይሰራልን ስለሚሉ ፕሮጀክቱ ሰፋ ተደርጎ ይሰራል ስለዚህ በፊት ከያዝነው በጀትና ጊዜ ጨምረን እናወጣለን፣ ሌላው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በሚኖርበት ጊዜ ይህ ችግር ያጋጥማል፣ እንዲሁም በሃዋሳ ከተማ የነበረው ከፍተኛ የሆነ የፀጥታና ብሄር ተኮር ግጭት ምክንያት ስራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ሊጠናቀቁ እንዳይችሉ እንዳደረገ በተጨማሪም ዋጋ ሰብረው የሚገቡ ኮንትራክተሮች በሚፈለገው ጊዜ ስራቸውን ሰርተው የማያጠናቅቁ መሆኑና የማሽነሪ እጥረት ለስራው መጓተት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳደረገ፣
- የባቱ ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ስራዎች የሚሰሩት በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ስለሆነ እነሱ የአቅምና የማሽነሪዎች ችግር ስላለባቸው በቶሎ ፕሮጀክቶቹን ሰርተው የማይጨርሱ መሆኑ እንዲሁም በዋጋ መጨመር ምክንያት ስራቸውን የሚያቋርጡ መሆናቸው ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጠናቀቁ እንዳደረገ፣

ገልፀዋል፡፡

76. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት የግብአት እጥረት ስለሚያጋጥማቸው፣ ሌላው የተጨማሪ ስራ የሚያጋጥማቸው መሆኑ፣ በከተሞቹ የፀጥታ ችግሮች ስለነበሩ እንዲሁም አንዳንዴ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ስራቸውን በሚገባ ስለማይሰሩ ስራቸውን ጀምረው አቋርጠው ስለሚጠፉና የወሰን ማስከበር ችግሮች በወቅቱ ስለማይፈቱ ስራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ እንዳደረገ ገልፀዋል፡፡

77. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽና እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የፕሮጀክቶች መዘግየት እንዳለ ይህም የሆነበት ምክንያት በተለይም ከወሰን ማስከበር፣ ከእቅድ መዘግየት፣ የአማካሪ ችግር፣ በክፍያ መዘግየት እና ፕሮጀክቶቹን

የሚሰሩት ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት የአቅም ውስንነትና ስራውን ጥሎ መሄድ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት እየተሻሻለ እንደመጣ ገልፀዋል፡፡

78. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ግኝቱ ትክክል እንደሆነና ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሻሻል የታየ ቢሆንም አሁንም ችግሩ ስላለ ወደፊት ጠንካራ ክትትል የሚደረግ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ በተለይ በፕሮግራሙ የመጀመሪያ ምዕራፍ (ULGDP I) የታቀፉ ከተሞች አብዛኛዎቹ መጓተት ያለባቸው እና ከልምድ ችግሮቹን መቅረፍ ስለነበረባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

79. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውሉ ላይ በታቀደላቸው ጊዜ ካልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶቹን ላልተገባ ተጨማሪ ጊዜ ከመዳረጋቸውም በላይ የፕሮጀክቱን ውጤታማነት እና ተጨማሪ ገንዘብ ለከተሞቹ እንዳይለቀቅ ከማድረጉም በላይ ባላለቁ ፕሮጀክቶች በሚከሰት አላስፈላጊ እንግልቶች የህብረተሰቡም እሮሮ ሊያስነሳ ይችላል፡፡

**የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ፣**

80. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

81. ሆኖም አንዳንድ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባላቸው ዋጋ እንደማይጠናቀቁ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ለመጥቀስ ያህል፡- በኦዲቱ በናሙና በታዩ ከተሞች

- ✓ በዲላ በ2007 ዓ.ም ከተሰሩት የውሃ መውረጃ ቦይ ስላብ Excavation ስራ ለመስራት ኮንትራቱ የተፈረመው በብር 13,104 ቢሆንም ሆኖም የፕሮጀክት ኮሚቴው ሳይስማማ፣ የስራ ትዕዛዝ ሳይሰጥና ሌላ የተጨማሪ ስራ ውል ሳይፈረም (without justification, work order and agreement) ብር 88,256 (673%) ጨምሮ መሰራቱ እንዲሁም Cart away excavated soil ለመስራት ውሉ በብር 27,456 ቢፈረምም ሆኖም አሁንም የፕሮጀክት ኮሚቴው ሳይስማማ፣ የስራ ትዕዛዝ ሳይሰጥና ሌላ ውል ሳይፈረም በብር 102,864 (374%) ጨምሮ መሰራቱ፣

✓ በሐዋሳ በ2010 ዓ.ም ከተሰሩት የጎርፍ መውረጃ ቦይ የክዳን ግንባታ ኮንትራቱ የተፈረመው በብር 13,818,756.82 ሲሆን ሆኖም በተጨማሪ ስራ ምክንያት በብር 2,145,207.93 (15.52%) ጨምሮ የተፈራረመ መሆኑ፣ በ2009 ዓ.ም ከተሰሩት Public toilet ኮንትራቱ የተፈረመው በብር 1,577,551.47 ሲሆን ሆኖም በተጨማሪ ስራ ምክንያት ብር 704,37946.46 (44.65%) ጨምሮ የተፈረመ መሆኑ፣

✓ በድሬደዋ በ2007 ዓ.ም ከተሰሩት construction of flood protection wall project Excavation for foundation ሲሰራ ኮንትራቱ የተፈረመው በብር 318,000 ለመስራት ቢሆንም ሆኖም የፕሮጀክት ኮሚቴው ሳይስማማ፣ የስራ ትዕዛዝ ሳይሰጥና ሌላ የተጨማሪ ስራ ውል ሳይፈረም ብር 212,487.60 (66.82%) ጨምሮ መሰራቱ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከከተሞቹ ሃላፊዎች ጋር ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የዲላ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2007 ዓ.ም አንድ ፕሮጀክት ልዩነት እንደፈጠረባቸው ምክንያቱም ፕሮጀክቱ የእግረኛ መንገድ ስለነበረው ዲች እንዲሰሩ ያልተፈቀደ እንደነበር በኋላ ግን የእግረኛ መንገዱን ወደ ዲች ለመቀየር ዲዛይኑ ሲሰራ ትክክል ስላልነበረ እንደገና እንዲሰራ እንደተደረገና እንደገና በሚሰራበት ጊዜ ዋጋው ከፍ እንዲል እንዳደረገ፣
- የሐዋሳ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፕሮጀክቶቹ እየተካሄዱ እያለ ተጨማሪ ሥራዎች ሊያስፈልጉ እንደሚችሉና ለምሳሌ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የግድ ክዳን መሰራት አለበት ምክንያቱም ክዳን ባለመሰራቱ ብዙ ችግሮች አጋጥመዋል ሰዎችም ጉድጓድ ውስጥ ገብተው የሞቱበት ሁኔታ አለ ስለዚህ የግድ ተጨማሪ ስራ መሰራት ስለነበረበት ከኮንትራት ውሉ በላይ ተጨማሪ ገንዘብ ሊወጣ እንደቻለ፣

ገልፀዋል፡፡

83. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከቁራ ጋር በተያያዘ

የኤሌክትሮ ሜካኒካል ዋጋ በመጨመሩና እነሱን ከማጓጓዝ ጋር በተያያዘ የመጣ እንደሆነ ሌላው ዕቅድ ሲይዙ ኮንቲንጀንሲ ሳይዙ በመስራታቸው እንደሆነና በደንብ ፕላን ካለማረግ የመጣ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

84. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ አንዳንድ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባላቸው ዋጋ እንደማይጠናቀቁ በማለት በባህር ዳር እና አዲግራት የተጠቀሰው በግንባታ ስራዎች ላይ ቀደም ተብሎ የታሰቡ ስራዎች በተፈጥሮ ክስተት የሚለዋወጡ በመሆናቸው እንደአግባብነቱ ሥርዓቱን የጠበቀ የዋጋ ጭማሪም ሆነ የመቀነስ አጋጣሚዎች እንዳሉ ቢወሰድ እና ሁለተኛ ውል የተባለው በግንባታ ላሉ ፕሮጀክቶች ሁለተኛ ውል የሚታሰር ሳይሆን ተጨማሪ ክፍያን የሚያስተናግድ ስምምነት እንደሚፈረም ነገር ግን ከዚህ ውጪ የተፈፀመ ከሆነ በዝርዝር አይተው ወደፊት መልስ እንደሚሰጡ፣ ለአንድ የስራ አይነት (Item) የቁፋሮ ስራ በ66.82% ጭማሪ አለ በሚል የተጠቀሰው በአይተም ደረጃ ሊጨምር እንደሚችል ነገር ግን ጭማሪው ከኮንትራት ውሉ ከተቀመጠው ጣራ (25%) በላይ መምጣት እንደሌለበትና በዲላ እና በሐዋሳ ከተሞች የተጠቀሱትን አስተያየቶች ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግና በአጠቃላይ ለፕሮጀክቶች ከውል በላይ መክፈል መንስኤ የሚሆኑ ሁኔታዎች በኮንስትራክሽን ሥራ አመራር ሂደት ውስጥ የሚታዩ ሆነው በአብዛኛው ከዲዛይን ዝግጅት አቅም ውስንነት ጋር ተያይዞ የተሟላ ዲዛይን ያለማዘጋጀት እና በኮንስትራክሽን ሂደት ሁሉንም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክስተቶችን በዲዛይን ቀድሞ ማወቅ ስለማይቻል ከኮንትራት በላይ የሚፈፀሙበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ገልፀዋል፡፡

85. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ ካልተጠናቀቁ ለሌላ መሰረተ ልማት ይውል የነበረውን በጀት እንዲሻሙ ከማድረጋቸውም በላይ ሥራዎች በበቂ ጥናት ላይ እንደማይመሰረቱ ያሳያል፡፡

### ከተሞች ከፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን በተመለከተ፣

86. ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንድ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአንዳንድ ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ ታውቋል፡፡ የ2001 እና ከ2007 እስከ 2010 ዓ.ም ያለው ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ የተመለከተ ሲሆን ከ2002 እስከ 2006 ያለው ማስረጃ ባለመቅረቡ ለማሳየት አልተቻለም፡፡

**ፕሮግራሙ ሲጀመር በ 2001 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | የሚለቀቅላቸው በጀት | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወላይታ ሶዶ | 16,103,493.00 | 1,972,458.00 | 12.2% |
| 2. | አርባ ምንጭ | 7,704,762.00 | 2,753,731.00 | 35% |
| 3. | ሐረር | 11,410,000.00 | 5,480,000.00 | 48.03% |
| 4. | ድሬደዋ | 70,800,000.00 | 10,200,000.00 | 14% |
| 5. | ጎንደር | 18,106,736.64 | 9,978,914.47 | 53.59% |
| 6. | አዲግራት | 6,927,750.00 | 2,664,943.20 | 38.47% |
| 7. | ሻሸመኔ | 10,537,685.00 | 5,632,859.00 | 53.6% |
| 8. | ጅማ | 12,118,000.00 | 2,770,000.00 | 22.86% |

**በ 2007 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | የሚለቀቅላቸው በጀት | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዲላ | 56,190,823.00 | 41,241,583.03 | 73% |
| 2. | ባህር ዳር | 362,708,961.39 | 209,601,321.91 | 58% |
| 3. | አምቦ | 18,943,452.84 | 5,435,467.19 | 29% |
| 4. | ደሴ | 133,020,745.00 | 103,400,051.88 | 78% |
| 5. | ጅማ | 137,370,135.10 | 47,923,614.90 | 35% |
| 6. | ቡራዩ | 265,037,369 | 141,458,229.89 | 53% |
| 7. | ሮቤ | 16,849,448.00 | 10,260,753.82 | 61% |
| 8. | ሚዛን አማን | 20,435,596.17 | 10,567,791.67 | 52% |
| 9. | ጋምቤላ | 37,259,973.00 | 12,748,070.40 | 34% |

**በ 2008 ዓ.ም**

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | የሚለቀቅላቸው በጀት | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዲላ | 62,604,725.00 | 37,778,395.62 | 60% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. | ባህር ዳር | 287,568,240.67 | 206,396,030.07 | 72% |
| 3. | ጅማ | 163,646,078.29 | 117,473,285.05 | 72% |
| 4. | ሻሸመኔ | 116,754,901.70 | 89922064.87 | 77% |
| 5. | ቡራዩ | 251,276,229.00 | 178,030,213.52 | 71% |
| 6. | ነቀምቴ | 84,214,952.00 | 65,326,645.23 | 78% |
| 7. | ሰበታ | 152,747,578.05 | 97,701,057.39 | 64% |
| 8. | ሚዛን አማን | 32,473,705.00 | 25,789,209.84 | 79% |
| 9. | ወላይታ ሶዶ | 132,793,275.14 | 90,334,967.97 | 68% |
| 10. | ጋምቤላ | 11,458,409.88 | 1,358,823.16 | 12% |
| 11. | አሶሳ | 31,929,412.96 | 16,314,118.78 | 51% |

በ 2009 ዓ.ም

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | የሚለቀቅላቸው በጀት | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ባህር ዳር | 396,673,426.00 | 297,123,542.78 | 74.90% |
| 2. | ጅማ | 60,886,779.09 | 95,997,083.81 | 56% |
| 3. | ቡራዩ | 66,317,766.32 | 155,634,091.43 | 55% |
| 4. | አምቦ | 44,356,314.34 | 23,503,141.00 | 53% |
| 5. | ሰበታ | 356,538,841.00 | 199,452,305.89 | 56% |
| 6. | ሮቤ | 49,969,331.61 | 35,709,887.92 | 71% |
| 7. | ሚዛን አማን | 42,240,260.53 | 25,485,973.75 | 60% |
| 8. | ጋምቤላ | 29,046,043.12 | 10,850,172.05 | 37% |
| 9. | ሐረር | 277,671,578.34 | 159,481,173.46 | 57% |

በ 2010 ዓ.ም

| ተ/ቁ | የከተማው ስም | የሚለቀቅላቸው በጀት | አፈፃፀም (በብር) | አፈፃፀም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዲላ | 77,730,037.30 | 32,832,889.82 | 42% |
| 2. | ሐዋሳ | 697,185,616.46 | 455,145,960.89 | 65% |
| 3. | ቡታጅራ | 54,740,270.16 | 41,785,252.67 | 76% |
| 4. | ጅማ | 189,614,486.63 | 119,652,035.00 | 63% |
| 5. | አምቦ | 67,744,666.44 | 25,142,111.12 | 37% |
| 6. | ቡራዩ | 226,068,755.70 | 152,131,177.14 | 67% |
| 7. | ሰበታ | 323,061,712.30 | 197,584,142.90 | 61% |
| 8. | ጋምቤላ | 46,180,012.97 | 25,636,411.36 | 56% |
| 9. | ሐረር | 135,552,624.50 | 30,668,547.52 | 23% |
| 10. | ድሬደዋ | 675,585,530.52 | 465,475,260.53 | 69% |

በጀት ብቻ መጠቀማቸው በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከከተሞቹ ኃላፊዎች ጋር ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. ከላይ ከሰንጠረዡ ከታዩት የከተሞች ዝርዝር ለማየት እንደተቻለው ከ2007 እስከ 2010 ዓ.ም ባሉት ተከታታይ ዓመታት ዝቅተኛ የበጀት አጠቃቀም ያሳዩ ሲሆን በተለይ እንደ ጋምቤላ፣ ቡራዩ፣ ጅማ እና ሚዛን አማን ያሉ ከተሞች በተደጋጋሚ አፈጻጸማቸው ዝቅ ያለ መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

89. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የባህር ዳር ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የካፒታል ኢንቨስትመንት እቅድ የጥራት ጉድለት፣ የክትትልና ድጋፍ እና ቁጥጥር አነስተኛ መሆን፣ ሌላዉ ደግሞ የኮንትራክተሮች የብቃት ችግር ነዉ በተለይ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ከፍተኛ ችግር መኖሩ የካፒታል ኢንቨስትመንት እቅድ አፈፃፀሙ አነስተኛ እንዲሆን እንዳደረገ፣
- በተጨማሪ የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተንከባለሉ (Roll ያደረጉ) ፕሮጀክቶች ነበሩ ከ2007 ወደ 2008 እንዲሁም ከ2008 ወደ 2009 ዓ.ም እነዚህ ጉዳዮች አፈፃፀሙን አነስተኛ እንዳደረጉትና በዚህም ምክንያት አመታዊ የአፈጻፀም ግምገማ (Annual performance asessemernt) ውጤታችን ደካማ እንዲሆን እንዳደረገ በተለይ በ2007 እና 2008 ዓ.ም ዝቅተኛ እንዲሆን እንዳደረገ፣
- የዱላ ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግዢ በሲአይፒ በተገለፀው እቅድ ወቅት ያለመግዛት ችግርና ማህበራትም ስራቸውን በሚገባ ስለማይሰሩ፣ ሌላው ደግሞ ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት ችግር ያመጣው እንደሆነ በተጨማሪም ዋናው ችግር ደግሞ የአመራሮች ስራ መልቀቅ (ተርን ኦቨር) ችግር ስለሚያጋጥም አፈፃፀሙ አነስተኛ እንዲሆን እንዳደረገ፣
- በተጨማሪ የዲላ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2010 ዓ.ም ጨረታ በወቅቱ ስላልወጣና አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ወደ 2011 ሮል ስላደረጉ አፈፃፀሙ በጣም አነስተኛ ሊሆን እንደቻለ ይህም በጣም ብዙ ነጥብ እንዳሳጣቸው ገልፀዋል፡፡

ይሁን እንጂ በተለይ የዲላ፣ የጅማ እና የባህርዳር ከተሞች ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በፕግራሙ የታቀፉ ከተሞች ከመሆናቸው አንጻር አፈጻጸማቸው መሻሻል እንዲሳይ ይጠበቅ ስለነበር የተሰጠውን ምክንያት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

90. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንደኛው ምክንያት ሲ አይ ፒ በወቅቱ ስለማይፀድቅና ጨረታ በወቅቱ ስለማይወጣ ከተሞቹ በጀታቸውን ባግባቡ ሳይጠቀሙበት ጊዜው የሚያልቅ መሆኑ እንዲሁም የአመራሩ በጀትን ያለመጠቀም ችግር በተጨማሪም የባለሙያዎች ከስራ መልቀቅና የወሰን ማስከበር ችግሮች ከተሞች ፈንዱን በአግባቡና በወቅቱ እንዳይጠቀሙበት እንዳደረገ ገልፀዋል፡፡

91. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በሰጡት አስተያየት የተገለፀው የከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ የፕሮግራሙ ፈንድ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የከተሞች ካፒታል መዋዕለ ነዋይ በጀት እንደሆነ፣ በ2007 ዓ.ም ቡራዩ፣ አምቦ፣ ሮቤ፣ ሚዛን አማን እና ጋምቤላ ከተሞች ወደ ፕሮግራሙ የገቡበት ዓመት ስለነበረ እና ለፕሮግራሙ አዲስ በመሆናቸው የተፈጠረ ክፍተት እንደሆነ፣ በ2008፣ በ2009 እና በ2010 ዓ.ም በባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ጅማ፣ ቡራዩ፣ ሮቤ እና ሚዛን አማን ከተሞች በነበረው አገር አቀፍ የፀጥታ ችግር የከተሞች አፈፃፀም ዝቅ ማለት እደቻለ እና ጋምቤላን በተመለከተ ግን የአመራር ቁርጠኝነት ባለመኖር የተከሰተ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

92. ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ ካልተጠቀሙበት የፕሮግራሙ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ መሆኑ እንዲሁም ከሌሎች አፍሪካ አገሮችና ከአገሪቷ ካሉ ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ከማድረጋቸውም ሌላ ገጽታቸውን ከመቀየር አኳያ የሚውለውን በጀት ፍሬ ቢስ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 2.4 የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ግዢን (Procurment) በተመለከተ

### ለፕሮጀክቶች የጨረታ ሂደት ከመጀመሩ በፊት የተሟላ ዲዛይን ስለመዘጋጀቱ፣

93. የከተማ አስተዳደሮቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ሊያዘጋጁ እንዲሁም የተሰሩት ዲዛይኖቹ በሌላ አካል ሊከለሱና ሊረጋገጡ ይገባል፡፡

94. ሆኖም የአዳማ፣ የቢሾፍቱ፣ የሮቤ፣ የሐዋሳ፣ የባቱ፣ የዲላ፣ የደብረ ታቦር፣ የባህር ዳር፣ የአሰላ የከተማ አስተዳደሮች

- ✓ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ማለትም Preliminary Design (Survey Data) እና የተለያዩ Drawing እንደማያዘጋጁ፣
- ✓ በየዓመቱ የሚሰሩት የፕሮጀክት ዲዛይኖች በሌላ አካል የማይከለሱ፣ የማይረጋገጡና የማይፀድቁ እንደሆነ፣
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የሚሰሩ የኮብል ስቶን መንገዶች (Cobblestone) ዲዛይኖች CBR (California Bearing Rate) for subgrade እና C-15 (charcterstics compressive strength or Concrete class) for curbstone የማይካተቱ መሆናቸው፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከከተሞቹ ሃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ጉዳዩ መሰረታዊ ችግርና ትክክል እንደሆነ፣ መጀመሪያ ዕቅድ ሲሰራ ዲዛይን እንደማይሰራ፣ ዕቅዱ የበሰለ እንዳይደለና እንደ ሃገር ተለምዶ ቅድሚያ ቢሰራ ጥሩ እንደሆነ በዚህም ምክንያት የዋጋ፣ የጊዜና በመሰረተ ልማቱ ላይ የጥራት ችግር እያመጣ እንደሆነ፣
- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2008 የመሬት ስራዉን የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ስለነበሩ አልተሰራም እንዲሁም ከ2010 በፊት የዲዛይን እና ዝርዝር

ሁኔታዎችን (design and break down) አይቶ የሚያፀድቅ አካል ስላልነበረ ዲዛይኖቹ በሌላ አካል አልተከለሱም እናም አልፀደቁም ከ2010 ጀምሮ ግን ኮንስትራክሽን ሪጉሌሽን በከተማ ደረጃ ተቋቁሞ ይሄንን ስራ እየሰራ እንደሆነ፣

- የደብረ ታቦር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነርና ምክትል ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ጨረታ ሰነድና ዲዛይን የማዘጋጀት ችግር ስላለ፣ የሚሰራው ዲዛይን በሌላ አካል የማይረጋገጥ በመሆኑ፣ የሙያ ክፍተትና ያለመረዳዳት ችግር መኖሩ፣ ዲዛይኑን ለማረጋገጥ ከክልልና ከፌዴራል መንግስት ፈቃድ ያልተሰጣቸው በመሆኑና የሚሰራው ስራ በሶፍትዌር የታገዘ ያለመሆኑ ያመጣው ችግር እንደሆነ፣

ገልፀዋል፡፡

96. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ችግር ፕሮጀክቱ ከመሰራቱ በፊት ዲዛይን ሊዘጋጅለት የሚገባ ቢሆንም ስለ ዲዛይን ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆንና የብቁ ባለሙያም እጥረት ስላለ እንዲሁም ቁርጠኛ የሆነ አመራር አለመኖር ችግር ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

97. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ በሰጡት አስተያየት ፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት ጥናትና የአካባቢያዊና ማህበራዊ ጥናት ስተሰራላቸው በዚያ ውስጥ Preliminary Design (Survey Data) የተካተተ ቢሆንም በተጠቀሱት ከተሞች የፕሮጀክቶች ዓይነት ስላልተገለፀ ጊዜ ወስዶ ማጣራት እንደሚያስፈልግ፣ ዲዛይኖች በሌላ አካል የማይከለሱ እንደሆነ የሚለውን ጊዜ ወስዶ ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግና በአንዳንድ ከተሞች የሚሰሩ የኮብል ስቶን መንገዶች (Cobblestone) ዲዛይኖች CBR for subgrade እና C-15 for curbstone የማይካተቱ መሆናቸው በተመለከተ ለወደፊቱ የሚስተካከል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

98. የከተማ አስተዳደሮቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን የማያዘጋጁ ከሆነና እንዲሁም የተሰሩት ዲዛይኖቹ በሌላ አካል ካልተከለሱ ተጨማሪ ወጪ ሊያስወጡና ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዳይሰሩ ሊደርግ ይችላል፡፡

**የአፈር ምርመራና የቅየሳ (ሰርቬይ) ጥናት በአግባቡ መሰራቱን በተመለከተ፣**

99. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የዲዛይን ጥራት እንዲኖራቸው ከመስመር መረጣ ጀምሮ የአፈር ምርመራና የቅየሳ (ሰርቬይ) ጥናት ሊሰራላቸው ይገባል፡፡ በየከተማው የሚመደቡ የፕሮጀክት ኢንጂነሮቹ የቅየሳ ሥራው በአግባቡ መሰራቱን ሊከታተሉ ይገባል፡፡

100. ሆኖም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና ካየናቸው ከተሞች ከቀረቡልን ማስረጃዎች ለመረዳት እንደቻልነው የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች ሳይከናወኑ ግንባታዎች እንደተከናወኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ፡-

በ2009 በጀት አመት

- ✓ በባህር ዳር ከተማ የመንገድ መብራቶች (Street light) ሲሰሩ Cable test and IP test for lamp ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በደብረ ታቦር ከተማ Cobble stone road earthen work እና Greenery road median fencing ሲሰሩ እንደቅደምተከተላቸው CBR እና C-25 concrete tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በደሴ ከተማ የኮብል ስቶን መንገዶች በአራዳ እና ዳውዶ ክፍለ ከተሞች ሲሰሩ CBR ቴስት ሳይከናወን እንደተሰራ፣ Canal cover and walk way construction ሲሰራ C-25 concrete test for slab covers ሳይከናወን እንደተሰራ እንዲሁም ክፍት የውሃ መውረጃ ትቦ ሲሰራ C-25 concrete test for culvert boxes ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአዲግራት ከተማ Drainage እና small bridge projects concrete work ሲሰሩ compressive strength (C-25) tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በፍኖተ ሰላም ከተማ Concrete pipe construction ሲሰራ C-25 concrete strength test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በጎንደር ከተማ Streetlight እና Drainage ሲሰሩ እንደቅደም ተከተላቸው Concrete test for C-25 pole pad, cable test, and IP test for lamp እና C-25 concrete test for slab cover ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በሐረር ከተማ retaining wall project's ሲሰራ bearing capacity ሳይከናወን እንደተሰራ፣ ቄራ ማዘጋጃ ሲሰራ soil test ሳይከናወን እንደተሰራ እንዲሁም street light ሲሰራ materials tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣

- ✓ በጅጅጋ ከተማ ጌጠኛ መንገድና የጠጠር መንገድ ሲሰራ soil test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በመቀሌ ከተማ የውሃ መውረጃ ቦይ እና ድልድይ ሲሰራ compressive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በኮምቦልቻ ከተማ በቀበሌ 05 ጌጠኛ መንገድ ሲሰራ CBR test ሳይከናወን እንደተሰራ፣ Open drainage with culvert ሲሰራ C-25 concrete test for culvert boxes ሳይከናወን እንደተሰራ እንዲሁም street light ሲሰራ C-25 concrete test for pole pad, cable and IP tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአላማጣ ከተማ Drainage site A below cluster shade at Kebelle 04 construction work፣ cover slab from Kokob Tsibah elementary school to St. Gebreal condominium and from Haji Ali Mohammed to Ato Mohammed Hadush እና greenery fence እና internal expansion at Kebele 04 projects' concrete works ሲሰሩ compressive strength tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአርባ ምንጭ፣ ቡታጅራ፣ ቢጋምቤላ፣ አሶሳ እና አረካ ከተሞች በ2009 በጀት ዓመት ጌጠኛ መንገዶች ሲሰሩ comprehensive strength test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በደብረ ብርሃን ከተማ Cobble stone roads with earth work በቀበሌ 04 እና 08 ሲሰራ CBR tests ሳይከናወን፣ Open drainage kebele 06 ሲሰራ C-25concrete test ሳይከናወን እንዲሁም street light ሲሰራ Cable test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአክሱም ከተማ Drainage እና Bridge projects concrete works ሲሰሩ compressive strength test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በሚዛን አማን ከተማ የጌጠኛ መንገዶች ሲሰሩ compressive strength test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በነቀምቴ ከተማ የጌጠኛ መንገዶች ሲሰሩ soil (CBR) እና compaction tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በሞጣ ከተማ Bridge ሲሰራ C-30 concrete strength test ሳይከናወን እንደተሰራ፣ Slab culverts ሲሰራ C-25 concrete strength test ሳይከናወን

እንደተሰራ እንዲሁም Drainage ሲሰራ C-25 concrete strength test for pre-cast beams ሳይከናወን እንደተሰራ፣

- ✓ በሮቤ እና በሰበታ ከተሞች ጌጠኛ መንገድ ሲሰራ CBR (soil)፣ quarry site እና compaction tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በወልዲያ ከተማ የውሃ መውረጃ ቦይ እና SME Shade ሲሰሩ እንደ ቅደም ተከተላቸው C-25 concrete test for culvert boxes እና C-25 concrete test for pillar works ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በውቅሮ ከተማ የውሃ መውረጃ ቦይ ሲሰራ compressive strength (c-25) test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በሰመራ ከተማ ጌጠኛ መንገዶች ሲሰሩ፣ Street light expansion on main road እና Greenery fence and fountain upgrading ሲሰሩ እንደ ቅደምተከተላቸው CBR፣ Concrete test for c-25 concrete pad, cable and IP tests እና C-25concrete test for fountain civil works ሳይከናወን እንደተሰራ፣

በ2008 በጀት ዓመት

- ✓ በወልዲያ እና በአዲግራት ከተሞች ሁሉም ጌጠኛ መንገዶችና የውሃ መውረጃ ቦዮች ሲሰሩ CBR ቴስት ሳይከናወን ምን እንደተሰራ፣
- ✓ በሐረር እና ጅጅጋ ከተሞች እንደቅደም ተከተላቸው የቁራ ማዘጋጃ የጭማሪ ስራ (additional work) እና masonry drainage project ሲሰራ Compressive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአዳማ ከተማ በ2008 በጀት ዓመት በቀበሌ 04 እና 01 ከልቨርት እና የጠጠር መንገድ ኮንትራት ውሉ በሚጠይቀው መሰረት የአፈር ምርመራ ሳይደረግ እንደተሰራ እንዲሁም የጠጠር መንገድ (Gravel Road) ሲሰራ የአፈር ምርመራ ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአምቦ ከተማ ጌጠኛ መንገዶች እና የውሃ መውረጃ ቦይ ሲሰሩ CBR (soil test) ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአሰላ ከተማ Bridge እና drainage's slab cover ሲሰሩ comprehensive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በባቱ (ዝዋይ) ከተማ የጠጠር መንገድ ሲሰራ compressive እና soil tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣

- ✓ በቡራዩ እና በአድዋ ከተሞች የጌጠኛ መንገዶች እና የውሃ መውረጃ ቦይ ሲሰሩ CBR test ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በሻሸመኔ ከተማ Bridge እና culverts ሲሰራ compressive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአርባ ምንጭ ከተማ Bridge፣ drainage's slabs እና culverts ሲሰሩ compressive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአረካ ከተማ Bridge ሲሰራ compressive tests ሳይከናወን እንደተሰራ፣
- ✓ በአላማጣ፣ በሁመራ እና በአክሱም ከተሞች የጌጠኛ መንገዶች ሲሰሩ CBR (Soil) tests ሳይከናወን እንደተሰራ በሽሬ እንደስላሴ ከተማ የጌጠኛ መንገዶችና አረንጓዴ ቦታዎች (greenery projects) ሲሰሩ CBR (Soil) tests ሳይከናወን እንደተሰራ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

101. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እነደዚህ አይነት ነገሮች እንደሚከሰቱና እንደ ትምህርት እንደሚወሰዱ ምናልባት ትንንሽ ከልቨርቶች ስለሆኑ ብዙም ችግር አይመጣም በማለት እንደሆነና ወደ ፊት በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ይሄ አይነት ችግር እንዳይከሰት እንደሚጥሩ፣
- የባህርዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነርና ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2009 ዓ.ም የመብራት ስራ ለነሱ አዲስ ስለነበረ Cable test እና IP test for lamp ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር ስላልነበረና የእውቀትና የልምድ ችግር የነበረባቸው በመሆኑ የተፈጠረ እንደነበረ፣

ገልፀዋል፡፡

102. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት አንዳንድ ከተሞች እነዚህን ነገሮች የሚሠራላቸው ተቋም በአካባቢያቸው ያለመኖር ሲሆን ሌሎች ምክንያቶች የማስፈፀም አቅም ክፍተት፣ የኢንጂነሮቹ ለስራው ትኩረት ሰጥተው ያለመስራት፣ የጊዜ እጥረት በማጋጠሙ ምክንያትና የአፈር ምርመራ ላብራቶሪ በማይኖርበት ጊዜ በተለምዶ ስራዎች ስለሚሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

103. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት በአርባ ምንጭ፣ ቡታጅራ ጋምቤላ፣ አሶሳና አረካ ከተሞች በ2009 ዓ.ም የኮብል ስቶን ድንጋይ ንጣፍ መንገዶች ሲሰሩ compressive strength test ሳይከናወን ተሰርቷል የተባለው የድንጋዩ ይሁን የአፈሩ የየትኛው ማቴሪያል compressive strength test እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም የኮብል ስቶን ድንጋይ ንጣፍ በቅድሚያ የድንጋዩ አይነት ከካባው ሳይት ታይቶ ድንጋዩ ጥቁር ዓለት (Basaltic) ከሆነና ውሃ የማይመጥ ከሆነ ለኮብል ስቶን ድንጋይ ንጣፍ መንገድ ስራ እንደሚመረጥና የcompressive strength test እንደማያስፈልገው፣ አፈሩ ከሆነ ደግሞ በአካባቢው ከዚህ በፊት የአፈሩ ናሙና ለኮብል ስቶን፣ ለጠጠር መንገድ፣ ለህንፃ ወይም ለድልድይ ሥራ የተጠና ካለ እና በባለሙያ እይታ የሚገነባበት አፈር የናሙና ጥናት ከተደረገለት አፈር ብዙም ልዩነት ከሌለው አስቀድሞ የተጠናውን አፈር Bearing Capacity Test ውጤት መውሰዱ ወጪን እንደሚቆጥብ፣ የአፈር እና የድንጋይ ምርመራ ከበጀት፣ ከፕሮጀክት ብዛት እና ከጊዜ አንፃር ቀደም ብለው በአካባቢው ከተሰሩት ፕሮጀክቶች ታሳቢ ተደርጎ ሲሰራ የነበረ ቢሆንም መሻሻል እያሳየ እንደመጣ እና ግኝቱ መጣራት ቢኖርበትም ኮንክሪት ቴስት ያለመሰራቱ እንደ ክፍተት እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

104. በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ

- የመንገድ መብራት በተመለከተ የሚመጣው እቃ ከህጋዊ አቅራቢ ድርጅት እና እቃውም በISO ከተረጋገጠ ከተሞች በዚህ አግባብ እንደሚሰሩ፣
- CBR በአጠቃላይ የመሬቱን የመሸከም አቅም ለማወቅ የሚረዳ ሲሆን ኮብል እስቶን ሲሰራ እንደዚህ አይነት መረጃዎች ከአቅራቢው ከተሰራ የአፈር ምርመራ ተወስዶ የሚሰራ ሲሆንና ከተሞችም በጥልቀት ያለውን የአፈር ሁኔታ በእይታም ጭምር ታይቶ ስለሚታወቅ በዚህ ሁኔታ ስራው ጥራቱን ጠብቆ እንዲሰራ እንደሚደረግ ከዚህም በተጨማሪ በብዛት ኮብል ስቶን ሲሰራ ቀድሞ በነበረና በአግባብ በተሰራ መንገድ ላይ ስለሆነ ከትራፊክ ፍሰት ከመሸከም አንፃር የጎላ ክፍተት አለመኖሩ፣
- C-25 concrete በተመለከተ በመጀመሪያ የኮንክሪት ደረጃው C-25 መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚስፈልግ ምክንያቱም የተለያየ ደረጃ ስላለ፣

- ከተሞች ከስራው አንገብጋቢነት እና ቶሎ በጀት ከመጠቀም አንፃር የኮንክሪት ደረጃውን በሚያስፈልገው የማቴሪያል ፕሮፖርሽን እንዲሆን ሳይት መሐንዲስ እየተከታተለ እና እያረጋገጠ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ፣
- በኦዲት የተገኙት ግኝቶች ለስራው ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት የተፈፀመ በመሆኑ ከማኑዋሉ አኳያ ግኝቱ ትክክል ሆኖ ለወደፊት በሚገነቡት መሰረተ ልማቶች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲደረግባቸው እንደሚደርጉ

ገልፀዋል፡፡

105. ይሁን እንጂ የመንገድ መብራትን በተመለከተ የመጣው እቃ ከህጋዊ አቅራቢ ድርጅት እና እቃውም በISO ከተረጋገጠ ከተሞች በዚህ አግባብ እንደሚሰሩ የገለፁ ቢሆንም ገቢ የተደረገው ዕቃ በቅድሚያ በሚመለከተው ባለሙያ ተረጋግጦ መደ ስራ የገባ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ሪፖርቱ ወጭ እስከተደረገበት ጊዜ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

106. የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች በአግባቡ እና በተፈለገው መጠን የማይሰራ ከሆነ የሚሰሩት የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የአገልግሎት ጊዜቸውን ሳያጠናቅቁ ሊበላሹ ይችላሉ፡፡

**ሚ/ር መ/ቤቱ የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

107. ከተሞቹ የመሠረተ ልማት ግንባታ ጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶችን በመሰረተ-ልማት ግንባታ እቅዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሊያካሂዱ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመረጣ ሂደቱን ተከትሎ ተግባራዊ ስለመደረጉ ሊከታተል ይገባል፡፡

108. ሆኖም በአብዛኛዎቹ ከተሞች ግዢዎች (የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች) የመሠረተ ልማት ዕቅዱ (CIP) ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንደማይካሄዱና እደሚዘገዩ በዚህም ምክንያት በየበጀት ዓመቱ መከናወን የነበረባቸው ሥራዎች እንዲዘገዩ እያረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለማሳያ በናሙና ከታዩት ከተሞች መካከል

| ተ.ቁ | ከተማው እና አካባቢው | ጨረታ ይወጣል የተባለበት ጊዜ | ጨረታ የወጣበት ጊዜ | የዘገየበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀዋሳ | | | |
| | ▪ Yeshi cobble to Addis Hiwot Cobble | 17/11/16 | 24/12/16 | 37 ቀናት |
| | ▪ Rear of Total to Lema Tej Bet | 06/12/16 | 03/02/17 | 57 ቀናት |
| | ▪ Tabor Ecotourism Development | 28/10/16 | 19/12/16 | 51 ቀናት |
| 2 | ባቱ | | | |
| | ▪ Cobblestone from Batu Technic College to Adventist School | 27/09/17 | 06/04/10 | 192 ቀናት |
| | ▪ Cobblestone from along Hospital Cobblestone Road to Batu Elementary No.2 | 27/09/17 | 15/12/17 | 78 ቀናት |
| | ▪ Masonry drainage from New Asphalt Butajira Road along Fence of Cemetery to Batu Elementry Shool No.2 | 01/12/17 | 15/12/17 | 14 ቀናት |
| 3 | ዲላ | | | |
| | ▪ ከቀበሌ 14 መስጊድ ኮብል ስቶን እስከ ተናኜ ቤት | 30/03/17 | 30/04/17 | 30 ቀናት |
| | ▪ Construction of Masonary Drainage 02 Kuteba Sefe | 13/10/17 | 3/04/18 | 170 ቀናት |
| | ▪ Cobblestone Maru Bet Sefer | 19/11/16 | 02/01/17 | 43 ቀናት |

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ መቻሉ፡፡

109. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- ስለሁኔታው የሐዋሳ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ብዙ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ጨረታዎች ከወጡ በኋላ እንደሚሰረዙ መጀመሪያ ጨረታ ከወጣ በኋላ ያሸነፈው አካል እነሱ በፈለጉት ዲዛይን ሊሰራ እንደማይችል ከተገነዘብን ሌላ ጨረታ እንደሚወጣ፣ የፋይናንስ ስርዓቶችን በምንከተልበት ወቅት ጊዜው ስለሚሄድ ጨረታው በወቅቱ የማይወጣ መሆኑና ሌላው አንዳንድ በጣም በዝቅተኛ ዋጋ የአሸነፉ ተጫራቾች

ስራቸውን በሚገባ እንደማይሰሩ ሲገነዘቡ ሌላ ጨረታ እንደሚያወጡና በዚህም ምክንያት ዕቅዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ጨረታ ላይካሄድ እንደሚችል፣

- የባቱ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንደኛ ሲአይፒ የፀደቀው ቶሎ ስለነበረና እኛ ጨረታ ያወጣነው ግን ዘግይተን ስለነበረ እንደሆነ፣ የመሰረተ ልማት እቅድ ከፀደቀ በኂላ ሌላ ጨረታ ስለወጣ እንደሆነና ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ስራውን መስራት አለባቸው ስለተባለ ስራውን ለነሱ ለመስጠት ስለተፈለገ ሌላ ጨረታ ሊወጣ እንደቻለና መዘግየቶች እንደተፈጠሩ ሌላው የኮንስትራክሽን ፅህፈት ቤት በጊዜ ግዢ እንድንፈፅም ስላልፈቀደልን እንደሆነ፣
- የዲላ ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአመራር ቶሎ ቶሎ መቀያየርና ሲመደቡም ቶሎ ከሥራው ጋር ያለመተዋወቅና ጨረታዎች ቶሎ እንዲወጡ ያለማድረግ፣ በከተማው የፀጥታ ችግር ስለነበረ እንደሆነ፣ ሌላው ደግሞ የፋይናንስ ዲፓርትመንት ግዢዎችን በወቅቱ ያለማፅደቅ ችግር እንዲሁም የባለሙያዎች ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ መሆን ያመጣው ችግር እንደሆነና በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶች በወቅቱ እንዳይጀመሩና እንዳይጠናቀቁ እንዳደረገ፣

ገልፀዋል፡፡

110. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አንደኛው ምክንያት ፕሮጀክቱ የካሳ ክፍያ የሚከፈልበት ኬዝ ካለው ካሳውን ከፍሎ ወደ ስራ ለመግባት ጊዜ ስለሚወስድ እንደሆነና የአመራር መቀያየርም ለዚህ ምክንያት እንደሆነ ሌላው ደግሞ ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ስለነበር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡
111. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የጨረታ መጓጓተት አልፎ አልፎ ቢታይም ይህም የሚሆንበት ምክንያት ከዕቅድ መዘግየት ጋር በተያያዘና በወሰን ማስከበር ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡
112. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ፡-
    - በከተሞች የሚካሄደው የግዥ ሥራ አመራር ሥራን በተመለከተ የጨረታ ሂደቶች የመዘግየት ሁኔታ እንደሚታይ፣

- በዚህም የተነሳ በካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ ውስጥ ባለው የድርጊት መርሃ ግብር ግዥውን ለማከናወን እንዳልተቻለ፣
- እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሱት የቴክኒካል ስፔስፊኬሽን የሚያዘጋጁ የምህንድስና ባለሙያዎች ከፍተኛ ፍልሰት በመኖሩ የሚከሰት መዘግየት፣
- የጨረታ ሰነድ ዝግጅት አቅም ውስንነት፣
- የጨረታ ግምገማ መራዘምና አሸናፊውን ተጫራች በቶሎ ለይቶ ያለማሳወቅ፣
- ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን አሰልጥኖ አደራጅቶ በወቅቱ ያለማዘጋጀት እንደሆነና
- ይህን ችግር ለመቅረፍ በብሔራዊ ደረጃ የተነደፈውን የግዥ አፈፃፀም መለኪያዎች /Procurement management key performance indicators/ ከተሞች የአፈፃፀም መመዘኛ ነጥቦች ውስጥ እንዲከሰተቱ ተደርጎ ከተሞች በየዓመቱ የሚገመገሙበት አሠራር እንደተዘረጋና በዚህም ረገድ መሻሻሎች እንደታዩ

ገልፀዋል፡፡

113. ከተሞቹ የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶችን በመሰረተ-ልማት ግንባታ እቅዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለማካሄዳቸው አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች በወቅቱ እንዳይጀመሩና እንዳይጠናቀቁ፣ ለከተሞቹ በበጀት አመቱ የተመደበው ሀብት ሥራ ላይ እንዳይውል አድርጓል፡፡

**ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያካሄዱ ተቋማት ግዥ/ ቅጥርን በተመለከተ፣**

114. ሚ/ር መ/ቤቱ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ (*Annual performance Assessment*) ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሊያከናውን ይገባል፡፡

115. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያካሂዱ (Annual Performance Assessment) ተቋማት ግገር እስከ መስከረም 30 ግገርው መከናወን ቢኖርበትም ግገርው ከ2009 ዓ.ም በስተቀር በወቅቱ እንደልተካሄድ ታውቋል፡፡

| የአፈፃፀም ግምገማ የሚካሄድበት ዓ.ም | ግገርው የተፈፀመበት ቀን |
|---|---|
| 2005 | የካቲት 28/2006 ዓ.ም |
| 2006 | ጥቅምት 11/2007 ዓ.ም |
| 2007 | ጥር 4/2008 ዓ.ም |

| | |
|---|---|
| 2008 | ጥቅምት 22/2009 ዓ.ም |
| 2010 | እስከ ታህሳስ 19/2011 ዓ.ም ድረስ ያልተፈፀመ መሆኑ |

116. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት አግባብ ባልሆነ ምክንያት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተፈጠረ ችግር እንደነበር፣ ሌላው በግገር አፅዳቂ ኮሚቴ የመጣ ችግር እንደሆነ በተጨማሪም ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በነበረ ውዝግብ ምክንያት የመጣ እንደሆነ፣ እንዲሁም ተወዳዳሪዎች ቅሬታ ስለሚያስገቡ ችግሩ ታይቶ እስከሚፈታ መዘግየት እንደሚፈጠር ገልፀዋል፡፡

117. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የ2005 እና የ2007 ዓ.ም የራሱ ምክንያት ቢኖረውም ከተለመደው ጊዜ አንፃር በእጅጉ የዘገየ እንደነበር ለዚህ በምክንያት ምናልባት ሊጠቀስ የሚችለው የግገር ሂደቱ በተለያዩ ምክንያቶች ሊጓተት እንደቻለ፣ የ2008 ዓ.ም አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ Annual Performance Assessment በአሸናፊዎቹ መካከል ከፍተኛ መካሰስ የነበረበት ቢሆንም በወቅቱ በበላይ አመራሩና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አመራሮች ውይይት ለመፍታት እንደቻለ፣ የግገር ሂደቱ ከማስፈፀም አቅም ጋር የሚያያዝና እጅግ በርካታ ትልልቅ የጨረታ ዶክሜንቶችን ከማየት አንፃር ያጋጠመ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

118. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ለዓመታዊ የከተሞች አፈፃፀም ገምጋሚ አማካሪ መረጣ መዘግየት ዋነኛ ምክንያት ከግገር ሂደት መራዘም ጋር የተያያዘ እንደሆነ፣ ከዓለም ባንክ ጋር በመወያየት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እንዲቻል በMulti year contract አሠራር ሁለት አማካሪዎች ተመርጠው በአሁኑ ወቅት የ2010 ዓ.ም አፈፃፀም ግምገማ በመካሄድ ላይ እንደሚገኝና የ2010 ዓ.ም በጀት ድልድል በወቅቱ ሊካሄድ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

119. ሚ/ር መ/ቤቱ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ (*Annual performance Assessment*) ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በወቅቱ ባለማካሄዱ ከፕሮግራም ፈንዱ ለከተሞች የሚለቀቀው ገንዘብ በማሳወቅ ረገድ መዘግየቶች እንዲፈጠር ማድረጉን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ ዝግጅት እንዲዘገይ እንዳደረገና ከፕሮግራሙ የሚለቀቀው በጀትም እንዲዘገይ በማድረግ፣ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጀመሩና ለሲአይፒ በጀት አፈፃፀም አነስተኛ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ሚ/ር መ/ቤቱ ለዓለም

ባንክ በወቅቱ ሪፖርት እንዳይቀርብ በማድረግ በየዓመቱ 500,000 ዩኤስ ዶላር እንዲያጣ አድርጓል።

## 2.5 ገቢን በራስ አቅም የመሰብሰብና የማሳደግ አቅምን በተመለከተ (Own Source Revenue Enhancement)

**ከተሞች በየዓመቱ ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ማሳደጋቸውን በተመለከተ፣**

120. ከተሞች የመሰረተ-ልማት እቅድ ላይ በተቀመጠው መሠረት ገቢ ሊሰበስቡና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ይገባል፡፡

121. ሆኖም የከተሞች የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ መሆንና በእቅዱ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ እና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ቢገባም ሆኖም ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት የማያሳድጉ ከተሞች መኖራቸው ታውቋል፡፡

122. የማዘጋጃ ቤት ገቢያቸውን ከመሬት ሊዝ ውጪና ከመሬት ሊዝ የተገኘው ገቢ ሲሆን ሌላው ደግሞ መንግስታዊ ገቢ ነው፡፡ በየአመቱ የተገኘው የገቢ ዕድገት ከ10 ከመቶ በታች የሆኑት ከተሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

- **ከመሬት ሊዝ ውጪ (Municipality Revenue Excluding Land Lease) በ10 በመቶ ያላሳደጉ ከተሞች፡-**

| በጀት ዓመት | የማዘጋጃ ቤት ገቢያቸውን ከመሬት ሊዝ ውጪ በ10 በመቶ ያላሳደጉ ከተሞች ዝርዝር በየአመቱ |
|---|---|
| በ 2007 | ደብረማርቆስ፣ መቀሌ፣ አድዋ፣ አክሱም፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ ውቅሮ፣ ሮቤ፣ ሚዛን አማን፣ አላማጣ እና ሰመራ፡፡ |
| በ 2008 | ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አምቦ፣ አሰላ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ነቀምቴ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ ሃዋሳ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ቡታጅራ፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ አድዋ፣ አላማጣ፣ ዉቅሮ፣ አሶሳ እና ድሬደዋ፡፡ |
| በ 2009 | ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ ኮምቦልቻ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ አምቦ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ቡታጅራ፣ ሆሳዕና፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ አላማጣ፣ ሁመራ፣ |

| | |
|---|---|
| | ዉቅሮ፣ ጅጅጋ፣ ጋምቤላ፣ ሰመራ እና ሐረር፡፡ |
| በ 2010 | ደብረ ማርቆስ፣ ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ ሮቤ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ቡታጅራ፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ አላማጣ፣ ዉቅሮ፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ጋምቤላ፣ ሐረር፣ ድሬደዋ፣ ሻሸመኔ፣ አሰላ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ነቀምቴ፣ ሃዋሳ እና አሶሳ ፡፡ |

- **የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ መሬት ሊዝን ጨምሮ** (Municipality Revenue including Land Lease) **በ 10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች፡-**

| በጀት ዓመት | የማዘጋጃ ቤት ገቢያቸውን ከመሬት ሊዝ ጨምሮ በ 10 በመቶ ያላሳደጉ ከተሞች ዝርዝር በየአመቱ |
|---|---|
| በ 2008 | ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደብረ ብርሃን፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አምቦ፣ አሰላ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ነቀምቴ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ ሐዋሳ፣ ዲላ፣ አረካ፣ ቡታጅራ፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ አድዋ፣ ሁመራ፣ አሶሳ እና ድሬደዋ፡፡ |
| በ 2009 | ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ሻሸመኔ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ቡታጅራ፣ ሆሳዕና፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ አድዋ፣ አላማጣ፣ ዉቅሮ፣ ጋምቤላ፣ ጅጅጋ እና ሃረር፡፡ |
| በ 2010 | ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ ቢሾፍቱ፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አምቦ፣ አሰላ፣ ባቱ፣ ነቀምቴ፣ ሐዋሳ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ቡታጅራ፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ አድዋ፣ ሁመራ፣ አሦሳ፣ ጋምቤላ፣ ሰመራ፣ ድሬደዋ እና ሃረር፡፡ |

- **የመንግስታዊ ገቢ** (State Revenue) **በ10 በመቶ ያላሳደጉ ከተሞች፡-**

| በጀት ዓመት | የመንግስታዊ ገቢ (State Revenue በ10 በመቶ ያላሳደጉ ከተሞች ዝርዝር |
|---|---|
| በ 2008 | ባህር ዳር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ሞጣ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አምቦ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ነቀምቴ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ቡታጅራ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ |

| | |
|---|---|
| | አዲግራት፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ ሁመራ፣ ሰመራ፣ ድሬዳዋ እና ሃረር፡፡ |
| በ 2009 | ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጅማ፣ አሰላ፣ ባቱ፣ ቡራዩ፣ ነቀምቴ፣ ሮቤ፣ ሰበታ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ሆሳዕና፣ ሚዛን አማን፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ አድዋ፣ አላማጣ፣ ውቅሮ፣ አሦሳ፣ ጋምቤላ፣ ጅጅጋ፣ ሰመራ፣ ድሬደዋ እና ሃረር፡፡ |
| በ 2010 | ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሞጣ፣ ወልዲያ፣ ሻሸመኔ፣ አሰላ፣ ሐዋሳ፣ ዲላ፣ ቡታጅራ፣ መቀሌ፣ አዲግራት፣ ሽሬ እንደስላሴ፣ አድዋ፣ አላማጣ፣ ሁመራ፣ አሦሳ፣ ጋምቤላ፣ ሰመራ፣ ድሬደዋ እና ሃረር |

እንደሆነ በኦዲት ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርቶችና ከከተሞቹ ኃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች ሙሉ ዝርዝር በአባሪ ሁለት ተያይዟል፡፡

123. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የባህር ዳር ከተማ ምክትል ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከራስ አቅም ጋር በተያያዘ ያሉትን አማራጮች ሙሉ በሙሉ ስላልተጠቀሙ እንደሆነና የመፈፀም ብቃት በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱ ገቢያቸውን ባቀዱት መጠን እንዳይሰበሰብ እንዳደረገ፣
- የዲላ ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት የፀጥታ ችግር የነበረ ሲሆን ገቢ ለመሰብሰብ አመቺ እንዳልነበረ ሌላው ደግሞ ፕሮጀክቶች ሲሰሩ በጣም ብዙ ካሳ ስለሚያስከፍሉ የተሰበሰበው ገቢ ተመልሶ ስለሚወጣ ይህም ገቢያችን እንዳናሳድግ አድርጎናል እንዲሁም የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት የቁርጠኝነት ችግር እንዲሁም የአመራሮች በቅንጅት ስራዎችን ያለመስራት ያመጣው ችግር እንዲሁም ከተማው በጣም ብዙ ገቢ ለመሰብሰብ እቅድ ስለሚይዝ የእቅድና አፈፀፃፀም ልዩነት እንደሚፈጠር፣

ገልፀዋል፡፡

124. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከተሞች ሊዝ ላይ ትኩረት

ስለሚያደርጉ ከሊዝ ውጪ ያሉ ቦታዎች ላይ ትኩረት አድርገው ያለመስራትና ገቢ ሊገኝባቸው የሚችሉ ትክክለኛ ቦታዎችን በሚገባ ለይቶ ያለመስራት ችግር እንዲሁም ለህብረተሰቡ ገቢና ታክስ ላይ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመስጠትና ለስራው ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት ችግር ያመጣው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

125. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- ከተሞች የአፈፃፀም ዕድገት ለማስመዝገብ በሚያስችል መልኩ እንዲያቅዱ ቢጠበቅም በመረጃ ክፍተት በእጃቸው ያለው ገቢ መጠን ማወቅ ስለሚቸገሩ ቢያንስ ባለፉት ከ3-5 ዓመታት አፈፃፀም በመገምገም እንደሚያቅዱ እንደሚፈለግ ሆኖም ግን የክልል ቢሮዎች (ክልል ከተማ ልማት ቢሮ ወይም ገቢዎች ባለስልጣን) እቅድ ወስነው ለየከተሞቹ ስለሚልኩላቸው አቅማቸውን ፈትሸው የማቀድ ሁኔታ እንደሌለ፣

ገልፀዋል፡፡

126. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት ማዘጋጃ ቤታዊ ላይ ዕድገት በሚፈለገው መጠን አለመሆኑና ራሱ እድገቱ በየጊዜው እያደገ እንዳይደለ ለዚህም በጣም ውስብስብ ምክንያቶች እንዳሉ፡-

- የማዘጋጃ ቤት ገቢ የመንግስት ገቢ (እንደ ገቢ ግብር፣ ተ.እ.ታ፣ ቲኦቲ የመሳሰሉት) አካል ተደርጎ እንደ ሃገር ማሻሻያ ጥናት ሳይደረግለት፣ ሕግና ስርዓት ሳይወጣለት (የመሬት ገቢ በስተቀር እሱም የህግ ማስከበር ክፍተት አለበት) እየተፈፀመ መሆኑ፣
- ይህንንና ሌሎች ወሳኝ ክፍተቶችን ለመሙላት በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በኩል የተዘጋጀው የከተማ ልማት ፋይናንስ ስትራቴጂ ሳይፀድቅ መቆየቱ፣ በዋነኝነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሆነው በዚሁ ክፍተት ምክንያት የመንግስት ግብርና የአገልግሎት ክፍያ አጣጣል፣ አወሳሰን፣ አሰባሰብ እና ሕግ ማስከበር ሥርዓቶችን ባልተከተ መልኩ ክልሎች ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስና አገልግሎት ክፍያ ታሪፍ መወሰናቸው፣
- ታሪፍ መወሰን ሊሰበሰብ ከሚችለው ገቢ መጠን ከመወሰን ጋር ቀጥታ ግንኙነት እያለው ክልሎች፣ ከተሞች ሊሰበስቡት የሚገባውን ኣመታዊ የገቢ መጠን ዕቅድ መወሰናቸው እንደ ተጨማሪ ውስንነቶች ሊጠቀሱ እንደሚችሉ

- በተጨማሪም በመረጃ ክፍተት ምክንያት ከተሞች በእጃቸው ያለው ገቢ መጠን (Potential or Taxable base) ማወቅ ስለሚቸገሩ ቢያንስ ያለፉት ከ3-5 ዓመታት አፈፃፀም በመገምገም እንደሚያቅዱ እንደሚፈለግ ሆኖም ግን የክልል ቢሮዎች (ክልል ከተማ ልማት ቢሮ ወይም ገቢዎች ባለስልጣን) እቅድ ወስነው ለየከተሞቹ ስለሚልኩላቸው አቅማቸውን ፈትሸው የማቀድ ሁኔታ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

127. እንዲሁም ቡና ጭነው ከከተማው ሲወጡ የነበሩ ከባድ ተሽከርካሪዎች ላይ የመንገድ መጠቀሚያ ተብሎ ይሰበሰብ የነበረው ገቢ እንዲቀር በመደረጉ በዋነኝነት 2007 ዓ.ም ላይ ከሚዛን አማን ከተማ አሰባሰብ አፈፃፀም ቅናሽ እንዲያሳይ ምክንያት ከመሆኑ በስተቀር የተቀሩት ከተሞች በየዓመቱ ከ10% በላይ የገቢ አሰባሰብ እድገት ያሳዩ መሆናቸው፣ በ2008 እና በ2009 ዓ.ም ገቢያቸው ዝቅ ያለው በሃገሪቱ በነበረው አለመረጋጋት ምክንያት እንደሆነ፣ በ2010 ዓ.ም ላይ ከ31ዱ አሰላ ከተማ ላይ ብቻ የመሬት ነባር ስሪት ኪራይ ውዝፍ ለማጥራት በ2009 ዓ.ም በተሰራው ስራ ምክንያት የተገኘው ውጤት በ2010 ዓ.ም ሊኖር ባለመቻሉ የተከሰተ ቅናሽ እንደሆነና አዲግራትና ጋምቤላ እድገታቸው ከ5-10 ከመቶ ውስጥ እንደሚገኙ፣ የተቀሩት በየዓመቱ ከ10% በላይ እድገት ያስመዘገቡ እንደሆነ እና ሁሉም ከተሞች የራሳቸውን አቅም በመፈተሸ እንዲያቅዱ ቢጠበቅም በክልል በኩል ዓመታዊ ዕቅድ ተወስኖ ስለሚሰጣቸው በየገቢ ርዕስ ከመሸንሸን የዘለለ ሥራ እንደማይሰሩ ገልፀዋል፡፡

128. ከተሞች የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ መሆኑ፣ በእቅዱ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ መቻላቸው እና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 በመቶ በላይ ለማሳደጋቸው ገቢ የመሰብሰብ አቅማቸው እንዳይጠናከር ማድረጉ፣ የራሳቸውን ገቢ በማሳደግ አቅማቸውን በይበልጥ እንዳያሳድጉ ማድረጉ፣ እንሰበስባለን ያሉትን ገንዘብ እንዳይሰበስቡ ከማድረጉም በላይ ከዩ.ኤል.ጂ.ዲ.ፒ ውጪ ያሉ በራሳቸው አቅም የሚሰሩትን ፕሮጀክቶች ፋይናንስ እንዳያደረጉ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡

## 2.6 ግልፅነትና ተጠያቂነትን በተመለከተ (Accountability and Transparency)

**ከተሞች የአገልግሎት ስታንዳርድ አውጥተው በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣**

129. ከተሞች የአገልግሎት ስታንዳርድ (የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና የመሬት አስተዳደር) አውጥተው ሊያዘጋጁና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

130. ሆኖም በ2010 ዓ.ም በአንዳንድ ከተሞች ለመጥቀስ ያህል

- ✓ በቡታጅራ፣ አረካ፣ ዲላ፣ ይርጋለም፣ ሚዛን አማን፣ አርባ ምንጭ፣ ሆሳእና፣ ወልዲያ፣ ደብረ ታቦር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና የመሬት አስተዳደርን በተመለከተ የዜጎች ቻርተር ኮፒ በክፍሎቹ የሌለ ወይም ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ✓ በወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ዲላ፣ በቡታጅራ፣ ይርጋለም፣ ሚዛን አማን፣ አርባ ምንጭ፣ ሆሳእና፣ ወልዲያ፣ ደብረ ታቦር ተገልጋዮች በትክክለኛው የመመዝገቢያ ፎርማት ላይ ማለትም በፎርማቱ ላይ የተገለጹት የተገልጋዩ ስም፣ አገልግሎቱን ለማግኘት የገባበትና አገልግሎቱን አግኝቶ የወጣበት ቀን፣ አገልግሎቱን ለማግኘት የፈጀበት ጊዜ፣ የተገልጋዩ ስልክ ቁጥር፣ የተገልጋይ ፊርማ ወዘተ፣ የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- ✓ በወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና፣ አርባ ምንጭ፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ይርጋለም እና ዲላ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርቶች የማይዘጋጁ መሆኑ፣
- ✓ በአርባ ምንጭ ከተማ ደካማ የምዘገባና የዶክመንቴሽን አያያዝ መኖር (Poor Documentation and Record Keeping)፣
- ✓ ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የተቀመጠው እስታንዳርድ የተለያየ የአመዘጋገብ ሂደት መኖር (The standards of similar services is not consistent across customer registered) ለምሳሌ አረካ ከተማ፣
- ✓ በዲላ እና ቡታጅራ ደካማ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት መኖር (Irregular Monitoring by officers and no recording of evidences)፣
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች ለመጥቀስ ያህል ዲላና ቡታጅራ ላይ የመሬት አስተዳደር ክፍል በስታንዳርዱ መሠረት ያልተዋቀረ መሆኑ፣
- ✓ በባህር ዳር፣ ደብረ ታቦር፣ ዲላ፣ ሐዋሳ፣ ባቱ እና ወላይታ ሶዶ አንዳንድ ነዋሪዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት እንደማያገኙ ለምሳሌ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስታንዳርድ ለከተማ ነዋሪዎች በሳምንት ሁለቴ የሚል ሲሆን አፈፃፀሙ ግን በሳምንት አንዴ ብቻ መሆኑ፣

- ✓ በሆሳዕና ለአንዳንድ አገልግሎቶች ተስማሚ የሆነ እስታንዳርድ ያልወጣላቸው መሆኑ ለምሳሌ አስፋልትና የውሃ መውረጃ ቦዮች የሚጸዱበት ስታንዳርድ፣ ለሆቴሎችና ለድርጅቶች የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እስታንዳርድ ያልወጣ እንደሆነ፣
- ✓ በ2007 ዓ.ም በተጠያቂነትና ግልፅነት (Accountability and Traansparency) ረገድ ሁሉም ክልሎችና ከተሞች ከመካከለኛው (መካከለኛው 64 ነው) ያነሰ እስኮር ወይም ውጤት ከጅማ በስተቀር ማምጣታቸው ማለትም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት በስታንዳርዱ መሠረት ያልሰጡና (የደረቅ ቆሻሻ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና የመሬት አስተዳደር እስታንዳርዶች) አብዛኞቹ ከተሞች መረጃዎችን በአግባቡ ያልያዙ መሆናቸው፣
- ✓ በ2008 ዓ.ም በተጠያቂነትና ግልፅነት (Accountability and Traansparency) ረገድ አብዛኞቹ ክልሎችና ከተሞች ከመካከለኛው (መካከለኛው 64 ነው) ያነሰ እስኮር (ውጤት) ማምጣታቸው ማለትም ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ በማደግ ላይ ያሉ ከተሞችና (ሰመራ፣ ጅጅጋ፣ አሶሳና ጋምቤላ) ሃረር 36፣ 42፣ 35 እና 6 ነጥቦች በዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ (Annual Performance Assesment) በቅደም ተከተላቸው ያመጡ መሆናቸው፣
- ✓ በ2009 ዓ.ም በተጠያቂነትና ግልፅነት አማራ 12፣ ኦሮሚያ 36፣ ደቡብ ህዝቦች 18፣ ትግራይ 42፣ በማደግ ላይ ያሉ ከተሞች 35 እና ሐረር 6 በአጠቃላይ 149 ነጥቦች ማጣታቸውና አሁንም ከተሞች በዚህ ረገድ በርካታ ነጥብ ከሚያጡባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ተጠያቂነትና ግልፅነት ረገድ መሆኑ፣
- ✓ በ2010 ዓ.ም በተጠያቂነትና ግልፅነት ረገድ አሶሳ፣ ሰመራ ሎጊያ፣ ባቱ፣ ነቀምቴ፣ አድዋ፣ አሰላ፣ ቢሾፍቱ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሁመራ እና ኮምቦልቻ ዝቅተኛ ነጥብ ማምጣታቸው፣

በኦዲት ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርት፣ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከተሞች ሰነዶችና ከከተሞች ኃላፊዎች ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

131. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር እና ምክትል ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በተቀመጠው በእስታንዳርድ

መሠረት ለመስራት ያልተቻለው የከተማው አርባናይዜሽን ሲጨምር የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ ይሄን ለማዳረስ የአገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች እጥረት ማጋጠሙ እንዲሁም የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ያመጣው ችግር እንደሆነና ይሄን ለመቅረፍ ጥናት እየተጠናቀቀ መሆኑ ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ተግባር ሲገባ ችግሩ እንደሚቀረፍ ሲገልጹ፣

- የዲላ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር እና ምክትል ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በስታንዳርዱ መሰረት ማስተናገድ የነበረብን ቢሆንም አንዳንድ ክፍተቶች እንዳሉና በስራ መደራረብ ምክንያት አንዳንድ አገልግሎቶች ላይ መዘግየቶች እየተፈጠሩ እንደነበረ እንዲሁም ብዙ ጊዜ አገልግሎት ሰጪዎች በስታንዳርዱ እየሰሩ ቢሆንም የመመዝገብ ችግር ስላለ አጠቃላይ ውጤቱ ላይ ዝቅተኛ እንዲሆን እንዳደረገ፣

ገልጸዋል፡፡

132. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት የሰው ሃይል እጥረት፣ እውቀትና ክህሎት ያለው ሠራተኛ ካለመኖሩ የተነሳ መሆኑ፣ ባለሙያዎቹ የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ተሰምቷቸው በሚገባ ያለመስራት ያመጣው መሆኑ፣ አመራሩም ክትትልና ግምገማ ያለማድረግ ችግር ስላለባቸው እንደሆነ፣ በተደራጀ ሁኔታ የስራ ወረቀቶችን ያለመያዝ ችግርና ስራዎች በስታንዳርዱ መሰረት እንዲተገበሩ ከማድረግ አንፃር ክፍተት ስላለ እንዲሁም የአፈፃፀም ችግሮችና ክፍተቶች በማጋጠሙ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

133. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የተጠቀሰው ግኝት ትክክል ሊሆን እንደሚችል ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለተጠቀሰው ጉዳይ ከፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ ከሆነ እጅግ ጥቂት ከተሞች /ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሀረር የመሳሰሉት/ ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛዎቹ ለፕሮግራሙ አዲስ ባለመሆናቸው የታዩ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ከከተሞች የማስፈፀም አቅም ክፍተትና አሰራርን በጥብቅ ዲሲፕሊን ይዞ ካለመተግበር የሚነሱ እንደሆነ ቢታይና ሆኖም ግን እንደ የከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ምክንያቱ ሊለያይ ስለሚችል ምክንያቱን ማጠቃለል እንደማይቻል እንደ አጠቃላይ አብዛኛዎቹ የአገልግሎት አሰጣጥ ጉዳዮች እንደ ሃገር ከነበረው ሰፊ የመልካም አስተዳደር ችግር

ጋር የሚቆራኝ ስለሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር የለም ማለት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡

134. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለተላከላቸው ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- ከተሞች በፕሮግራሙ ከመታቀፋቸው በፊት የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት የሰፈነባቸው እንዳልነበሩና መተግበሪያ መሣሪያ ያልነበራቸው እንደነበሩ፣
- ከጊዜ ወደ ጊዜ በፕሮግራሙ የታቀፉ ከተሞች የሚታየውን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማሻሻል ዘላቂ የተቋማዊ ሥርዓት በመዘርጋት ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ሰፊ ስራ ሲሰራ እንደቆየ፣
- በተለይ በተወሰኑ አገልግሎቶች በደረቅ ቆሻሻ፣ በመሬትና በግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ዙሪያ በፌዴራል ደረጃ ስታንዳርዶች ከተዘጋጁ በኋላ በሚመለከታቸው የክልልና ከተሞች ባለሙያዎች ተሳትፎ ሰነዱ እንዲዳብር ተደርጎ በክልሎች አማካኝነት ለከተሞች በማስተላለፍ ተግባራዊ ሲደረግ እንደቆየ ይሁንና መረጃ አያያዝና በስታንዳርዱ መሠረት ወጥነት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ክፍተቶች እንደነበሩ፣
- ከፎርማሊቲ አለመሟላትና መረጃ አያያዝ ጋር ተያይዞ ያሉ ክፍተቶችንም ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ሥራው በርካታ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ በመሆኑ የተቋማዊ አቅም በመገንባትና የቅንጅታዊ አሠራርን በማጎልበት የአገልግሎቱን አሰጣጥ ለማሻሻል ከፍተኛ ሥራ እየተሰራ እንደሚገኝ

ገልፀዋል፡፡

135. ከተሞች ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት ባለመስጠታቸው ምክንያት የመልካም አስተዳደር እሮሮ ማምጣቱ እንዲሁም ከተሞች በተጠያቂነትና ግልፅነት ረገድ አነስተኛ ነጥብ ሊያመጡ እንደቻሉ በዚህም ምክንያት ከተሞቹ ለተጨማሪ የመሰረተ ልማት ሊያውሉት ይችሉት የነበረ በርካታ ገንዘብ እንዲያጡ አድርጓል፡፡

**ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

136. ከተሞች ለሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች በወቅቱ፣ ተያያዥ ማስረጃዎች ሲቀርቡ ክፍያ ሊፈጽሙና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ በአፋጣኝ የሚታረሙበትና እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

137. ሆኖም በ2007 ዓ.ም

- ✓ በአሶሳ እና በአላማጣ 16 የሙስናና ብልሹ አሰራር (Fraud and Corruption) ኬዞች እንደታዩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ካቀረበው የ 2007 አመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ እንደተቻለ እና ከነዚህ መካከል 14 በአሶሳ ሲሆኑ 2 በአላማጣ እንደሆኑ እንዲሁም 7 እና 2 ኬዞች በአሶሳ እና በአላማጣ እንደ ቅደም ተከተላቸው እንደተፈቱ ቢገለፅም እንዴት እንደተፈቱ በሪፖርቱ ላይ ያልተገለጸና ሌሎቹ 7ቶቹ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ በ2007 ዓ.ም በአሶሳ የጌጠኛ መንገድ ግንባታ ከሳር ቤቶች እስከ ኖክ ማደያ ያለው ከተቋራጩ ጋር ውል ሲፈረም በውሉ ላይ የተቀመጠውን ነጠላ ዋጋውን በመቀየር ተቋራጩ የብር 681,547.50 ተጨማሪ እንዲከፈለው መደረጉና ተቋራጩ ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣

ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ችለናል፡፡

138. ስለሁኔታው የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ስለዚህ ጉዳይ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

139. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየትና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ በአሶሳ ሰነዱ ላይ እንደተመለከተው ነጠላ ዋጋ ተቀይሯል ተብሎ ሊጠረጠር የሚችለው (በነጠላ ዋጋው ላይ ያለው ስርዝ ድልዝ አሳማኝ ባለመሆኑ) በተ.ቁ 6.2፣ 7.1 እና 7.2 ያሉት ነጠላ ዋጋ ሲሆን ጠቅላላ ዋጋው ብር 681,547.50 ሳይሆን ብር 106,740 መሆኑ፣ የከተማ አስተዳደሩ ለክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ በ15/11/08 በደብዳቤ እንዳሳወቀው ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጫ ሳይከፈት የሚገኘውን ሰነድ ማየት እንደሚቻል መግለፁ፣ የጨረታ አካሂድ የነጠላ ዋጋ ግዢ በመሆኑ የጨረታ ኮሚቴው ወይም ድርጅቱ ጠቅላላ ዋጋን በነጠላ ዋጋ መሰረት መስራትና ማወዳደር ያለበት ሲሆን ሊኖር የሚችለው የዋጋ ልዩነት ችግር መነሻ ከBOQ ወደ ማጠቃለያ ሲወሰድ በኮንትራክተሩ የተደረገ ስህተት ሊሆን እንደሚችል በሰነዱ ላይ የሚያመላክት ነው

በሚል ከፌዴራል የአማካሪዎች ቡድን ጉዳዩን ያውቃል ከተባለው መሐንዲስ የተሰጠ ጥቅል ማብራሪያ የተወሰደ ቢሆንም በቀጣይ ጊዜ ወስዶ ማጣራት የሚጠይቅ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በአሶሳ እና በአላማጣ ስለተከሰቱት ሌሎች የሙስናና የብልሹ አሰራር ኬዞች ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

140. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ በዚህ ዙሪያ የተሰራ ስራ እንዳለና ያስመለስነው ሀብት (ገንዘብ) እንዳለ ነገር ግን ፕሮግራሙ በስትሪንግ ኮሚቴ ስለሚመራ ማንዴቱ የስትሪንግ ኮሚቴ አባል ለሆነው የፀረ ሙስና ኮሚሽን እንደሆነና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሁኔታዎችን በጥልቀት ተመልክቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

141. ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጉዳዩ ተጣርቶ በአፋጣኝ እንዲታረም እና እርምጃ እንዲወሰድ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ካልቻለ እና ከአስተዳደራዊ ውሳኔ ከፍ የሚል ሁኔታ ሲፈጠረም ጉዳዩን ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በማሳወቅ እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል ማድረግ ካልተቻለ በቀጣይ ብልሹ አሰራር የሚፈጸምበት ሁኔታ እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 2.7 የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናቶች ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘቡ መሆኑን በተመለከተ (Environmental and Social Safeguards)

### የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር ጥናትን በተመለከተ፣

142. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር ጥናት በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሊጸድቅ ይገባል፡፡

143. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በዲላ፣ ባህርዳርና አዳማ ከተሞች የፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት የሚዘጋጁትና በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ይሁንታ የሚያገኙ ፕሮጀክቶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ ለምሳሌ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2">የፕሮጅቱ ስም</th><th rowspan="2">ውሉ የተፈረመበት ቀን</th><th colspan="2">የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት</th></tr>
<tr><th>የተዘጋጀበት/የጸ</th><th>ልዩነት</th></tr>
</table>

| | | | ደቀበት/ ቀን | በቀን/በወር |
|---|---|---|---|---|
| | በባህር ዳር | | | |
| 1 | MSE Cluster Development Sub Project | 03/06/04 | 16/11/04 | ከ 5 ወር በኋላ |
| 2 | Bridge Construction Sub Project Civil work | 15/08/04 | 13/11/04 | ከ 3 ወር በኋላ |
| | በዲላ | | | |
| 3 | Low Cost House Construction | 30/10/2006 (07/07/2014) | መስከረም/2007 (መስከረም/2014) | ከ 3 ወር በኋላ |
| | በደብረ ታቦር | | | |
| 4 | MSE Shade Construction ቀበሌ 02 የከብት ማድለቢያ | 12/04/10 | 09/05/10 | ከ 1 ወር በኋላ |
| 5 | MSE Shade Construction ቀበሌ 06 የዶሮ እርባታ | 12/04/10 | 09/05/10 | ከ 1 ወር በኋላ |
| 6 | MSE Shade Construction ቀበሌ 06 የዶሮ እርባታ | 12/04/10 | በ17/05/10 | ከ 1 ወር በኋላ |
| 7 | የእግረኛ መንገድ ከቀበሌ 03 ሙሉ ወርቄ ህንፃ ወደ ስላሴ ቤተክርስቲያን | 12/04/10 | 17/05/10 | ከ 1 ወር በኋላ |
| | በአዳማ | | | |
| 8 | በ 2004 ዓ.ም Adama Gravel Road Project | 19/07/2004 (28/03/2012) | ሚያዚያ 2004 | ከ 1 ወር በኋላ |
| 9 | አዳማ ከ Sheria court up to Maya Hotel | 10/06/2008 (18/02/16) | ነሐሴ 2008 | ከ 6 ወር በኋላ |

144. እንዲሁም በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከየከተሞቹ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ከተደረገው ቃለመጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ✓ በዲላ፣ ይርጋለም፣ አርባ ምንጭ፣ ሆሳዕና፣ ወላይታ ሶዶ፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ቡታጅራ ወዘተ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ ሕብረተሰቡን ሳያማክሩ (No Public Consultation for Environmental and Social Screening) እንደሚዘጋጁ፣ ዓመታዊ የአተገባበር እቅድ ሳይዘጋጅ እንደሚቀርብ፣ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ቢኖሩም ሆኖም የሕብረተሰብ የመልሦ ማስፈር ጥናት ሳይከናወን እንደሚሰራ፣ የአካባቢያዊ ቁጥጥር ዕቅድ ሳይኖራቸው የሚዘጋጁ (No Environmental Monitoring Plan) መሆናቸው፣

- ✓ በዲላ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ቡታጅራ፣ ደብረ ብርሃን ወዘተ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲከናወን ቼክሊስቶቹ በሚገባ ሳይሞሉ እንደሚዘጋጁ፣ ወርሃዊ የክትትል ሪፖርት ሳይቀርብ የአካባቢና የማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት እንደሚዘጋጅ፣
- ✓ በነዋሪዎች መግቢያ አካባቢ የውሃ መውረጃ ቦዮች ሲሰሩ ክፍት ሆነው መሰራታቸው በህብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆናቸው ለመጥቀስ ያህል ወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና ወዘተ፣ አንዳንድ መንገዶች ሲሰሩ የውሃ መውረጃ ቦዮች አብረው ባለመሰራታቸው በመንገዱና በነዋሪዎች ቤት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣
- ✓ በአረካ ለዝቅተኛ ህብረተሰቦች ቤቶች ሲገነባ የመፀዳጃ ቤቶች ሳይኖራቸው እንደተገነቡ፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች ወደ ደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች መለወጣቸው፣
- ✓ ቦርከና ወንዝ የደረቅ ቆሻሻና የግንባታ ግብዓቶች መጠራቀሚያ መሆን፣
- ✓ በሚዛን አማን ለኮሶኮል ወንዝ ድልድይ ለመስራት የተቆፈረው ቦታ ጥልቀት ያለው ጊዜያዊ ኩሬ መፍጠሩና አጥር ስላልታጠረ በሰዎችና በእንስሳት እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣ ቦርከና ወንዝ የደረቅ ቆሻሻና የግንባታ ግብዓቶች መጠራቀሚያ መሆን፣
- ✓ በአብዛኛው የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ልየታ (Screening) ሪፖርት ሲሰራ ከዓለም ባንክ ፈንድ ለመጠቀም ብቻ ሲባል እንጂ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይቶ የማይሰራ እንደሆነና የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአንዱን ለሌላው ኮፒ ፔስት በማድረግ ሪፖርቶቹ እንደሚዘጋጁ (Copy and Pasting of information in Environmental and Social Screening Reports)፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

145. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የዲላ ከተማ የፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግኝቱ ትክክል እንደሆነና ይሄን ፕሮጀክት ወደ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት እንዲፀድቅ ይዘን ስንሄድ ፋይሉ እንደጠፋና ሊገኝ እንዳልቻለ በዚህም

ምክንያት ከነሱ ጋር ሊግባቡ እንዳልቻሉ ምንም ማድረግ ስላልቻሉ ፕሮጀክቱ ይሁንታ ሳያገኝ ወደ ውል ሊገባ እንደቻለ፣

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የግንዛቤ ጉድለት ችግር እንደሆነና ሰነዶች የሚዘጋጁት መሰራት በሚገባው ልክ እንዳልነበረና ወደ ጨረታ ከመገባቱ በፊት ስልጣኑ ባለው አካል መሰራት እንደነበረበት፣
- የባቱ ከተማ ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እስትሪት ላይት ኤክስፓንሽን ፕሮጀክት ላይ የአካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት ባለሙያው ቦታውን በትክክል ስላልተጠቀሰ የይሁንታ ፈቃድ አይሰጠውም ስላለ ፕሮጀክቱ የይሁንታ ፈቃድ እንዳላገኘ እንዲሁም የአካባቢና ማሕበራዊ ደህንነት ልየታ ሲሰራ ሙሉ በሙሉ ሳይንሱን አሟልቶና ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይቶ ከመስራት ጋር በተያያዘ አሁንም ችግሮች እንዳሉ፣
- የባህር ዳር ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅእኖ ጥናት የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ስለሆነ እንደሆነ፣ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ከመስራት ጋር በተያያዘ ብዙ ገና የሚቀር ነገር እንዳለና ሁሉም ፕሮጀክቶች እኩል ትኩረትና እስክሪንኒንግ ይሰራ ማለት ሳይሆን በተለይ በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያመጡ ፕሮጀክቶች ካሉ ለነዛ ለየት ያለ ትኩረት ሰጥቶ በጥልቀት ጥናቱ ሊሰራ እንደሚገባ፣
- በተጨማሪም የባህር ዳር ከተማ ፕሮጀክት ኢንጂነር የ2003 ዓ.ም የገበያ ማስፋፊያ (Market upgrading) ሲሰራ የመልሶ ማቋቋም (RAP) ጥናት አለ ተብሎ የተሰራ ቢሆንም ወደ አፈፃፀሙ ሲገባ ግን ውሉ በጥናቱ መሰረት ስላልሰፈረ የመልሶ ማቋቋም ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣ የ2010 ዓ.ም ደግሞ የቆሻሻ መድፊያ ጉድጓድ (Sanitary Land Fill) እንደገና በአዲስ ጥናቱ በኮንሰልታንት እየተጠና ስለሆነ ሰራው እንዳልተሰራ ሆኖም በአብዛኛው የከተማው የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ቶሎ ልየታዉን አድርጎ ካቀረበ በኋላ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት ጥናቱን አይተው ቶሎ አፅድቀው የማይልኩ መሆኑና የከተማው ባለሙያዎች ሄደው ካልጠየቁ ይዘው ቁጭ የማለት ችግር እንዳለና በቃል ይሁንታ ብቻ በመግለፅ ስራዉን ጀምሩ እንደሚሉ አንዳንድ ፕሮጀክቶች የይሁንታ ደብዳቤ እንዳልተሰጣቸው፣

- የደብረ ታቦር ከተማ ምክትል ከንቲባ እና ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግኝቱ ትክክል እንደሆነ፣ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅእኖ ልየታ አሁን አሁን ትንሽ እየተለመደ እንደመጣ፣ መጀመሪያ አካባቢ ፈንዱን ለማግኘት ሲባል ብቻ እንደሚሰራ፣ በፊት ልምዱም ስላልነበረ አይሰራበትም እንደነበረና አሁን አቅማቸው እየተገነባ ስለሆነ መሻሻሎች እንዳሉ፣

ገልጸዋል፡፡

146. የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግንባታቸው ከጀመረ በኋላ ይሁንታ ማግኘታቸው ትክክል እንዳይደለና የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት ከተደረገ በኋላ ነው ውሉ መፈረም የሚገባው ይሄ ቅደም ተከተሉን አውቆ ካለመስራት የመጣ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡን ሳያማክሩና የካሳ ክፍያ ሳይከናወን ስራው መሰራቱ ተቀባይነት የሌለው ነገር እንደሆነና አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ ካለመስራት የመጣ እንደሆነ በየደረጃው ያለው አመራር ለአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚሰጡት ትኩረት አናሳ በመሆኑ እንደሆነና የክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት የኢንቫይሮሜንታል ኦዲት አስፈላጊ ሲሆን ማድረግ እንዳለበት ህብረተሰቡም ለሚሰራው መሰረተ ልማት ያለው ንቃተ ህሊና ደካማ በመሆኑ በየጊዜው ግንዛቤውን ለማሳደግ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰራት እንዳለበት እንዲሁም የልየታ ሪፖርቶች ሲዘጋጁ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይተው አለመሰራታቸው አገር አቀፍ ችግር አልፎ ተርፎም የአለም አቀፍ ችግር መሆኑና በተለይ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ልየታው ሲከናወን በጣም በጥንቃቄ መከናወን እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

147. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት በደብረ ታቦር ከተማ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነት ልየታ በ2010 ዓ.ም በሚመለከተው አካል ከመፅደቁ በፊት ሦስት ፕሮጀክቶች የስራ ውል መሰጠቱን አስመልክቶ የተሰጠው አስተያየት ትክክል እንደሆነና በግልፅ ሥራን ለማስጀመር ለተቋራጩ ስራው የተሰጠው (Site Hand Over) ግን የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ጥናት በአካባቢ ጥበቃ ከፀደቀ በኋላ እንደሆነና ይህም ስራውን ለማፋጠን የተሰራ ሲሆን የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት መመሪያዎቹን ለመጠበቅ እንደተሞከረ፣ በዲላ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ቡታጅራና ደብረ ብርሃን በቼክሊስት

መሠረት አለመሠራቱን ትኩረት በመስጠት ተገቢው ክትትል እንደሚያደርጉ እንዲሁም አንዳንድ መንገዶች ሲሰሩ የውሃ ማፍሰሻ ቦይ አለመሰራቱ ባለው የገንዘብ ችግር እንደሆነና የአካባቢውን ኅብረተሰብ በማማከር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመስራት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ማናቸውም የውሃ ማፍሰሻ ቦይ ክዳን አብሮ እንዲሰራ ቅድሚያ የመስጠት በጎ ጅምር እንዳለ ገልፀዋል፡፡

148. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ፡-

- በደብረ ታቦር ከተማ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ልየታ በ2010 ዓ.ም በሚመለከተው አካል ከመፅደቁ በፊት ሦስት ፕሮጀክቶች የሥራ ውል መሰጠቱን አስመልክቶ የተሰጠው አስተያየት ትክክል ሲሆን በግልፅ ሥራን ለማስጀመር ለተቋራጩ ሥራው የተሰጠው ግን አካባቢና የማህበራዊ ጥናት በአካባቢ ጥበቃ ከፀደቀ በኋላ እንሆነ ይህም ሥራውን ለማፋጠን የተሠራ ሲሆን የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት መመሪያዎቹንም ለመጠበቅ እንደተሞከረ፣
- የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታና ተጽዕኖ ጥናት እና የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር ጥናት የሚመለከታቸው የክልል መ/ቤቶች ተግባርና ሃላፊነት ከመሆኑም ባሻገር ለዚሁ ስራ ማስፈፀሚያ በጀት እንዲያገኙ ተበጅቶ በስትሪንግ ኮሚቴ እየፀደቀ የሚሰራ በመሆኑ የፌዴራል እና የክልል አካባቢ ባለስልጣንም ትኩረት እንዲሰጠው ዋና ኦዲተር የሚመለከታቸው የፕሮግራሙ እስትሪንግ ኮሚቴ አባላት እንደተቋቋሙበት ተግባር፣ ሃላፊነትና ስልጣን አግባብነት እንዲያውቁት በኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ከተሞች ጋር በመሆን በድጋሚ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በቅንጅት ከመስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ስራዎችን በግዜ እንዲሰሩ ለማድረግ እና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደረግ፣
- በዲላ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ቡታጅራና ደብረ ብርሃን በቼክሊስት መሰረት አለመሰራቱን አስመልክቶ የተሠጠው አስተያየት ትኩረት በመስጠት ተገቢው ክትትል እንደሚደረግ

- ይህንንም በባለቤትነት እንዲከታተል የአካባቢ ጥበቃ የስትሪንግ ኮሚቴ አባል ቢደረግም መስራት የሚገባውን እየሰራ አለመሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

149. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ተግባራዊ አለመደረጉ ፕሮጀክቶች በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጡት ተፅእኖ እንዳይታወቅ፣ ምን ያህል ሰዎች በፕሮጀክቶቹ አማካኝነት እንደተፈናቀሉ እንዳይታወቅና ካሳ በወቅቱ እንዳይከፈላቸው ከማድረጉም በላይ የመልካም አስተዳደር ችግር ሊያመጣ እንዲችል እንዳደረገ ህብረተሰቡም ልማቱን በባለቤትነት እንዳያየው ያደርጋል፡፡

## 2.8 የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ (Job Creation)

**የሁለተኛው የከተሞች አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች (ዩኤልጂዲፒ) ላይ በተቀመጠው ዕቅዱ መሰረት አዳዲስ የስራ እድል ስለመፍጠሩ፣**

150. በሁለተኛው የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP II) የሚሳተፉ ከተሞች አዳዲስ የስራ ዕድል እንዲፈጠር በዕቅድ ሊይዙና በዕቅዱም መሰረት ሊተገብሩ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በዕቅዳቸው መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡

151. ሆኖም አንዳንድ ከተሞች በበጀት ዓመቱ ካቀዱት አንፃር ግባቸውን ሙሉ በሙሉ እያሳኩ እንዳልሆነ ለምሳሌ ያህል፡-

| ተ.ቁ | ከተማው | በእቅድ የተያዘው የስራ ዕድል | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ክንውን | ልዩነት በቁጥር | ልዩነት በመቶኛ | |
| 1 | በደብረ ታቦር በ2010 | 2536 | 1,603 | 933 | 36.79% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በደብረ ታቦር በ2010 | 1,054 | 792 | 262 | 24.86% | ቋሚ የስራ እድል |
| 2 | በጎንደር በ2010 | 3,073 | 613 | 2460 | 80.05% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በጎንደር | 2,330 | 384 | 1946 | 83.52% | ቋሚ የስራ እድል |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በ2010 | | | | | |
| 3 | በኮምቦልቻ በ2010 | 1,065 | 380 | 685 | 64.32% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በኮምቦልቻ በ2010 | 1,282 | 247 | 1035 | 80.73% | ቋሚ የስራ እድል |
| 4 | በባህር ዳር በ2010 | 5,540 | 3,841 | 1699 | 30.67% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በባህር ዳር በ2010 | 2,800 | 856 | 1944 | 69.43% | ቋሚ የስራ እድል |
| 5 | በደብረ ማርቆስ በ2010 | 574 | 92 | 482 | 83.97% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በደብረ ማርቆስ በ2010 | 2,251 | 1,424 | 827 | 36.74% | ቋሚ የስራ እድል |
| 6 | በፍኖተ ሰላም በ2010 | 10,194 | 1,556 | 8638 | 84.74% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| | በፍኖተ ሰላም በ2010 | 273 | 160 | 113 | 41.39% | ቋሚ የስራ እድል |
| 7 | በሐረር በ2010 | 3,666 | 1,679 | 1987 | 54.20% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| 8 | በድሬደዋ በ2010 | 5,158 | 1,394 | 3764 | 72.97% | ጊዜያዊ የስራ እድል |
| 9 | በሐረር በ2010 | 5,439 | 3,004 | 2435 | 44.77% | ጊዜያዊ የስራ እድል |

እንደሆነ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

152. ስለሁኔታው የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዋናው ምክንያት ከታች ያሉት አመራሮች በእቅዱ መሠረት ስለማያስፈፅሙ የመጣ ችግር እንደሆነና ሌላው ስምምነቱ የሚለው አብዛኞቹ ስራዎች የሚሰጡት ለተደራጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ውስጥ ላሉ ወጣቶች ቢሆንም አንዳንድ ስራዎች ለነዚህ ማህበራት

እንደማይሰጡና እቅዳቸው ላይ ኤልሲቢ ይላል ነገር ግን በዛ መሰረት ለወጣቶቹ የስራ እድሉ የማይፈጠር በመሆኑ በአንዳንድ ከተሞች የስራ እድል አፈፃፀሙ አነስተኛ ሊሆን እንደቻለ ገልፀዋል፡፡

153. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ የስራ እድል ፈጠራ በኦዲት ግኝቱ በአብዛኛው የተቀመጠው ትክክል እንደሆነና በሁለት ከተሞች ግን ልዩነት መኖሩ ማለትም በደብረ ታቦር ጊዜያዊ የስራ ዕድል እቅድ 1268 ክንውን 1603 እና ድሬደዋ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ዕቅድ 4171 ክንውን 3428 እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

154. የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መረጃው የተወሰደው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዓለም ባንክ ( IDA credit 5435-ET) በ August 22 2018 አዘጋጅቶ በላከው የ2010 (2017/18) የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተወሰደ በመሆኑ በደብረ ታቦር እና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል አልቻልንም፡፡

155. በከተሞቹ በዕቅዱ መሰረት ጊዜዊና ቋሚ የስራ ዕድል አለመፈጠሩ ከፕሮግራሙ አላማዎች አንዱ በመሆኑ የሚሰሩ ሥራዎች የአካባቢውን ህብረተሰብ ካላሳተፈ በህብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ እንዲነሳ ከማድረጉም በላይ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲነሱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 2.9 የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ መሰራታቸውን በተመለከተ (Quality of Infrastructure)

### የመሰረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው መሰራታቸውና ለተባለላቸው አገልግሎት እየዋሉ ስለመሆኑ፣

156. ከተሞች የሚሰሯቸው የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች በግንባታ ስፔሲፊኬሽን መሰረት ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም የመሠረተ ልማት አውታሮቹ በጥራት ስለመሰራታቸውና ለተባለላቸው አገልግሎት እየዋሉ ስለመሆኑ በዕቅድ እየያዘ ክትትል ሊያደርግና ሊደግፍ ይገባል፡፡

157. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው ከተሞች (አዳማ፣ ባህር ዳር፣ ሐዋሳ፣ ዲላ፣ ደብረ ታቦር ከተሞች እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ካየናቸው ሌሎች ከተሞች እንደተረዳነው

- ✓ በፕሮግራሙ ከሚሰሩት የመሠረተ ልማት ግንባታ መካከል የኮብል ስቶን ግንባታ ስራ የጥራት ችግሮች መኖር፣

- ✓ በተጨማሪም በአንዳንድ ከተሞች ፕሮጀክቶች ሲሰሩ በጥራት ባለመሰራታቸው፣ የዲዛይን ችግሮች በማጋጠማቸውና ዲዛይኑን ተከትሎ ስለማይሰሩ ከተጠናቀቁ በኋላ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ መሆኑ ለማሳያ፡-
- ✓ በ2007 ዓ.ም በአምቦ ከተማ የውሃ መውረጃ ትቦ ሲሰራ ክፍት ሆኖ (lacks ditch cover) መሰራቱ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ላይ እክል መፍጠሩ፣ በይርጋለም ከተማ የኮብል ስቶን መንገድና የውሃ መውረጃ ቦይ ሲሰሩ በጥራት ያልተሰሩ መሆኑ ማለትም በግሬደርና ኮምፓክተር በሚፈለገው መጠን ያልተጠቀጠቁ መሆኑ (they lack quality as they were not performed by the required machinery such as grader and compactor)፣
- ✓ በ2009 ዓ.ም በፍኖተ ሰላም ከተማ የውሃ መውረጃ ትቦ ሲሰራ ትቦዎቹ ሳይከደኑ መሰራታቸውና (without any cover (culverts) መጋለጣቸው ተሽከርካሪዎች ሲያልፉ በቀላሉ የሚበላሹ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ስዕል አንድ፡ በአምቦ የውሃ መውረጃ ትቦ ሲሰራ ክፍት ሆኖ** (lacks ditch cover) **መሰራቱ** (ከ 2007 **ዓ.ም** Value For Money **የተወሰደ**)፣



**ስዕል ሁለት፡ በፍኖተ ሰላም የውሃ መውረጃ ትቦ ሲሰራ ትቦዎቹ ሳይከደኑ መሰራታቸውና** (without any cover (culverts) **መጋለጣቸው** (ከ 2009 **ዓ.ም** Value for Money **የተወሰደ**)፣

- ✓ የኮብል ስቶን መንገዶች በግንባታ ዕቃዎች (ቁሳቁሶች) መከማቻ እንደሆኑና እየተበላሹ መሆን፣
- ✓ መኪኖች እየመጡ በሚያፈሱት የተለያዩ ግብዓቶች የኮብል ስቶን መንገዶችና ድልድዮች መዘጋትና መከማቻ መሆን፣
- ✓ የኮብል ስቶን መንገዶች በግንባታ እቃዎችና መሸከም ከሚችሉት ጭነት በላይ በከባድ መኪና እየተመላለሱባቸው እየተበላሹ እንደሆነ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ መቻሉ፣
- ✓ የጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት ለተለያዩ አገልግሎት ይውሉ የነበሩ የተጠናቀቁ ሼዶች የሲሚንቶና የተለያዩ እንጨቶች ማከማቻ እንዲሆኑ መደረጉ (ከተሰሩበት አላማ ውጪ እየዋሉ መሆኑ) ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ መቻሉ ፣
- ✓ በነዋሪዎች መግቢያ አካባቢ የውሃ መውረጃ ቦዮች ሲሰሩ ክፍት ሆነው መሰራታቸው በህብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆናቸው ለመጥቀስ ያህል ወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና ወዘተ፣ አንዳንድ መንገዶች ሲሰሩ የውሃ

መውረጃ ቦዮች አብረው ባለመሰራታቸው በመንገዱና በነዋሪዎች ቤት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣

- ✓ በአረካ የውሃ መውረጃ ቦዮች ወደ ደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች መለወጣቸው፣ በአረካ ለዝቅተኛ ህብረተሰቦች ቤቶች ሲገነባ የመፀዳጃ ቤቶች ሳይኖራቸው እንደተገነቡ፣
- ✓ በሚዛን አማን ለኮሶኮል ወንዝ ድልድይ ለመስራት የተቆፈረው ቦታ በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ጥልቀት ያለው ጊዜያዊ ኩሬ መፍጠሩና አጥር ስላልታጠረ በሰዎችና በእንስሳት እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣ ቦርከና ወንዝ የደረቅ ቆሻሻና የግንባታ ግብዓቶች መጠራቀሚያ መሆን፣
- ✓ የኮብል ስቶን መንገዶች ለጋራዥ ስራ ማዋል (ለምሳሌ በጎንደር)

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ስዕል ሦስት፡ በደሴ በመበላሸት ላይ ያለ የኮብል ስቶን መንገድ** (**ከ** 2010 **ዓ.ም ከቀረበ የአማካሪ ሪፖርት የተወሰደ**)



ስዕል አራት፡ በአዳማ በመበላሸት ላይ ያለ የኮብል ስቶን መንገድ



ስዕል አምስት፥ በሰመራ በመበላሸት ላይ ያለ የኮብል ስቶን መንገድ (ከ Value for Money የተወሰደ)




ስዕል ስድስት ፡ በደብረ ብርሃን የኮብል ስቶን መንገድ በግንባታ ቁሳቁሶች መከማቻ መሆን (ከ2010 ዓ.ም ከቀረበ የአማካሪ ሪፖርት የተወሰደ)



ስዕል ሰባት፥ በደብረ ታቦር የኮብል ስቶን መንገድ በግንባታ ቁሳቁሶች መዘጋት



ስዕል ስምንት፡ በጎንደር ለጋራዥ ስራ የዋለ የኮብል እስቶን መንገድ (ከ 2010 ዓ.ም ከቀረበ የአማካሪ ሪፖርት የተወሰደ)

158. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ የዲላ እና የባቱ ከተሞች ከንቲባዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ችግሩ የሚያጋጥም እንደሆነና የህብረተሰቡ የአመለካከት ችግር በመኖሩ ለህግ ተገዢ ያለመሆን እና የእርምጃ አወሳሰዱ ደካማ በመሆኑ ለችግር ያጋለጣቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ለአካባቢው ማህበረሰብ ጥሩ የሆነ ግንዛቤ በመፍጠር እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ትኩረት አድርገው እየሰሩ እንደሆነ በተጨማሪም የኮብል ስቶን መንገዱን በሚያበላሹና በግንባታ ቁሳቁሶች የሚሞሉትን ወንጀለኞች ጠንካራ እርምጃ በመውሰድ ላይ እንደሆኑ፣

159. የባህር ዳር፣ ደብረ ታቦር እና ሐዋሳ ከተሞች ከንቲባዎችና ፕሮጀክት ኢንጂነሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የኮብል እስቶን መንገዶች በግንባታ ዕቃዎች መከማቻ መሆናቸው እነሱም የገመገሙት እንደሆነና የማህበረሰቡ ንቃተ ህሊና ባለመዳበሩ ምክንያት የመጣ እንደሆነ በተጨማሪም ለህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ፅ/ቤቱ ባለመስጠቱ እና የቁጥጥር ስርዓቱ የተጠናከረ ባለመሆኑ ምክንያት እነዚህ ነገሮች ሊፈፀሙ እንደቻሉ ወደፊት ዘመቻ በማድረግ ችግሮቹን ለመቅረፍ እንደሚጥሩ ገልጸዋል፡፡

160. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ

- የከተሞቹ አስተዳደሮች ክፍተት ያመጣው መሆኑ፣
- የኮብል ስቶን መንገዶች ዓላማ ለመኪና መቆሚያ ሳይሆን ህብረተሰብ መመላለሻ እንዲሆን እንደነበረ ሆኖም ከዓላማቸው ውጪ ለተለያዩ አገልግሎቶች እየዋሉ መሆናቸውና ህግ ወጥቶ በሚያበላሹ አካላት ላይ ተገቢው ቅጣትና እርምጃ ሊወሰደባቸው የሚገቡ መሆናቸው፣
- ለህብረተሰቡም በቂ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ እንደሚገባ፣
- እነዚህን ነገሮች እየተከታተለ እርምጃ የሚወስድ አካል ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባና
- የኮብል ስቶን መንገዶች የጥራት ችግር በአብዛኛው የሚሰሩት የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ስለሆኑና ጀማሪ ስለሚሆኑ መንገዶቹ የጥራት ችግር እንደሚያጋጥማቸው ይሄን ለመቅረፍ የከተሞች የፕሮጀክት መሃንዲሶች እየተከታተሉአቸው ስህተት ሲኖር የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱና ተቋማቱን የማብቃትና ክህሎታቸውን በማሳደግ ችግሩን ሊቀርፉ እንደሚገባ

ገልፀዋል፡፡

161. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ የጥራት ችግር አለ ተብሎ የቀረበው አልፎ አልፎ የሚታይ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም አፈጻጸሙ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እንደመጣ በዋነኛነት ለጥራት ችግር መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ልምድ የሌላቸው መሆኑ፣ ከግብዓት ጋር ያለ ችግር ሲሆን ይህም ከክልሎች እና ከተሞች ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት እየተሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

162. ከተሞች በፕሮግራሙም ሆነ ከሌላ የበጀት ምንጭ የሚሰሯቸው የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ አለመሰራታቸውና ህብረተሰቡ የሚፈለግባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ ሊበላሹ፣ የመሰረት ልማቶቹ አገልግሎት ዘመን እንዲያጥር እና ለጥገና መንግስትም አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጣያደርጋል፡፡

## የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ መተላለፋቸውን በተመለከተ፣

163. በከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ርክክብ ሊከናወንላቸው፣ ወደ ህብረተሰቡ ሊተላለፉና የሚፈለገውን አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ርክክብ መደረጉንና ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡፣

164. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ የማይተላለፉ እንደሆነ እና ሲጠናቀቁም የሚመለከተው ኃላፊም በወቅቱ ርክክብ የማይደረግ መሆኑና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ርክክብ የተደረገበት ሰነድ ላይ መቼ ርክክብ እንደተደረገላቸው የማይገለፅ መሆኑና የሚመለከታቸው አካላት ፊርማ ያልሰፈረባቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ✓ በ2007 ዓ.ም በአረካ ከተማ ከቸሩ ቤት እስከ ሃዋርያት ቤተክርስቲያን እና ከአድማሱ ክሊኒክ እስከ ጆብሮ ቤት ድረስ ያለው የኮብል እስቶን መንገድ ይፋዊ ርክክብ ያልተደረገለት መሆኑ (acceptance certificate was not issued)፣ በአሰላ ከተማ የውሃ መውረጃ ቦይ እና የገበያ ቦታ ግንባታ ተከናውኖ ርክክብ ያልተደረገለት መሆኑ፣ በድሬደዋ ከተማ የአረንጓዴ መናፈሻ ቦታዎችና የኮብል እስቶን መንገዶች (Cobblestone) ከገንዴ ሸበሌ እስከ ካባ ያለው ሲሰራ ርክክብ ያልተደረገለት መሆኑ፣ በአሰላ እና ባቱ ከተሞች የኮብል ስቶን መንገድና የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሲሰሩ ርክክብ የተደረገበት ቀንና የሚመለከታቸው አካላት ፊርማ ያላረፈበት መሆኑ (lack the dates of acceptance and concerned officials and the contractors did not sign the documents)
- ✓ በ2008 ዓ.ም በአዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ጎንደር፣ ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ወልዲያ፣ ሰመራ ሎጊያ፣ ሁመራ ወዘተ ከተሞች የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ርክክብ ተከናውኖ ወደ ህብረተሰቡ ያልተላለፉ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

165. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው ለታዩ ከተሞች የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፡-

- የአዳማ ከተማ ከንቲባ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የመሰረተ ልማት ያለመሟላት ችግር እንዳለና በዛ ምክንያት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ወደ

ህብረተሰቡ እንደማይተላለፉና ዳሰሳ ሳይሟላና ትናንሽ ነገሮች ሳይሟሉ ለማስረከብ ችግር ስለፈጠረባቸው ያለቁትን ፕሮጀክቶች ለህብረተሰቡ እንዳልተላለፉ፣

- የአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ኢንጅነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ግኝቱ ትክክል እንደሆነና አንዳንድ ፕሮጀክቶችን ህብረተሰቡ የራሱ አድርጎ ክትትል ስለሚያደርግ ባይተላለፉ ምንም ችግር የለውም በማለት እንደሆነና ሁሉንም ትንንሽ ፕሮጀክቶችን ባናስተላለፍም በተለይ ወደፊት ወሳኝ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ለህብረተሰቡ እንደሚያስተላለፉ፣
- የደብረ ታቦር ፕሮጀክት ኢንጂነር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፕሮጀክቶች እንደተጠናቀቁ በመጀመሪያ ለቀበሌ፣ ቀበሌዎች ለልማት ቡድን፣ የልማት ቡድኑ ደግሞ ለህብረተሰቡ በተዋረድ ስለማያስተላለፉ ችግሩ የተፈጠረ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

166. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት የክዋኔ ኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተጠቀሰው መሠረት አስተያየት ለመስጠት ጊዜው መቼ እንደሆነና ፕሮጀክቶቹ ምን አይነት እንደሆኑ ያልተገለፀ በመሆኑ ተገቢ ምላሽ መስጠት እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

167. የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ የማይተላለፉ ከሆነ፣ ሲጠናቀቁም የሚመለከተው ሃላፊም በወቅቱ ርክክብ የማያደረግ ከሆነና ለተሰሩበት ዓላማ ወዲያውኑ የማይውሉ ከሆነ ከቆይታቸው ጊዜ በፊት ሊበላሹ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ሮሮ ሊያሰማና የመልካም አስተዳደር ችግር ሊያመጣ ይችላል፡፡

## 2.10 ከፕግራሙ ጋር የተያያዙ መረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ

### የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣

168. ሚ/ር መ/ቤቱና ከተሞች የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ሥራ ተቋራጮች፣ የፕሮጀክት ኢንጂነሮች፣ የፌዴደራልና የክልል የሞባይል ቡድን እና ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ (Annual Performance Assesement) የሚሰሩ አማካሪ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የአፈፃፀም ሪፖርቶች በሥርዓት እንዲያዙ እና ለመረጃውን ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

169. ሆኖም በሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- ✓ ሰነዶች በየሥራ ዘመናቸው በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተላቸው መሰረት ያልተቀመጡ መሆናቸውን፣ የማስረጃዎቹም አቀማመጥ በአመቺ ሁኔታ በቅደም ተከተላቸው ያልተቀመጡ መሆኑን መመልከት መቻሉና በተለያዩ ክፍሎች ተበታትነው የሚገኙ መሆናቸው እንዲሁም ከ2001-2006 ዓ.ም ያሉት መረጃዎችና ሰነዶች ከ 2001 ዓ.ም APA (Annual Performance Assesment) ሪፖርት በስተቀር ሌሎች ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረቡ መሆኑ፣
- ✓ በናሙና ተመርጠው በአካል በታዩት በባህር ዳር፣ በአዳማ፣ በዲላ እና በደብረ-ታቦር ከተሞች በአካል ተገኝቶ ባደረገው ምልከታ መረጃዎች የሚቀመጡባቸውን ቢሮዎች መመልከት የቻለ ቢሆንም በሁሉም ቢሮዎች ሰነዶች በየሥራ ዘመናቸው በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተላቸው መሰረት ያልተቀመጡ መሆናቸውን እና የማስረጃዎቹም አቀማመጥ በአመቺ ሁኔታ በቅደም ተከተላቸው ያልተቀመጡ መሆኑን መመልከት መቻሉ፣

ከተከለሱ ሰነዶችና ከከተሞቹ ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅና በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



ስዕል ዘጠኝ፥ በሐዋሳ ማዘጋጃ ቤት ሰነዶች ተበታትነው ተቀምጠው

170. ስለሁኔታው የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሥራ ሃላፊዎች ከቦታቸው ሲነሱና ሌላ ሰው በምትካቸው ሲቀጠር ተገቢውን ርክክብ ስለማያደርጉ እንደሆነና ያለፉት

አመራሮች ሲለቁ ፈቃደኛ ሆነው ሰነዶችን ስላላስረከቡ የመጣ ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በተገቢው መንገድ አደራጅቶ ሠነዶችን ከማስቀመጥ አንፃር በጣም ከፍተኛ ክፍተቶች መኖራቸው፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው ችግር ከተሞቹም ጋር እንዳለና የእቅድና ሪፖርት ያለመቀናጀት ችግር በርካታ ፕሮጀክቶች ስለሆኑ እነዚህን መረጃቸውን አቀናጅቶ ከማዘጋጀትና ሪፖርት ከማድረግ አንፃር ችግሮች መኖራቸውና ይሄን ለመቅረፍ ከወረቀት ሥራ ወጥተን መረጃዎችን በዳታ ቤዝ በመያዝ ሂደቱን የተቀላጠፈ ለማድረግ እየተሰራ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

171. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ከፍተኛ የሆነ የቢሮ ጥበትና የሠነዶች ማስቀመጫ ቦታ ችግር ያለ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ዋና ዋና ሰነዶችን በሚመለከት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በሶፍት ኮፒ እና በሃርድ ኮፒ የተደራጀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተመሳሳይም በከተሞችም ችግሩ ሊኖር እንደሚችል፣ በዚህ መሠረት የመረጃ አያያዝንና ፍሰቱን በጠንካራ ቅንጅት መምራት እንዲቻልና ችግሩን ለመፍታት ሲባል ከፌዴራል እስከ ከተሞች የመረጃ ሥርዓቱን የሚያዘምን ሲስተም ለማስለማት የሚያስችል የግዢ ሂደት እንደተጀመረ ገልፀዋል፡፡

172. ሰነዶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በከተሞች በተደራጀ ሁኔታ በቅደም ተከተል በአመቺ ሁኔታ ማስቀመጥ አለመቻሉ በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ በሚሄዱበት ወቅት ለወቅታዊ ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማግኘት ከጊዜ አንጻር ሊያስቸግርና ማስረጃዎች እንዲጠፉ በር ከመክፈቱም በላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

### በፌዴራል እና በክልል ያሉ ባለሙያዎች የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ፣

173. በፌዴራል ደረጃ ያሉ ባለሙያዎችና የክልል ባለሙያዎች መካከል የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

174. ሆኖም በፌዴራል ደረጃ ባሉ ባለሙያዎችና በክልል ያሉ ባለሙያዎች መካከል ያለው የመረጃ ልውውጥ አነስተኛ እንደሆነና ከክልል ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ ከከተሞች ጋር በመገናኘት ለማደራጀት እንደተሞከረ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

175. ስለሁኔታው የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት የክልልና የፌዴራል ሞባይል ቡድኖች ተቀናጅተው ካለመስራት የመጣ ችግር እንደሆነ፣ ተቀናጅተው ስለማይሰሩም ለአንዱ የሚሰጠው ምላሽ ለሌላው ሌላ መረጃ የሚሰጣቸው መሆኑና በቼክ ሊስት በተደገፈ መንገድ ካለመደገፍ የመጣ ክፍተት እንደሆነና ይሄን ለመፍታት የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፈፀሚያ እቅድ አዘጋጅተን መቼ መገናኘት እንዳለባቸው አስቀምጠን ሊሰሩበት እንደተዘጋጁ ገልፀዋል፡፡

176. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ በፌዴራልና በክልል የፕሮግራሙ ባለሙያዎች ያለው ቅንጅታዊ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት በሚመለከት በእኛ በኩል በጥቅል መገለፁ ትክክል አለመሆኑ ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ እንደሆነ ይበልጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመፍታት በ2010 ዓ.ም መጨረሻ በክፍተቶች ላይ ያተኮረ የሁኔታ ግምገማ ዳሰሳ በማድረግና የማስፈፀሚያ ስልት ሰነድ በማዘጋጀት ከህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ለሚገኙ ም/ቤቶችና አስፈፃሚ አካላት የተግባር ማስፈፀሚያ እንዲሆን ሰነዱ እንዲደርሳቸው እንደተደረገና በቀጣይም አፈፃፀሙን በጠንካራ ዲሲፕሊን እንደሚከታተሉና እንደሚደግፉ ገልፀዋል፡፡

177. ሆኖም የተዘጋጀው የማስፈፀሚያ ስልት ሰነድ በኦዲት ወቅት ያልቀረበልን እና ከህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ለሚገኙ ም/ቤቶችና አስፈፃሚ አካላት የተላከላቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃዎች ያልቀረበልን በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

178. በፌዴራል ደረጃ ባሉ ባለሙያዎችና በክልል ባሉ ባለሙያዎች የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመጠናከሩና ወጥ ባለመሆኑ የሚቀርቡት ሪፖርቶች ተመሳሳይ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ የሚቀርቡት ሪፖርቶችም ተዓማኒ እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፣**

179. በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል በቅንጅት የሚሰሩበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

180. ሆኖም በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል

- ✓ ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ እንደሆነ ለመጥቀስ ያህል
    - የእርስ በእርስ ልምድ መለዋወጥ ላይ፣ አቅም ግንባታ ላይ፣ በሪፖርት ፎርማት ላይ አንድ አይነት መግባባት አለመኖር፣ Monitoring and Evaluation ፎርማቶች ውስብስብ መሆናቸውና
    - ስልጠናና ድጋፍ ላይ በቅንጅት የመስራት ችግሮች መኖራቸውና የተሟላ ድጋፍና ክትትል ከመስጠት አኳያ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- ✓ የሪጅናል ሞባይል ቡድን ለከተሞች በቂ የሆነ ድጋፍ ባለማድረጉ የፌዴራል ሞባይል ቡድን በክልሎች በቀጥታ ገብቶ ድጋፍ ለማድረግ የተገደደ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ችለናል፡፡

181. ስለሁኔታው የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ችግሩ እንዳጋጠመና ችግሩ የሚፈጠረውም የሰራተኞች የደመወዝ ክፍያ በጣም አነስተኛ ስለሆነ፣ ብዙዎቹ በስራቸው ደስተኛ አለመሆናቸውና በደንብ የማይሰሩ በመሆኑና ከስራ የሚለቁ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነና ቅንጅታዊ አሰራሩ ደካማ ሊሆን እንደቻለ በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶችን በተፈለገው ጥራትና የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጠናቀቁ እንዳደረገ ገልፀዋል፡፡

182. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ በጥቅሉ በክዋኔ ኦዲት ሪፖርቱ እንደተገለፀው መቀመጡ ትክክል እንዳልሆነና ሆኖም ግን ቀደም ባሉት ጊዜያት በዋናነት በክልል ደረጃ የሚገኙት እነዚህ አካላት ከቅንጅትና ተልኳቸውን በሚገባ ከመወጣት አንጻር የተወሰነ ክፍተት የነበረ ቢሆንም ይደረጉ በነበሩ ምዘናዎችና የመስክ ድጋፍና ክትትል ቅንጅታዊ ግንኙነቱ እየተሻሻለ የመጣ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

183. ፕሮግራሙን አስመልክቶ በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል ቅንጅታዊ አሰራሩ አጥጋቢ ባለመሆኑ የሚያደርጉት ክትትልና ድጋፍ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድና በተዋጣለት ሁኔታ እንዳይመራ፣ የሚሰጡትም ስልጠናዎች ግባቸውን እንዳይመቱ ከማድረጉም በላይ ከተሞቹ ከነሱ የሚፈልጉትን ድጋፍ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

184\. ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተሞች የመሠረተ ልማት ግንባታ ትግበራና አፈፃፀም ውጤታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተተገበረ መሆኑን እንዲሁም የተዘረጋውን ሥርዓት ለመተግበር የሚካሄደው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

**ዕቅድና በጀትን በተመለከተ** (Planning and Budgeting)

- ✓ በፕሮግራም ኦፕሬሽናል መሰረት የመሠረተ ልማት ዕቅድ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 24 እ.ኤ.አ እያዘጋጁ የማያቀርቡ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ የየሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን የማያዘጋጁ ከተሞች መኖራቸው፣

**የመሠረተ ልማት አውታሮች አስተዳደርን በተመለከተ** (Asset Management)

- ✓ ሁሉም ከተሞች ለጥገና ለሚያስፈልጋቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች ትኩረት ሰጥተው የማይሰሩ መሆኑ፣
- ✓ የሚፈለገውን የጥገና በጀት የማይመድቡ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ ጥገና የሚወጣው በጀት አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 ፐርሰንት ማነስ የሌለበት ሊሆን እንደሚገባ በፕሮግራም ኦፕሬሽን ማኑዋሉ ላይ ቢቀመጥም ከተጠቀሰው በታች አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች መኖራቸው፣

**የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ** (Financial Management)

- ✓ አንዳንድ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ከተካሄደላቸው በኋላ በጥናቱ መሰረት ወደ ስራ ሳይገቡ ዓመታት የሚያልፉ መሆናቸውና እንደገና ሌላ ጥናት ሊካሄድላቸው መሆኑ፣
- ✓ ለትልልቅ ፕሮጀክቶች (ትልቅ የገበያ ማዕከላት፣ ቄራ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ የጠጠር መንገድ) የአዋጭነት ጥናት ሳይካሄድላቸው ወደ ትግበራ የሚገባ መሆኑ፣

- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የሚዘጋጁት ቢል ኦፍ ኳንቲቲዎች ሁሉንም ስራዎች የማያካትቱ መሆናቸው በአንዳንድ ከተሞች ደግሞ መካተት የሌለባቸው ስራዎች የሚካተቱ መሆኑ፣
- ✓ በአብዛኛዎቹ ከተሞች መሰረተ ልማቶች ለመገንባት የተዘጋጀው የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ (Capital Investment Plan (CIP) ላይ የተያዘው በጀትና በኮንትራት ውሉ ላይ የተቀመጠው ዋጋ መካከል ልዩነቶች መኖራቸው፣
- ✓ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ የማይጠናቀቁ መሆኑ፣
- ✓ አንዳንድ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውል በተገባላቸው ዋጋ እንደማይጠናቀቁ፣
- ✓ ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለማስፋፊያ ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ የማይጠቀሙበት ከተሞች መኖራቸው፣

**የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ግዢን በተመለከተ** (Procurment)

- ✓ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ማለትም Preliminary Design (Survey Data) እና የተለያዩ Drawing የማያዘጋጁ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ በየዓመቱ የሚሰሩት የፕሮጀክት ዲዛይኖች በሌላ አካል የማይከለሱ፣ የማይረጋገጡና የማይፀድቁ እንደሆነ፣
- ✓ የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች ሳይከናወኑ ግንባታዎች የሚከናወኑ መሆኑ፣
- ✓ ግዢዎች (የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች) የመሠረተ ልማት ዕቅዱ (CIP) ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማይካሄዱ መሆኑ፣
- ✓ ዓመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያካሄዱ (Annual Performance Assessment) ተቋማት ግዢ በወቅቱ የማይካሄድ መሆኑ፣

**ገቢን በራስ አቅም የመሰብሰብና የማሳደግ አቅምን በተመለከተ** (Own Source Revenue Enhancement)

- ✓ የከተሞች የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ አንጻር አነስተኛ መሆንና በእቅዱ መሰረት ገቢን አለመሰብሰብ እና በየዓመቱም ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት የማያሳድጉ ከተሞች መኖራቸው፣

**ግልፅነትና ተጠያቂነትን በተመለከተ (Accountability and Transparency)**

- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና የመሬት አስተዳደርን በተመለከተ የዜጎች ቻርተር ኮፒ በክፍሎቹ የሌለ ወይም ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ✓ ተገልጋዮች በትክክለኛው የመመዝግቢያ ፎርማት ላይ የማይመዘገቡ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርቶች የማይዘጋጁ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ ደካማ የምዝገባና የዶክመንቴሽን አያያዝ መኖር (Poor Documentation and Record Keeping) ያላቸው ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ የመሬት አስተዳደር ክፍል በስታንዳርዱ መሠረት ያልተዋቀረ መሆኑ፣
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች ውስጥ ነዋሪዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት እንደማያገኙ፣
- ✓ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት በስታንዳርዱ መሠረት የማይሰጡና (የደረቅ ቆሻሻ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና የመሬት አስተዳደር እስታንዳርዶች) መረጃዎችን በአግባቡ የማይዙ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ በተጠያቂነትና ግልፅነት (Accountability and Transparency) ረገድ አብዛኞቹ ክልሎችና ከተሞች ከመካከለኛው (መካከለኛው 64 ነው) ያነሰ እስኮር (ውጤት) ማምጣታቸው፣

**የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናቶች ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘቡ መሆኑን በተመለከተ (Environmental and Social Safeguards)**

- ✓ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናት የሚዘጋጁትና በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ይሁንታ የሚያገኙት ፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ መሆኑ፣
- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ ሕብረተሰቡን ሳያማክሩ እንደሚዘጋጁ፣ ዓመታዊ የአተገባበር እቅድ የማያዘጋጁ ከተሞች መኖራቸው፣
- ✓ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲሰራ የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ቢኖሩም ሆኖም የሕብረተሰብ የመልሦ ማስፈር ጥናት ሳይከናወን እንደሚሰራ፣ የአካባቢያዊ ቁጥጥር ዕቅድ ሳይኖራቸው የሚዘጋጁ መሆናቸው፣

- ✓ በአንዳንድ ከተሞች ለመጥቀስ ያህል በዲላ፣ ይርጋለም፣ ሆሳዕና፣ አረካ፣ ሚዛን አማን፣ ቡታጅራ፣ ደብረ ብርሃን ወዘተ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሲከናወን ቼክሊስቶቹ በሚገባ ሳይሟሉ እንደሚዘጋጁ፣ ዓመታዊ የክትትል ሪፖርት ሳይቀርብ እንደሚዘጋጅ፣
- ✓ በነዋሪዎች መግቢያ አካባቢ የውሃ መውረጃ ቦዮች ሲሰሩ ክፍት ሆነው መሰራታቸው በህብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆናቸው ለመጥቀስ ያህል ወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና ወዘተ፣ አንዳንድ መንገዶች ሲሰሩ የውሃ መውረጃ ቦዮች አብረው ባለመሰራታቸው በመንገዱና በነዋሪዎች ቤት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣
- ✓ በአረካ ለዝቅተኛ ህብረተሰቦች ቤቶች ሲገነባ የመፀዳጃ ቤቶች ሳይኖራቸው እንደተገነቡ፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች ወደ ደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች መለወጣቸው፣
- ✓ በሚዛን አማን ለኮሶኮል ወንዝ ድልድይ ለመስራት የተቆፈረው ቦታ ጥልቀት ያለው ጊዜያዊ ኩሬ መፍጠሩና አጥር ስላልታጠረ በሰዎችና በእንስሳት እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣
- ✓ ቦርከና ወንዝ የደረቅ ቆሻሻና የግንባታ ግብዓቶች መጠራቀሚያ መሆን፣
- ✓ በአብዛኛው የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ልየታ (Screening) ሪፖርት ሲሰራ ከዓለም ባንክ ፈንድ ለመጠቀም ብቻ ሲባል እንጂ ከዘለቄታዊ ጥቅም አንፃር ታይቶ የማይሰራ እንደሆነና የአካባቢያዊና ማህበራዊ ልየታ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአንዱን ለሌላው ኮፒ ፔስት በማድረግ ሪፖርቶቹ እንደሚዘጋጁ፣

**የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ (Job Creation)**

- ✓ በአንዳንድ ከተሞች የስራ እድሎች በዕቅዱ መሠረት አለመፈጠሩ፣

**የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ መሰራታቸውን በተመለከተ (Quality of Infrastructure)**

- ✓ የኮብል ስቶን ግንባታ ስራ የጥራት ችግሮች መኖር፣
- ✓ የኮብል ስቶን መንገዶች ከተሰሩበት አላማ ውጭ በግንባታ ዕቃዎች (ቁሳቁሶች) መከማቻ እንደሆኑና እየተበላሹ መሆኑ፣
- ✓ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተሰርተው የተጠናቀቁ ሼዶች የሲሚንቶና የተለያዩ እንጨቶች ማከማቻ እንዲሆኑ መደረጉ፣

- ✓ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ የማይተላለፉ እና ሲጠናቀቁም የሚመለከተው ሃላፊም በወቅቱ ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በከተሞች ከፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ሰነዶች በየሥራ ዘመናቸው በዓመት ምህረት ቅደም ተከተላቸው መሰረት ያልተቀመጡ መሆናቸውን፣
- ✓ ከ2001-2006 ዓ.ም ያሉት የፕግራሙ መረጃዎችና ሰነዶች ከ2001 ዓ.ም APA (Annual Performance Assesment) ሪፖርት በስተቀር ሌሎች ተጠይቀው ያልቀረቡ መሆኑ፣
- ✓ በፌዴራል እና በክልል ያሉ ባለሙያዎች መካከል ያለው የመረጃ ልውውጥ አነስተኛ መሆኑ፣
- ✓ በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ መሆኑ፣ በቂ ያልሆነ ድጋፍ በሪጅናል ሞባይል ቲም መኖሩና የፌዴራል ሞባይል ቲም ችግሩን ለማቃለል በክልሎች በቀጥታ ገብቶ ድጋፍ እያደረገ መሆኑ፣

185. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

186. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት በመፍጠር በሶስተኛው ዩ ኤል ጂ ዲ ፒ ፕሮግራም ዓላማን ለማሳካት ሊሰሩ የታቀዱት የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣ የከተሞች የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ የከተሞች የገቢ አሰባሰብ አቅም ማሳደግ እና ሌሎች ሥራዎች ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እንዲሁም መንግስት ለወደፊት በራሱ አቅም ሊገነባቸው እና ሊያሰፋፋ ለሚያቅዳቸው የፕሮጀክት ግንባታዎች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

**ዕቅድና በጀትን በተመለከተ** (Planning and Budgeting)

- ✓ ከተሞቹ ማግኘት የሚገባቸውን ነጥብና ከፍተኛ ገንዘብ እንዳያጡ፣ በርካታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጀምሩና በወቅቱ እንዲጠናቀቁ እንዲሁም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲሰሩ የሶስት ዓመቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱ በበቂ መረጃ፣ እውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ እንዲዘጋጅ ሊደረግና በወቅቱ በማጸደቅ ወደ ሥራ እመግባት አለባቸው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይሄ ስለመደረጉ ከፍተኛ ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ከተሞቹ ከፕግራሙ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረቱን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

**የመሠረተ ልማት አውታሮች አስተዳደርን በተመለከተ** (Asset Management)

- ✓ በከተሞቹ የሚገኙት አብዛኛዎቹ መሰረተ ልማቶች ጥገና ስለሚያስፈልጋቸው ከተሞች ከአዳዲስ የመሠረት ልማት ግንባታዎች ጎን ለጎን ለነዚህ መሰረተ ልማት አውታሮች አይነተኛ ትኩረት እንዲሰጡና ሥራው ቀጣይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው የሲአይፒያቸውን 10% ወይም የአጠቃላይ የከተማውን ሃብት 2% ለጥገና በጀት እንዲመድቡና በየዓመቱ በእቅድ እየያዙ መተግበር እንዲጀምሩ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ከፍተኛ ክትትልና እገዛ ሊደርጉላቸውና ጥገናው በራስ ኃይል(አቅም) ወደፊት ለመስራና ዘላቂነት እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡

**የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ (Financial Management)**

- ✓ ከተሞች በፕሮግራሙ ለሚያሰሩት ትልልቅ ፕሮጀክቶች (ትልቅ የገበያ ማዕከላት፣ ቄራ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ የጠጠር መንገድ) የአዋጭነት ጥናት እንዲካሄድላቸው ሊያደርጉና በጥናቱ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ እንዲሁም በአንዳንድ ከተሞች ስለ አዋጭነት ጥናት ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ረገድ ከተሞች ያለባቸውን ክፍተት እየለየ ትኩረት ሰጥቶ ተከታታይነት ያለው ስልጠናና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ ወጪ ወጥቶባቸው ከተጠኑ በኋላ ወደ ስራ እንዲገባ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እገዛ እና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ ከተሞቹ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ (Bill of Quantity) ሲያዘጋጁ የተሟላ ትክክለኛ የሆነና በተቋራጮቹ የሚሰራው ስራ ሁሉንም ዋና ዋና ስራዎች እንዲካተቱ ከተሞች ሊደርጉ ይገባል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሚታዩ የአቅም ክፍተቶች ካሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ በየጊዜው መሻሻል መኖሩን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡
- ✓ ከተሞች የመሰረት ልማት ግንባታቸውንም ሆነ የጥገና እቅዳቸውን በእቅዱ መሰረት በመተግበር ተጨማሪ ለሌላ ፕሮጀክት ሊሆን የሚችል ገንዘብ እንዲያገኙ በየደረጃው ተገቢው ድጋፍና ክትትል እንዲሁም እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም ከተሞቹ ለሚያሰሯቸው እያንዳንዱ ፕሮጀክቶች ሲአይፒ ላይ ባቀዱት መሠረት እንዲከፍሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ ድጋፍና እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
- ✓ ፕሮጀክቶቹ በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራቸው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከተሞች ተገቢውን ክትትል ሊያደርጉና ላልተገባ ተጨማሪ ጊዜና ወጪ እንዳይዳረጉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህብረተሰቡም እሮሮ እንዳይነሳባቸው ፕሮጀክቶች በወጣላቸው የጊዜ ሰሌዳና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሁሉን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በየዓመቱ በዕቅድ በመያዝ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ✓ የፕሮግራሙ ዓላማ እንዲሳካ፣ ከተሞች ገጽታቸውን ከመቀየር አኳያ የሚውለውን በጀት ሙሉ ለሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ የምክክር መድረክ በማዘጋጀትና፣ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ከተሞች

የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ እንዲጠቀሙበት አይነተኛ አስተዋፅኦ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ከ2001 በጀት ዓመት ጀምሮ በተደጋጋሚ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ከተሞች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ልዩ ክትትልና ድጋፍ ሊያደረግላቸው ይገባል፡፡

**የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ግዢን በተመለከተ** (Procurment)

- ✓ ከተሞቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን እንዲዘጋጁ፣ የሚዘጋጁትም ዲዛይኖች ገለልተኛ በሆነ አካል ሊከለሱይገባል፡፡ በፌዴራል ሞባይል ቡድንና ይሄን ፕሮግራም እየረዱ ባሉት አማካሪዎች ከፍተኛ ግምገማ በማድረግ ከተሞቹን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የአፈር ምርመራና ሌሎች ምርመራዎች ሳይከናወኑ ግንባታዎች እዳይከናወኑ በየደረጃው ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር በማደረግ የመሰረተ ልማቶቹ የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ በአብዛኛዎቹ ከተሞች ግዢዎች (የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች) ሲከናወኑ የመሠረተ ልማት ዕቅዱ (CIP) ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ባለመካሄዳቸው በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ የማይጀመሩና የማይጠናቀቁ በመሆናቸው ሚ/ር መ/ቤቱ በዚህ ረገድ ለከተሞች ስልጠና ሊሰጥና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
- ✓ ከፕሮግራም ፈንዱ ለከተሞች የሚለቀቀው ገንዘብ በማሳወቅ ረገድ መዘግየት እንዳይፈጠር፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ዕቅድ ዝግጅት በወቅቱ እንዲካሄድ፣ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀመሩና ሚ/ር መ/ቤቱ በዚህ ረገድ በርካታ የአሜሪካ ዶላር እንዳያጣ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በወቅቱ ማከናወን ይኖርበታል፡፡

**ገቢን በራስ አቅም የመሰብሰብና የማሳደግ አቅምን በተመለከተ** (Own Source Revenue Enhancement)

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሞች በፕሮግራሙ ላይ በተቀመጠው መሰረት በየዓመቱ ገቢያቸውን በ10 ፐርሰንት ባነሰ ሁኔታ የሚያሳድጉትን ከተሞች ተለይቶ የገቢ አሰባሰባቸው የሚያድግበትን ከእቅድ አንጻር አነስተኛ የሆነበትን መንስኤ አጥንቶ የሚሻሻልበትን መንገድ ከሚመለከታቸው

ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ሊያደረግላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከገቢ ጋር በተያያዘ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተከታታይ የአቅም ግንባታ እና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

**ግልፅነትና ተጠያቂነትን በተመለከተ** (Accountability and Transparency)

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዜጎች ቻርተር የሌላቸው ማዘጋጃ ቤቶችና ሌሎች በፕሮግራሙ የታቀፉ ተቋማት ያላቸው ከተሞች እንዲያዘጋጁና ከተሞች በቻርተሩ መሰረት ተገልጋዮቻቸውን ሊያተናግዱ እና በትክክለኛው የመመዘግቢያ ፎርማት ላይ እንዲመዘግቡ ድጋፍ ሊደርግላቸው፣ ይገባል፡፧ በተጨማሪም የሚከናወኑ ሥራዎች አስመልክቶ በየሩብ አመቱ የአፈፃፀም ሪፖርቶች በወቅቱ ሊያዘጋጁና በማያዘጋጁት ላይ ደግሞ ተጠያነት የሚኖርበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

**የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናቶች ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘቡ መሆኑን በተመለከተ** (Environmental and Social Safeguards)

- ✓ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር ጥናት የግንባታ ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊጠኑና ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጡት ተፅእኖ ሚቀነስበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

**የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን በተመለከተ** (Job Creation)

- ✓ በከተሞቹ በዕቅዱ መሰረት ለነዋሪዎቻቸው ጊዜያዊና ቋሚ የስራ ዕድል በፕግራሙ አማካኝነት ሊፈጥሩና በከተሞች ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥርን ከመቀነስ አኳያ ፕሮግራሙ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲሳካ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሥራ ዕድል ለመፍጠር በፕሮግራሙ የተቀመጠውን አላማ ለማሳካት የበኩልን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

**የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ መሰራታቸውን በተመለከተ** (Quality of Infrastructure)

- ✓ በፕሮግራሙ የተሰሩ እየተገነቡ ያሉ እና የሚገነቡት የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ጥራታቸውን ጠብቀው ሊገነቡ እና ይህን በማያሟላ መልክ የሚሰሩ በየደረጃው ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተገነቡት መሰረተ ልማቶች

በየጊዜው እየተበላሹ መንግስትም አላስፈላጊ ወጪ እንዳያወጣ፣ ለጥገና የሚወጣውን ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ለማዳን እንዲሁም የሚሰሩት የፕሮጀክት ግንባታዎች ለተፈለገላቸው ዓላማ ሳይውሉና የሚፈልግባቸውን ቆይታ ሳያከናውኑ እንዳይበላሹ እና ህብረተሰቡ በዚህ ምክንያት ቅሬታና እሮሮ እንዳያነሳ በየደረጃው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የግንባታዎቹን ጥራት ለመጠበቅ ለጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትና በከተሞቹ ለሚገኙ ፕሮጀክቶቹን ለሚቆጣጠሩ የፕሮጀክት ኢንጂነሮችና ሌሎች ባለሙያዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር ስልጠናና የልምድ ልውውጥ በማዘጋጀት ባለሙያዎቹን ክህሎትና አቅም የሚገነባበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

- ✓ በፕሮግራሙ በተመደበ በጀት የተገነቡ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ህጋዊ ርክክብ ሊከናወንላቸው እና ወደ ህብረተሰቡ ሊተላለፉ ይገባል፡፡ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ርክክብ እንዲከናወንና ህብረተሰቡ እንዲጠቀምበት የማያደርጉ አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበት ግልጽ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ፕግራሙ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያሉና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በከተሞቹ የሚገኙ መረጃዎች በሥርዓት ተደራጅተውና ለቀጣይ ሥራና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መልኩ መቀመጣቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎቹም ሆነ ከተሞቹ ሊያረጋግጡ ይገባል፡ በኦዲቱ ወቅት ሊቀርቡ ያልቻሉ ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም ስለ ፕሮግራሙ (ዩ ኤል ጂ ዲ ፒ አንድ) የሚያወሱ ሰነዶች ርክክብ ሊፈጸምባቸውና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ከፕግራሙ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ያላስረከቡ ወይም ርክክብ እንዲከናወን ያላደረጉ ኃላፊዎችም በየደረጃው ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ✓ በፌዴራል ደረጃ ባሉ ባለሙያዎችና በክልል ባሉ ባለሙያዎች የመረጃ ልውውጡ የሚመራበት ሥረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሪፖርት አቀራረብ ወጥ የሚሆንበት፣ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓቱ በቴክኖሎጂ የሚታገዝበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ✓ ፕሮግራሙን አስመልክቶ በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን ሁሉም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሊደረግ የሚገባና በሁለቱ መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራሩ በማጠናከር ክልሎች አቅማቸው የሚገነባበትና በራሳቸው ድጋፍና ክትትል በሂደት ማከናወን የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ✓ በተለይ በአላማጣና በአሶሳ ከተሞች ከፕሮግራሙ ትግበራ ጋር ተያይዘው የተከሰቱት ብልሹ አሰራሮች በየደረጃው እርምጃ ሊወሰድባቸው እና እስከአሁን ምንም እርምጃ ያልተወሰደባቸው እንደጉዳዩ አይነት ከአስተዳደረዊ እርምጃ ጀምሮ እስከ የከተሞቹና የክልሉ የፍትህ አካላት በማሳወቅ ጉዳዩን እንዲያጣራ ማድረግና የተከሰቱት ሁኔታዎች እልባት እንዲያገኙ ከተሞች፣ ክልሎችና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ጉዳዩን አጣርተው እልባት እንዲያገኙ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የአዳማ፣ የባህር ዳር፣ የደብረ ታቦር፣ የዲላ፣ የሐዋሳ እና የባቱ (ዝዋይ) የከተማ ከንቲባዎች፣ ምክትል ከንቲባዎች፣ ፕሮጀክት ኢንጂነሮች፣ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅእኖ ባለሙያዎች እና የከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም የከተማ ስራ አስኪያጆች እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ አንድ፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| 1.የከተሞች የመሰረተ-ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የእቅድ ዝግጅት እና አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መደረጋቸውን መገምገም፣ | 1. የከተማ አስተዳደሮቹ የ3 ዓመት የመሰረተ-ልማት እቅድ (*Capital Investment Plan*) ከትግበራ እቅድ ጋር አያይዘው ሊያዘጋጁና የከተማ ምክር ቤቱም በወቅቱ ሊያፀድቅ ይገባል፡፡ |
| | 2. የከተማ አስተዳደሮቹ በፕሮጀክቱ ለሚያከናውኑቸው እያንዳንዱ ተግባር መነሻ መረጃ (Baseline data) ሊኖራቸውና ውጤቱም ከመነሻው አንጻር ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 3. ከተሞች የመሰረተ-ልማት እቅዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት ገቢ ሊሰበስቡና በየዓመቱም ገቢያቸውን ከ10 ፐርሰንት ባላነሰ ሁኔታ ሊያሳድጉ ይገባል፡፡ |
| | 4. ከተሞች የአገልግሎት ስታንዳርድ (የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና የመሬት አስተዳደር) አውጥተው ሊያዘጋጁና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 5. የከተማ አስተዳደሩ ለጥገና (መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የውሃ መውረጃ ቦዮች፣ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች፣ የገበያ ቦታዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ወዘተ) የሚወጣውን በጀት ሊያዘጋጅና አፈፃፀሙም ከእቅዱ ከ80 ፐርሰንት ማነስ የሌለበት ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 6. የከተማ አስተዳደሮቹ ለፕሮጀክቶቹ የጨረታ ሂደት ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ዲዛይን ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡ |
| | 7. የፕሮጀክት ኢንጂነሮቹ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የዲዛይን ጥራት ኢንዲኖራቸው ከመስመር መረጣ ጀምሮ የአፈር ምርመራና የቅየሳ (ሰርቬይ) ጥናት በአግባቡ መሰራቱን ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| | 8. ሚ/ር መ/ቤቱ የጨረታ እና የተቋራጭ መረጣ ሂደቶች በመሰረተ-ልማት ግንባታ እቅዱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መካሄዳቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 9. ሚ/ር መ/ቤቱ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ (*Annual performance Assessment*) ለሚያካሂዱ ተቋማት የሚሆን ግዥን በወቅቱ ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 10.ሚ/ር መ/ቤቱ ከዚህ በፊት በተሳተፈባቸው የመሰረተ- ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ደካማ የስራ አፈፃፀም ያላቸው (አለም ባንክ በድህረ ገጽ ላይ እንዳይሳተፉ የከለከላቸው) ተቋራጮችና አማካሪዎች በአዲስ የጨረታ ሂደት እንዳይሳተፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11. ሁሉም የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ሊካሄድላቸው ይገባል፡፡ |
| | 12. የከተማ አስተዳደሮቹ የግዥ ሂደቶች የክልሉን የግዥ ሂደት ባሟላ መልኩ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| | ሊተገበሩና ከተቋማቱ ጋር የሚገባው ኮንትራት ኦዲት ለማድረግ በሚያመች መልኩ መረጃዎች ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | 13. ሁሉም ከተሞች ሂሳባቸውን በመስከረም 30 ዘግተው ለክልሎቹ ዋና ኦዲተሮች ሊያስረክቡና ኦዲቱም እስከ ጥር 7 ተዘጋጅቶ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ *(ፕሮግራም* |
| | 14. የክልሎቹ የግዢና የንብረት አስተዳደር ኤጀንሲዎች ከአራተኛው የአመታዊ አፈፃፀም ግምገማ ጀምሮ (4th APA) **የግዢ ኦዲት** ሊያከናውኑ ይገባል፡፡ |
| | 15. ከተሞቹ **ቢል ኦፍ ኳንቲቲ** (bill of Quntity) ሲያዘጋጁ የተሟላ ትክክለኛ የሆነና በተቋራጮቹ የሚሰራው ስራ ሁሉንም ዋና ዋና ስራዎች ሊያካትት |
| | 16. ከተሞቹ ለሚያሰሯቸው እያንዳንዱ ፕሮጀክቶች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ ሊከፍሉ አይገባም፡፡ (*መልካም ተሞክሮ*) |
| | 17. የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በዕቅድ በታቀደላቸው ጊዜና በኮንትራት ውል በተገባበት ዋጋ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ |
| | 18. ከተሞች ለመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ለማስፋፊያ እና ለጥገና ከፕሮግራም ፈንዱ የሚለቀቅላቸውን በጀት በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ |
| | 19. ተቋራጮች የሚሰሯቸው የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች በግንባታ ስፔሲፊኬሽን መሰረት ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 20. የፕሮጀክት ኢንጂነሮቹ ተቋራጭ ለግንባታ ያሰማራው የሰው ሃይል እና መሳሪያዎች በየወሩ በአማካሪው የሚረጋገጥ መሆኑን ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| | 21. ተቋራጮች ስራቸውን በተረከቡ በ28 ቀናት ውስጥ ለፕሮጀክት ኢንጂነሮቹ የስራ ፕሮግራማቸውን ሊያቀረቡ ይገባል፡፡ |
| | 22. የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወደ ህብረተሰቡ ሊተላለፉና የሚፈለገውን አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 23. የፕሮጀክት ኢንጂነሮቹ በየአመቱ፣ በየሩብ ዓመቱ ወይም በመ/ቤቱ የግዜ ሰሌዳ በታቀደና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ከአማካሪ ድርጅቶች የሚላክ የፕሮጀክት አፈፃፀምን መሰረት በማድረግ በመስክ ጉብኝት መረጃ በማሰባሰብ እና በማደራጀት የግንባታ ስራው በጥራት ስለመሰራቱ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች የፅሁፍ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 24. ሚ/ር መ/ቤቱ በዓመታዊ ዕቅዱ ውስጥ በተካተቱ ሁኔታዎች ከአማካሪና ከተቋራጮች ጋር በመሆን የሶስትዮሽ ግምገማ ሊያከናውን እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 25. ሚ/ር መ/ቤቱ፣ አማካሪ ድርጅቶቹ እና የክልሎች ሞባይል ቡድን በመዋቅሩ በተቀመጠው መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | *26.* የሁለተኛው ዩኤልጂዲፒ በዕቅዱ መሰረት አዳዲስ የስራ እድል ሊፈጥር |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| | ይገባል፡፡ |
| | 27. የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር እቅድ የምህንድስና ስራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | *28.* የመሰረተ ልማት ሲታቀድ የአካባቢውን ህብረተሰብ ግምት ውስጥ ያስገባና ያሳተፈ ሊሆን ይገባል። |
| | 29. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር እቅድ በክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሊዘጋጅና ሊጸድቅ ይገባል፡፡ |
| | 30. ሚ/ር መ/ቤቱ እና አማካሪ ድርጅችም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማና የህብረተስብ መልሶ ማስፈር እቅድ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | *31.* ሚ/ር መ/ቤቱና አማካሪ ድርጅቶች ለግንባታ አፈርና ድንጋይ የወጣባቸው እና ለክሬሸር ስራ እና ለማከማቻ ጥቅም ላይ የዋሉ ቦታዎች የተፈጥሮ ይዞታቸውን በጠበቀ መልኩ መመለሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡ |
| | 32. የህብረተሰብ መልሶ ማስፈር እቅድ ሲዘጋጅ ሴቶች፣ ልጆች፣ የአካል ጉዳተኞች እና በዕድሜ ከገፉ ሰዎች ጋር ምክክር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 33. ሁሉም የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነት ልየታ (*Screening*) ውስጥ ሊያልፉ ይገባል፡፡ |
| 2. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞችን የመሰረተ ልማት-ማስፋፊያ ፕሮግም ትግበራና አፈጻፀምን በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 34. ሚ/ር መ/ቤቱ የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕጀክቶችን በተመለከተ ስራ ተቋራጮች፣ የፕሮጀክት ኢንጂነሮች፣ የፌዴደራልና የክልል የሞባይል ቡድን እና APA የሚሰሩ አማካሪ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የአፈፃፀም ሪፖርቶች በስርዓት መያዛቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 35. በፌዴራል ደረጃ ባሉ ባለሙያዎችና በክልል ባሉ ባለሙያዎች የመረጃ ልውውጥ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 36. ሚ/ር መ/ቤቱ የመሠረተ ልማት ሃብት መረጃ ዳታ ቤዞችን በተናጠልና በጋራ በማዘጋጀት፣ መረጃዎቹንም በዘመናዊ መልኩ የማደራጀትና የመጠቀም አቅጣጫን ሊከተል ይገባል፡፡ |
| | 37. በስትሪንግና በቴክኒካል ኮሚቴ፣ በክልሎች እና በፌዴራል ሞባይል ቡድን መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 38. የፕሮጀክት ሰራተኞቹ የፕሮጀክት ሰነዶችና መመሪያዎች ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ |
| | 39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከተሞቹ ጋር በመሆን የምክክር መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 40. የፕሮጀክቶቹ ሰራተኞች ከመመሪያዎችና መረጃዎች ጋር በቂ ትውውቅ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 41. ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞች የሚፈፀሙ ክፍያዎች በማስረጃ የተደገፉ እንዲሆኑ በማድረግየሚከሰት የብልሹ አሰራርን ሊቀንስ ይገባል፡፡ |

## አባሪ ሁለት፡ የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢቻውን ሊዝን ጨምሮ በ10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች

| ተ.ቁ | ከተማ | የ2007 ዓ.ም አፈፃፀም % | የ2008 ዓ.ም አፈፃፀም % | ጭማሪ በማነስ/ በመብለጥ % |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ባህር ዳር | 102% | 100% | -2% |
| 2. | ደብረ ብርሃን | 156% | 163% | -7% |
| 3. | ጎንደር | 110% | 77% | -33% |
| 4. | ሞጣ | 155% | 133% | -22% |
| 5. | አዳማ | 114% | 88% | -26% |
| 6. | ወልዲያ | 121% | 124% | 3% |
| 7. | ቢሾፍቱ | 96% | 84% | -12% |
| 8. | ጅማ | 82% | 86% | -4% |
| 9. | ሻሸመኔ | 77% | 70% | -7% |
| 10 | አምቦ | 62% | 55% | -7% |
| 11 | አሰላ | 104% | 82% | -22% |
| 12 | ቡራዩ | 85% | 78% | -7% |
| 13 | ባቱ (ዝዋይ) | 91% | 88% | -3% |
| 14 | ነቀምቴ | 101% | 94% | -7% |
| 15 | ሮቤ | 103% | 101% | -2% |
| 16 | ሰበታ | 110% | 62% | -48% |
| 17 | ሐዋሳ | 99% | 82% | -17% |
| 18 | ዲላ | 81% | 77% | -4% |
| 19 | አረካ | 83% | 86% | 3% |
| 20 | ቡታጅራ | 114% | 99% | -15% |
| 21 | ይርጋ አለም | 93% | 72% | -21% |
| 22 | መቀሌ | 121% | 124% | 3% |
| 23 | አዲግራት | 119% | 106% | -13% |
| 24 | አክሱም | 113% | 74% | -39% |
| 25 | ሽሬ | 95% | 85% | -10% |
| 26 | አድዋ | 101% | 107% | 6% |
| 27 | ሁመራ | 79% | 84% | 5% |
| 28 | አሶሳ | 102% | 77% | -25% |
| 29 | ድሬደዋ | 73% | 57% | -16% |

በ2009 ዓ.ም ማዘጋጃ ቤታዊ ገቢያቸውን ከሊዝ ውጭ በ10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች

| ተ.ቁ | ከተማ | የ2009 ዓ.ም አፈፃፀም በፐርሰንት | የ2010 ዓ.ም አፈፃፀም በፐርሰንት | ጭማሪ በማነስ/በመብለጥ በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1) | ባህር ዳር | 125% | 94% | -31% |
| 2) | ደሴ | 147% | 104% | -43% |
| 3) | ጎንደር | 103% | 101% | -2% |
| 4) | ደብረ ብርሃን | 100% | 81% | -19% |
| 5) | ደብረ ማርቆስ | 104% | 104% | 0% |
| 6) | ደብረ ታቦር | 107% | 97% | -10% |
| 7) | ፍኖተ ሰላም | 102% | 93% | -11% |
| 8) | ሞጣ | 105% | 110% | 5% |
| 9) | ወልዲያ | 99% | 102% | 3% |
| 10) | አዳማ | 109% | 68% | -41% |
| 11) | አምቦ | 75% | 70% | -5% |
| 12) | ሮቤ | 89% | 70% | -19% |
| 13) | ሰበታ | 60% | 52% | -8% |
| 14) | አርባ ምንጭ | 138% | 104% | -34% |
| 15) | ዲላ | 75% | 47% | -28% |
| 16) | ሶዶ | 98% | 104% | 6% |
| 17) | አረካ | 96% | 96% | 0% |
| 18) | ቡታጅራ | 99% | 99% | 0% |
| 19) | ሆሳዕና | 104% | 68% | -44% |
| 20) | ሚዛን አማን | 100% | 99% | -1% |
| 21) | ይርጋ አለም | 91% | 94% | 3% |
| 22) | መቀሌ | 104% | 107% | 3% |
| 23) | ሽሬ | 91% | 97% | 6% |
| 24) | አላማጣ | 116% | 103% | -13% |
| 25) | ሁመራ | 81% | 88% | 7% |
| 26) | ውቅሮ | 99% | 100% | 1% |
| 27) | ጅግጅጋ | 99% | 105% | 6% |
| 28) | ጋምቤላ | 170% | 69% | -101% |
| 29) | ሰመራ | 116% | 111% | -5% |
| 30) | ድሬደዋ | 107% | 93% | -14% |

## በ2010 ዓ.ም ማዘጋጃ ቤታዊ ገቢያቸውን ከሊዝ ውጭ በ10 ፐርሰንት ያላሳደጉ ከተሞች

| ተ.ቁ | ከተማ | የ2009 ዓ.ም አፈፃፀም በፐርሰንት | የ2010 ዓ.ም አፈፃፀም በፐርሰንት | ጭማሪ በማነስ/በመብለጥ በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ደብረ ማርቆስ | 104% | 99% | -5% |
| 2. | ደብረ ታቦር | 97% | 86% | -11% |
| 3. | ፍኖተ ሰላም | 93% | 99% | 6% |
| 4. | ባህር ዳር | 94% | 102% | 8% |
| 5. | ጎንደር | 101% | 97% | -4% |
| 6. | ኮምቦልቻ | 145% | 103% | -42% |
| 7. | ሞታ | 110% | 103% | -7% |
| 8. | ወልዲያ | 102% | 100% | -2% |
| 9. | ድሬ ዳዋ | 92% | 45% | -50% |
| 10. | ሀረር | 93% | 56% | -37% |
| 11. | ጋምቤላ | 69% | 64 | -5% |
| 12. | ሻሸመኔ | 85% | 88% | 3% |
| 13. | አሰላ | 100% | 82% | -18% |
| 14. | ባቱ | 97% | 96% | -1% |
| 15. | ቡራዩ | 87% | 91% | -4% |
| 16. | ነቀምቴ | 108% | 102% | -6% |
| 17. | ሮቤ | 70% | 79% | 9% |
| 18. | ሃዋሳ | 102% | 102% | 0% |
| 19. | አርባ ምንጭ | 104% | 102% | -2% |
| 20. | ዲላ | 47% | 46% | -1% |
| 21. | ሶዶ | 104% | 102% | -2% |
| 22. | አረካ | 98% | 79% | -19% |
| 23. | ቡታጅራ | 99% | 98% | -1% |
| 24. | ሚዛን አማን | 99% | 98% | -1% |
| 25. | ይርጋ አለም | 94% | 100% | 6% |
| 26. | መቀሌ | 107% | 104% | -3% |
| 27. | አዲግራት | 91% | 79% | -12% |
| 28. | አክሱም | 104% | 92% | -12% |
| 29. | አድዋ | 120% | 105% | -15% |
| 30. | አላማጣ | 103% | 98% | -5% |
| 31. | ዉቅሮ | 100% | 103% | 3% |
| 32. | አሶሳ | 115% | 87% | -28% |

## አባሪ 3፡ የከተሞች የገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞብላይዘሽንና ፋይናንስ ቢሮ አደረጃጀት



## አባሪ 4፡ በወቅቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን ያላዘጋጁ ከተሞች

| በጀት አመት | በወቅቱ የመሠረተ ልማት ዕቅዱን ያላዘጋጁ ከተሞች | የተከለሰውን የመሠረተ ልማት ዕቅዱን በወቅቱ ያላቀረቡ ከተሞች | በጀት አመቱ ካለፈ በኋላ ያቀረቡ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 1. ሚዛን አማን 21/01/2007 ዓ.ም<br>2. አክሱም 23/01/2007 ዓ.ም፣<br>3. አረካ 03/02/2007 ዓ.ም፣<br>4. አድዋ 18/02/2007 ዓ.ም<br>5. ቡራዩ 19/2/2007 ዓ.ም (ጥቅምት 2014)፣<br>6. ኮምቦልቻ 26/02/2007 ዓ.ም፣<br>7. ውቅሮ 27/02/2007 ዓ.ም፣<br>8. ቡታጅራ 27/02/2007 ዓ.ም<br>9. አክሱም 27/02/2007 ዓ.ም፣<br>10.አርባ ምንጭ 02/03/2007 ዓ.ም<br>11.ደብረ ታቦር 02/03/2007 ዓ.ም (ህዳር 2014)<br>12.ጅግጅጋ 04/05/2007 ዓ.ም (ጥር 2015)፣ | 1. ሁመራ 28/6/2007 ዓ.ም (የካቲት 2014)፣<br>2. ነቀምት 16/10/2007 ዓ.ም፣<br>3. ጋምቤላ 18/07/2007 ዓ.ም<br>4. ሆሳዕና 19/08/2007 ዓ.ም (መጋቢት 2015)፣<br>5. ወላይታ ሶዶ 21/08/2007 ዓ.ም<br>6. አክሱም 07/08/2007 ዓ.ም (ሚያዚያ 2015)፣<br>7. አሰላ 16/09/2007 ዓ.ም (ግንቦት 2015)<br>8. ባቱ 01/10/2007 ዓ.ም፣<br>9. ሐረር 05/10/2007 ዓ.ም፣<br>10.ጅማ 09/10/2007 ዓ.ም፣<br>11.ውቅሮ 11/10/2007 ዓ.ም፣<br>12.ሽሬ 15/10/2007 ዓ.ም፣<br>13.ኮምቦልቻ 16/10/2007 ዓ.ም፣<br>14.አምቦ 18/10/2007 ዓ.ም፣<br>15.ፍኖተ ሰላም 24/10/2007 ዓ.ም<br>16.ጎንደር 30/10/2007 ዓ.ም (ሰኔ 2015)፣ | |
| በ2008 | 1. ጎንደር 14/12/2008 ዓ.ም<br>2. ሻሸመኔ 16/12/2007 ዓ.ም (ነሐሴ 2015)፣<br>3. አርባ ምንጭ 20/01/2008 ዓ.ም፣<br>4. በወላይታ ሶዶ 21/01/2008 ዓ.ም፣<br>5. ሰመራ-ሎጊያ 25/01/2008 ዓ.ም፣<br>6. አሶሳ 28/01/2008 ዓ.ም፣<br>7. ሁመራ 10/02/2008 ዓ.ም፣ | 1. ሻሸመኔ 08/07/2008 ዓ.ም<br>2. ዲላ 22/07/2009 ዓ.ም (መጋቢት 2016)<br>3. ነቀምቴ 05/08/2008 ዓ.ም<br>4. አዲግራት 11/08/2008 ዓ.ም (ሚያዚያ 2016).<br>5. ሮቤ 23/08/2008 ዓ.ም (ግንቦት 2016)<br>6. አክሱም 01/10/2008 ዓ.ም፣ | ጋምቤላ 22/10/2008 ዓ.ም ሐረር 25/10/2008 ዓ.ም (ሐምሌ 2016)፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 8. ሐዋሳ 11/02/2008 ዓ.ም<br>9. ሮቤ 19/02/2008 ዓ.ም (ጥቅምት 2015) | 7. መቀሌ 02/10/2008 ዓ.ም፣ (ሰኔ 2016) | |
| በ2009 ዓ.ም | 1. መቀሌ 20/12/2008 ዓ.ም (ነሐሴ 2016)፣<br>2. ሻሸመኔ 13/01/2009 ዓ.ም (መስከረም 2016)<br>3. ቢሾፍቱ 27/01/2009 ዓ.ም፣<br>4. አረካ 01/02/2009 ዓ.ም፣<br>5. አዲግራት 01/02/2009 ዓ.ም፣<br>6. ውቅሮ 04/02/2009 ዓ.ም፣<br>7. ሽሬ 08/02/2009 ዓ.ም፣<br>8. አርባምንጭ 10/02/2009 ዓ.ም፣<br>9. ጋምቤላ 11/02/2009 ዓ.ም፣<br>10. ሰመራ ሎጊያ 14/02/2009 ዓ.ም፣<br>11. ይርጋ አለም 16/02/2009 ዓ.ም<br>12. ሐዋሳ 16/02/2009 ዓ.ም (ጥቅምት 2016) | 1. ጅግጅጋ 6/07/2010 ዓ.ም (መጋቢት 2017)<br>2. ሚዛን አማን 22/7/2009 ዓ.ም፣<br>3. ሆሳዕና 22/07/2009፣<br>4. ቢሾፍቱ 27/07/2009 ዓ.ም፣<br>5. ይርጋአለም 27/07/2009 ዓ.ም፣<br>6. አዳማ 28/07/2009 ዓ.ም፣<br>7. መቀሌ 03/08/2009 ዓ.ም፣<br>8. ድሬደዋ 03/08/2009 ዓ.ም፣<br>9. ሰበታ 04/08/2009 ዓ.ም፣<br>10. ነቀምቴ 5/08/2009፣<br>11. ሮቤ 5/08/2009 ዓ.ም፣<br>12. ሐረር 5/08/2009 ዓ.ም፣<br>13. ሐዋሳ 05/08/2009 ዓ.ም፣<br>14. አሶሳ 10/08/2009 ዓ.ም፣<br>15. አምቦ 11/08/2009 ዓ.ም፣<br>16. ወላይታ ሶዶ 12/08/2009 ዓ.ም (ሚያዚያ 2017)፣ | |
| በ2010 | 1. ሽሬ 16/12/2009 ዓ.ም፣<br>2. አድዋ 16/12/2009 ዓ.ም፣<br>3. አክሱም 16/12/2009 ዓ.ም (ነሐሴ 2015)፣<br>4. ጅግጅጋ 03/13/2009 ዓ.ም፣<br>5. ሁመራ 17/12/2009 ዓ.ም፣<br>6. ውቅሮ 15/01/2010 ዓ.ም፣<br>7. መቀሌ 12/01/2010 ዓ.ም፣<br>8. አድግራት 11/01/2010 ዓ.ም፣<br>9. አላማጣ 12/01/2010 ዓ.ም፣ (መስከረም | 1. አላማጣ 30/6/2010 ዓ.ም፣<br>2. አዲግራት 30/06/2010 ዓ.ም፣<br>3. ውቅሮ 3/07/2010 ዓ.ም፣<br>4. መቀሌ 4/07/2010 ዓ.ም፣<br>5. አክሱም 4/07/2010 ዓ.ም፣<br>6. ሁመራ 13/7/2010 ዓ.ም፣<br>7. ሰመራ ሎጊያ 13/07/2010 ዓ.ም፣<br>8. ድሬደዋ 17/07/2010 ዓ.ም፣<br>9. ሀረር 19/07/2010 ዓ.ም | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 2017)፣<br>10.ሰመራ-ሎጊያ 23/01/2010 ዓ.ም፣<br>11.ድሬደዋ 24/01/2010 ዓ.ም፣<br>12.ሀረር 25/01/2010 ዓ.ም (ጥቅምት 2017)፣ | 10.ጅግጅጋ 20/07/2010 ዓ.ም (መጋቢት 2018)<br>11.ጋምቤላ 26/07/2010 ዓ.ም (ሚያዚያ 2018)<br>12.ሽሬ 07/09/2010 ዓ.ም (ግንቦት 2018) | |

# አባሪ 5፡ ከ2007 እስከ 2010 ከ80 ከመቶ በታች የጥገና አፈጻጸም ያላቸው ከተሞች

| 2007 | የከተማው ስም | የተያዘው በጀት | አፈጻጸም (በብር) | አፈጻጸም (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍኖተ ሰላም | 666,505.45 | 168,552.43 | 25% |
| 2 | ደብረ ብርሃን | 237,500 | 177,128 | 75% |
| 3 | አክሱም | 785,620 | 363,710.27 | 46% |
| 4 | አላማጣ | 500,00 | 339,367.50 | 68% |
| 5 | ሰበታ | 5,038,000 | 3,620,208.45 | 72% |
| 6 | አሶሳ | 1,4,000 | 0.00 | 0% |
| 7 | ጋምቤላ | 4,362,580 | 0057 | 14% |
| 8 | ሰመራ | 49,000 | 0.00 | (0%) |
| 2008 | | | | |
| 1 | ፍኖተ ሰላም | 2,512,258.70 | 1,278,984.00 | 51% |
| 2 | ደሴ | 7,500,000.00 | 5,625,000.00 | 75% |
| 3 | አሰላ | 5,882,143.98 | 3,594,017.41 | 61% |
| 4 | ባቱ (ዝዋይ) | 1,644,993.91 | 1,246,463.00 | 76% |
| 5 | ሮቤ | 1,784,000.00 | 821,316.66 | 46% |
| 2009 | | | | |
| 1 | ደብረ-ታቦር | 1,533,850.00 | 1,086,671.00 | 71% |
| 2 | አሰላ | 3,882,149.57 | 2,754,208.28 | 71% |
| 3 | ሐረር | 11,803,918.68 | 9,053,545.63 | 77% |
| 2010 | | | | |
| 1 | ደብረ ብርሃን | 8,473,164.00 | 2,475,785.41 | 29% |
| 2 | አምቦ | 6,764,183.35 | 798,289.22 | 12% |
| 3 | አሰላ | 6,480,367.14 | 4,570,057 | 71% |
| 4 | ነቀምቴ | 1,604,908.29 | 1,037,420.68 | 65% |
| 5 | ጋምቤላ | 4,618,001.30 | 2,266,884.53 | 49% |

አባሪ ስድስት፡ ከ2007 -2010 በጀት አመታት በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዝርዝር

| ክልል | በ ULGDP I እና II በየከተሞቹ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በ2007 በጀት ዓመት | በ2008 በጀት ዓመት | በ2009 በጀት ዓመት | በ2010 በጀት ዓመት | |
| ULGDP I የነበሩ ከተሞች | | | | | |
| አማራ | ✓ በደሴ 17፣<br>✓ በጎንደር 34፣<br>✓ በኮምቦልቻ 4፣ | ✓ | | ✓ በደሴ 2፣<br>✓ በጎንደር 8፣<br>በኮምቦልቻ 1፣ | ✓ |
| | 55 | | | 11 | 66 |
| ኦሮሚያ | ✓ በአዳማ 12፣<br>✓ በቢሾፍቱ 2፣<br>✓ በጅማ 28፣<br>✓ በሻሸመኔ 2፣ | ✓ በአዳማ 18፣<br>✓ በቢሾፍቱ 10፣<br>✓ በጅማ 17፣<br>✓ በሻሸመኔ 7፣ | ✓ በሻሸመኔ 29፣ | ✓ በአዳማ 10፣<br>✓ በቢሾፍቱ 30፣<br>✓ በጅማ 5፣<br>✓ በሻሸመኔ 4፣ | ✓ |
| | 44 | 52 | 29 | 49 | 174 |
| ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ | ✓ በአርባ ምንጭ 39፣<br>✓ በዲላ 3፣<br>✓ በወላይታ ሶዶ 26፣ | ✓ በሐዋሳ 22፣<br>✓ በአርባ ምንጭ 7፣<br>✓ በዲላ 4፣<br>✓ በወላይታ ሶዶ 7፣ | ✓ በሐዋሳ 10፣<br>✓ በአርባ ምንጭ 2፣<br>✓ በዲላ 7፣<br>✓ በሶዶ 5፣ | ✓ በሐዋሳ 31፣<br>✓ በአርባ ምንጭ 7፣<br>✓ በዲላ 36፣<br>✓ በወላይታ ሶዶ 18፣ | ✓ |
| | 68 | 40 | 24 | 92 | 224 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | ✓ በመቀሌ 98፣<br>✓ በአዲግራት 41፣<br>✓ በአክሱም 50፣<br>✓ በሽሬ 46፣ | ✓ በመቀሌ 81፣<br>✓ በአዲግራት 52፣<br>✓ በአክሱም 47፣<br>✓ በሽሬ እንደስላሴ 43፣ | ✓ በመቀሌ 79፣<br>✓ አዲግራት 58፣<br>✓ በአክሱም 45፣<br>✓ በሽሬ እንደስላሴ 39፣ | ✓ በመቀሌ 16፣<br>✓ በአዲግራት 1፣<br>✓ በአክሱም 1፣<br>✓ በሽሬ 1፣ | ✓ |
| | 235 | 223 | 221 | 19 | 698 |
| ሐረሪ | ✓ በሃረር 47 | በሐረር 18 | በሐረር 59 | በሐረር 55 | 179 |
| ድሬዳዋ | በድሬደዋ 21 | በድሬደዋ 20 | በድሬደዋ 53 | ✓ በድሬደዋ 36 | 130 |
| | 470 | 353 | 386 | 262 | 1471 |
| ULGDP II የተካተቱ ከተሞች | | | | | |
| አማራ | ✓ በደብረ ብርሃን 34፣<br>✓ በደብረ ታቦር 2፣<br>✓ በፍኖተ ሰላም 5<br>✓ በወልዲያ 17፣ | | | ✓ በደብረ ብርሃን 2፣<br>✓ በሞጣ 2፣<br>በወልዲያ 1፣ | ✓ |
| | 58 | | | 5 | 63 |
| ኦሮሚያ | ✓ በአምቦ 7፣<br>✓ በአሰላ 4፣<br>✓ በባቱ (ዝዋይ) 6፣<br>✓ በቡራዩ 21፣<br>✓ በሰበታ 33 | ✓ በአምቦ 9፣<br>✓ በአሰላ 1፣<br>✓ በባቱ (ዝዋይ) 3፣<br>✓ በቡራዩ 77፣<br>✓ በነቀምቴ 13፣<br>✓ በሮቤ 22፣<br>✓ በሰበታ 40፣ | ✓ በአምቦ 20፣<br>✓ በአሰላ 36፣<br>✓ ባቱ (ዝዋይ) 20፣<br>✓ በቡራዩ 106፣<br>✓ በነቀምቴ 42፣<br>✓ በሮቤ 35፣<br>✓ በሰበታ 66 | ✓ በአምቦ 27፣<br>✓ በአሰላ 19፣<br>✓ በባቱ (ዝዋይ) 13፣<br>✓ በቡራዩ 8፣<br>✓ በነቀምቴ 30፣<br>✓ በሮቤ 18፣<br>✓ በሰበታ 17፣ | ✓ |
| | 71 | 165 | 325 | 132 | 693 |
| ደቡብ | ✓ በሆሳዕና 1፣ | ✓ በአረካ 2፣ | ✓ በአረካ 2፣ | ✓ በአረካ 8፣ | ✓ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ብ/ብ/ሕ/ | በይርጋለም 1፣ | ✓ በቡታጅራ 5፣<br>✓ በሆሳዕና 3፣<br>✓ በሚዛን አማን 9፣<br>በይርጋለም 7፣ | ✓ በቡታጅራ 1፣<br>✓ በሆሳዕና 2፣<br>✓ በሚዛን አማን 6፣<br>በይርጋለም 8፣ | ✓ በቡታጅራ 6፣<br>✓ በሆሳዕና 7፣<br>✓ በሚዛን አማን 3፣<br>በይርጋለም 2፣ | |
| | 2 | 26 | 19 | 26 | 73 |
| ትግራይ | ✓ በአድዋ 40፣<br>✓ በአላማጣ 21፣<br>✓ በሁመራ 27፣<br>በውቅሮ 24፣ | ✓ በአድዋ 42፣<br>✓ በአላማጣ 14፣<br>✓ በሁመራ 16፣<br>✓ በውቅሮ 30፣ | ✓ በአድዋ 40፣<br>✓ በአላማጣ 31፣<br>✓ በሁመራ 17፣<br>✓ በውቅሮ 33፣ | ✓ በአድዋ 2፣<br>✓ በአላማጣ 1፣<br>✓ በሁመራ 2፣<br>✓ በውቅሮ 1፣ | ✓ |
| | 112 | 102 | 121 | 6 | 341 |
| ጋምቤላ | ✓ በጋምቤላ 4፣ | | | በጋምቤላ 13፣ | 17 |
| ሶማሌ | ✓ በጅጅጋ 1 | ✓ በጅጅጋ 3፣ | | | 4 |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | ✓ በአሶሳ 4፣ | | በአሶሳ 2፣ | በአሶሳ 1፣ | 7 |
| አፋር | ✓ | ✓ በሰመራ 2፣ | | | 2 |
| | 252 | 298 | 467 | 183 | 1200 |
| | 722 | 651 | 853 | 445 | 2671 |